"ሁለት ታጣቂዎች መድረኩ አካባቢ ከጠ/ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ጋር ተጋጭተዋል"

በአደጋው የተጎዱ ሰዎች ምን ይላሉ?

የፖለቲካ ሰዎች ስለ ሰላማዊ ሰልፉ

የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ምን አሉ?

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 11 ሰኔ 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99



ልዩ ዕትም

## በፈርዖን ቤት ያደገው ሙሴ

"ኢትዮጵያ ወደቀድሞ ገናናነቷ እንደምትመለስ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አይኑራችሁ"

"የይቅርታ ጉዞአችን ከተደናቀፈ፣ ተሸንፈናል ማለት ነው"

## ከቦምቡ ጥቃት በስተጀርባ

- የጥቃቱ ዒላማ ማነው?
- የደስሙካ 'ጥበቃ' ለምን?
- ጣቶች ወዴት ይጠቁማሉ?
- ኤፍ. ቢ. አይ. ምን ይሠራል?

**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ሰኔ 30 ይጠብቁን!**




ቁጥር 10 ዕትም


2 የጠ/ሚ የድጋፍ ሰልፍ ከአ.አ እስከ ክልል ከተሞች

3 በመስቀል አደባባይ የነበረው የአንድነትና ፍቅር ስሜት!

5 በአደጋው የተጎዱ ሰዎች ምን ይላሉ?





7 ከቦንቡ ጥቃት በስተጀርባ

14 “ሆን ተብሎ የሽብር ሥራ ሲሠራ እንደነበር መገመት ይቻላል”
ስዩም ተሾመ

15 “ሁለት ታጣቂዎች መድረኩ አካባቢ ከጠ/ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ጋር ተጋጭተዋል”
ስንታየሁ ቸኮል



10 በፌርዖን ቤት ያደገው ሙሴ
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

17 “ለውጡን እንደግፍ፤ ዲሞክራሲን እናበረታታ”
*ክንፈ ሚካኤል ደበበን (አበበ ቀስቶ)*

18 መደመር ብቻ ለምን?
ሁሴን ከድር

19 ዐቢይ ሰው!!!
ጋዜጠኛ ሚካኤል ዱኖ

20 ራስ ሳይጠና ጉተና!!!
በፍቃዱ አባይ


21 “ህመም ከሌለ፥ ለውጥ አይኖርም”
ታምራት መርጊያ

23 የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ምን አሉ?

24 ጠ/ሚ ዐቢይ በኔልሰን ማንዴላ የፍቅር እና የዕርቀ-ሰላም መንገድ ላይ...!!
ተረፈ ወርቁ

26 “ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ገናናነቷ እንደምትመለስ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አይኑራችሁ”
*ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ*

28 የፖለቲካ ሰዎች ስለ ሰላማዊ ሰልፉ





# የጠ/ሚ የድጋፍ ሰልፍ ከአ.አ እስከ ክልል ከተሞች



ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. "የመደመር፣ የፍቅር እና የይቅርታ ቀን" በሚል በመላ ሀገሪቱ ባሉ ዋና ዋና ከተሞች ሚሊዮኖች በተገኙበት እጅግ ደማቅ ታሪካዊ የድጋፍ ሰልፍ ተከናውኗል:: ይህን ሰልፍ ካለፉት ዓመታት ለየት የሚያደርገው፤ ሁሉም የሚፈልገውን ሐሳብ፣ መፈክር፣ ዓርማ በነፃነት ያንፀባረቀበት፤ በልዩነት ውስጥ ፍቅር፣ መከባበር የተስተዋለበት፤ ስለአንድነትና ስለፍቅር የተዘመረበት፤ ኢትዮጵያዊነት ከወደቀበት አፈር ልሶ የነገሠበትና ከፍ ያለበት መሆኑ ነው:: ኮከብ አልባው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ በየከተሞቹ አደባባይ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ደምቆ የናኘበት፤ ታሪካዊና የማይረሣ ልዩ ቀን ሆኖ አልፏል::

የሰልፉ ዋና መጠንሰሻ የሆነችው አዲስ አበባ ከአራት ሚሊየን ህዝብ በላይ በተገኘበት የህዝብ ማዕበል ከሌሊት ስድስት ሠዐት ጀምሮ ወደ መስቀል አደባባይ የተመመው የአዲስ አበባና አካባቢዋ ህዝብ ኢትዮጵያዊነትንና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ከፍ ሲያደርግ ውሏል:: በዚህ የህዝብ ማዕበል ውስጥ የኦነግን ጨምሮ የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች በነፃነት ያለምንም የሃሳብ ግጭት ተውለብልቧል፤ ሰልፈኛውም የተሰማውን የግል ሀሳብ ያለገደብ በነፃነት ሲገልፅ ነበር:: "ባንተባበር ሊበሉን ነበር"፤ "ዐቢይ ከጎንህ ነን"፤ "ምን አለ? ዐቢይ ምን አለ? ሀገሬን ለጅብ አልሰጥም አለ"፤ እና የመሳሰሉት መፈክሮች በሚሊዮኖች እጅ ተስተውለዋል::

ረፋድ 3፡15 ሲሆን መድረኩ ላይ የተከሰቱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የምስጋና ንግግር ከማድረጋቸው በፊት ሕዝቡ ስማቸውን እየጠራ በታላቅ አድናቆት ደጋግሞ ያወድሳቸው ነበር::

ንግግራቸውን በሰልፈኛው ጭብጨባና አድናቆት ታጅበው የጨረሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በትህትና ዝቅ እያሉ ለህዝቡ ያላቸውን ልባዊ አክብሮት አሳይተዋል:: ወደተዘጋጀላቸው መቀመጫ አምርተው ከም/ጠ/ሚ አቶ ደመቀ መኮንን አጠገብ እንደተቀመጡ ብዙም ሳይቆይ ነው አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተት የተፈጠረው::

የሀገሪቱ ህዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወዱትን መሪ ደግፈው በነቂስ በወጡበት በዚህ ታሪካዊ ዕለት፤ በተደራጀና በተጠና መልኩ ህዝባዊ መሪውን ዒላማ ያደረገ የቦንብ ጥቃት ተካሂዷል:: እንደ ዕድል ሆኖ በዕለቱ የፍቅርና የይቅርታ መሪው ምንም ጉዳት ሳያስተናግዱ ከቦንብ ፍንዳታው ቢያመልጡም፣ ብዙ ንጹሐን ዜጎች ለሞትና ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል:: ወደህትመት እስከገባንበት ሐሙስ ድረስ፤ ሁለት ሰዎች መሞታቸውንና 156 ደግሞ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የፖሊስ መረጃ ያሳያል::

የሀገሪቱን አንድነትና ሰላም የማይሹ፤ አሁን ያለው የፍቅርና የይቅርታ መንገድ የማይመቻቸው አባልተው ሊበሉን ቀን ከሌት ለጥፋትና ለእልቂት የሚሠሩ አካላት፤ ያሰቡት አልተሳካም እንጂ የመስቀል አደባባዩ ዕቅዳቸው በሀገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ የእርስ በእርስ ፍጅት መፍጠር ነበር::

ከአደጋው የተረፉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከቤተ መንግሥት በሰጡት መግለጫ፤ የደረሰው ጥቃት የኢትዮጵያን አንድነትና የመደመር ጉዞ ለማጨለም በሚንቀሳቀሱ ኃይሎች የተፈጸመ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ቀን ደስታችንንና ፍቅራችንን ለማጨለም፤ አንድነታችንን ለማደፍረስ ያሰቡ ኃይሎች እንዳልተሳካላቸውም ተናግረዋል። "ኢትዮጵያ አሁንም ለአንድነት፣ ለፍቅርና ለይቅርታ የዘረጋችው እጇ አይታጠፍም፤ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የሚዘንበው ፍቅርና ሰላምም አይቀየርም" ሲሉም ተደምጠዋል:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ በዚሁ ዕለት ምሽት ተጎጅዎችን በየሆስፒታሉ ተዘዋውረው በመጎብኘት አፅናንተዋል፤ አበረታተዋል::

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀኔራል ዘይኑ ጀማል በምርመራ ሂደቱ ከፌደራል፣ ከአዲስ አበባና ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እንዲሁም ከፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የተውጣጡና በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እየተሳተፉ መሆኑን አስረድተዋል። በምርመራው የአሜሪካ ብሔራዊ የምርመራ ቢሮ (ኤፍ.ቢ.አይ.) ባለሙያዎችም የምርመራ ሥራ መጀመራቸውን ተናግረዋል።

የአዲስ አበባው ትዕይንተ ህዝብ በተካሄደበት ተመሳሳይ ዕለት፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞችም ደማቅ የድጋፍ ሠልፎች ተካሂደዋል::

በአማራ ክልል፣ በደቡብ ወሎ ዞን የሚገኙ የተለያዩ ከተሞች፤ በጠ/ሚኒስትሩ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ለመገኘት በወጡ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ደምቀው ታይተዋል:: በዕለቱ በተለይም የደሴ ከተማ ነዋሪዎች ከተማዋን የዐቢይ ከተማ አድርገዋት ውለዋል:: በደሴ በተካሄደው ትዕይንተ ሕዝብ፤ የጠ/ሚ ዐቢይን፣ የአቶ ደመቀን፣ የአቶ ለማንና፣ የአቶ ገዱን ፎቶ የያዙ ቲሸርቶችን የለበሱ ነዋሪዎች ከተማዋን አጥለቅልቀዋት ውለዋል:: የከተማዋ ዋና አደባባይ በሆነው በ"ፒያሳ" እና በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ላይ የደሴ ህዝብ ባለ ኮኮቡን ሰንደቅ አውርዶ፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩን ሰንደቅ ዓላማ በመዘመር ታጅቦ በይፋ ሰቅሏል:: በኮምቦልቻም ተመሳሳይ ድርጊት የተፈፀመ ሲሆን፤ "ግንቦት 20 ት/ቤት" በሚል ስያሜ የሚጠራውን ባለብረት ፖስተር፣ ሰልፈኞች ነቃቅለው ወደ ቦርከና ወንዝ ሲጥሉ ታይተዋል:: በኮምቦልቻና በደሴ ከተሞች "ቢመችሽም ባይመችሽም፣ ወያኔ አንለቅሽም"፤ "ለውጡን ለመቀልበስ የሚጥሩ ኃይሎችን እናወግዛለን"፤ "ህወሓት የቀን ጅብ ናት"፤ "ዐቢያችን የአንድነት ምልክታችን" … የሚሉ መፈክሮች በስፋት ተሰምተዋል::

*"የቀና መሰለኝ የሀበሻ "ገዱ"፣*
*ያ ደብዛዛ መስመር "ደመቀ" መንገዱ፤*
*ኢትዮጵያ ናት ዛሬ "ዐቢይ" ቁም ነገሩ፣*
*ቃርሚያ ማን ሊከጅል ከ "ለማ" ሀገሩ"፤*


የሚል ሰምና ወርቅ አዘል ግጥም የያዘ ባነርም የሰልፉ ማድመቂያ ነበር::

በምሥራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ፣ በደብረ ማርቆስም ወደ ተክለ ሃይማኖት አደባባይ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ የቀን ጅቦችን በማውገዝ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሲደግፍ ነበር:: በታሪካዊነቷና በቀደምት የሥልጣኔ መናገሻነቷ በምትታወቀው ጎንደር ከተማም፣ በጭቆና ትግሉ በተሠዉ ጀግኖች ሠማዕታትና አሁን ባሉት የለውጥ መሪዎች ፎቶ ተጥለቅልቃለች:: "ለማ መገርሳ የኢትዮጵያ አንበሳ"፤ "ነፍስ ዜግነት የላትም"፤ "ዘመኑ የአናብስቱ ነው"፤ "የቀን ጅቦች ወደ ጫካችሁ ግቡ"፤ "እውነተኛው ሲኖዶስ ወደ ቦታው ይመለስ"፤ "Game over TPLF" እና የመሳሰሉት መፈክሮች የተደመጡ ሲሆን፣ በም በወረታ ከተማም ተመሳሳይ ሰልፍ ተካሂዶአል:: በሱማሌ ክልል ዋና ከተማ፣ በጅግጅጋም ደማቅ የድጋፍ ሰልፍ አካሂደዋል::

ሰሞኑን የክልሉን አመራር በመቃወም በዓመጽ ስትናጥ የሰነበተችው የአፋር ክልልም በአይበገሬ ሀገር ወዳድ ህዝቦቿ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን በመደገፍ በደማቅ ሰልፍ ላይ ነበረች:: የአፋር ወጣቶች ካሰሟቸው መፈክሮች መካከልም "እውነትን ይዞ በሀገር ወዳድነት ስሜት እንጂ፣ በአበል ሰልፍና ስብሰባ ቀረ" የሚለው ይገኝበታል::

ወትሮም የፍቅርና የመተሳሰብ መገለጫ የሆነችው ድሬም በፍቅር ደምቃ ሰንበታለች:: በሰልፉ ላይ በፍቅር ከተማዋ ድሬ፣ የኢትዮጵያ ባለኮኮቡና ልሙጡ ሰንደቅ፤ የኦነግ፣ የኦህዴድና የኢሶህዴፓ ዓርማዎች በጋራ ተደምረው ውለዋል::

ሰኔ 20 ቀን 2010 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የትውልድ ቦታ ጅማም በአነስተኛ የጉብኝት አውሮፕላን በተበተነ በራሪ ጽሑፍ በመታገዝ፤ በመቶ ሺዎች የድጋፍ ሰልፍ ደምቃ ውላለች:: በማግስቱም ወልቂጤ ከተማ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ደምቃ "ዘርማ + ቄሮ + ፋኖ = ኢትዮጵያ.." እና ሌሎች መፈክሮችን አሰምታለች:: የጅማና አካባቢው ህዝብ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ለማግኘት በከፍተኛ ናፍቆት ሲጠብቅ የነበረ ቢሆንም፣ በፀጥታና በደህንነት ችግር ምክንያት ወደ ስፍራው አላቀኑም:: ይኼው የመደመር የድጋፍ ሰልፍ ዛሬ ቅዳሜ ሰኔ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ቀጥሎ በባህር ዳርና በወልድያ ከተሞች በድምቀት እየተካሄደ ይገኛል::



# በመስቀል አደባባይ የነበረው የአንድነትና ፍቅር ስሜት !

## - በአካባቢው “ቀበሌዎች” ቅዳሜ ህዝቡን ስብሰባ ጠርተው ነበር፤


ባለፉት 27 ዓመታት ህዝብን ያለፍላጎቱና ያለ ይሁንታው በአፈሙዝ እንደፈለገ እየረገጠ፣ በጎጥ ከፋፍሎ እርስ በርስ በማጋጨት፣ የሥልጣን ዕድሜውን አርዝሞ የቆየው ህወሓት/ኢህአዴግ፣ የአንድነት ስሜትን ከሕዝብ ውስጥ ለማስወገድ ቀን ከሌሊት የተለያዩ ህዝብን የማጋጨትና የመከፋፈል ድርጊቶችን በስፋት አከናውኗል፡፡

መለስና ጓደኞቹ የተሻለ ሐሳብ ይዞ የመጣውን ተፎካካሪ በመልካም ጎኑ ከማየት ይልቅ፣ “የጥፋት መልዕክተኛ፣ ሽብርተኛ ነው” በማለት ለዓመታት ሲያስሩ፣ ከሀገር ሲያባርሩ ቆይተዋል፡፡ ዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን እንዳጡና የሥርዓቱ ግፍ ከመጠን በላይ እንደተትረፈረፈ፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱም በጥቂት ሰዎች እጅ እንደወደቀ በድፍረት ከመጻፍና ከመናገር በዘለለ፣ የህወሓት/ኢህአዴግን ስውር ደባ ያጋለጡ ጋዜጠኞችና ጦማርያን ያለ ርህራሄ ተገርፈዋል፣ “ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለመናድ የሚጥሩ ሽብርተኞች” በሚል ተለጣፊ ስምም በተደጋጋሚ ለእስር ተዳርገዋል፡፡

ይህን መሰሉ አምባገነናዊ ሥርዓት እንዲቀየርና እንዲሻሻል፣ የተለያዩ ወገኖች ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ከፍተኛ የሕዝብ አመጽ በማቀጣጠል የጀመሩት የለውጥ ንቅናቄ፣ ከሁለት ወራት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን የመሰለ ሀገር ወዳድ መሪ እንድናገኝ አድርጎናል፡፡ እኚህ ሰው ዜጎችን ሲያስር፣ ሲገድል፣ ዘራቸውን ሲያመክንና ሲገርፍ፣ ሲበድል፣ በጨለማ ቤት ሲያጉር ከነበረው ኢህአዴግ መካከል መውጣታቸው ደግሞ ፈፅሞ የማይታመን እውነታ ሆኗል፡፡ “ፍትሕ እንፈልጋለን፣ ሥርዓቱ አንገሽግሾናል” በማለት ዜጎች አደባባይ ከመውጣታቸው ባለፈ፣ የማያባራ መሥዋዕትነት በመክፈላቸው በለማ መገርሳ እና በገዱ አንዳርጋቸው የሚመራው ቡድን ከህወሓት/ኢህአዴግ ቡድን ተነጥሎ እንዲወጣና ከሕዝብ ጎን እንዲቆም አድርጎታል፡፡

ህዝብን ሲያንገላታ የከረመው ኢህአዴግ በዚህ በጠ/ሚኒስትሩ አመራር ወደ ለውጥ ጎዳና ሲገሰግስ መታየቱ ሊደገፍ የሚገባው ነበርና፣ ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ኢትዮጵያውያን በፍቅርና በነፃነት አንድ ሆነው የዘመሩባት ዕለት ሆናለች፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ የማይመቻቸው፣ ዜጋቸውን እያሰቃዩና እየገደሉ መኖር የሚፈልጉ ወገኖችና ተላላኪዎቻቸው ደግሞ በሌላ አቅጣጫ በዕለቱ የጥፋት ተግባር ፈፅመዋል፡፡

አዲስ አበባ እስከ ዛሬ ድረስ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለመሪያቸው ፍቅር በሚሰጡ ዜጎች ከውድቅት ሌሊት ጀምሮ ደማምቃ አረፋፍዳለች፡፡ ኢህአዴግ ግንቦት 20ን እና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ በሚጠራቸው ሰልፎች ላይ በ50 ብር አበልና በማይረባ ጥቅማ ጥቅም፣ አረጋውያንን ከየመንደሩ ሰብስቦ በማስወጣት ድጋፍ ያለው ለመምሰል ዕድሜውን ሙሉ ያደረገው ጥረት፣ ቅዳሜ ዕለት ድርጅቱ



ቀን 14/10/2010


የስብሰባ ጥሪ

ለ [redacted]

እርስዎ በወረዳችን ቀጠና 5ሀ ነዋሪ መሆንዎት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በአካባቢ ልማት ኮብል ስቶን ሥራ እና በመንግስት ወቅታዊ አጀንዳዎች ማለትም በኢትዮ-ኤርትራና በልማት ድርጅቶች ውሳኔ ዙሪያ ውይይት ስለሚደረግ ቅዳሜ ሰኔ 16/2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 [illegible] በሚገኘው የወጣት ማዕከል አዳራሽ እንዲገኙልን ስንል በአክብሮት ጠርተነዎታል፡፡

ማሳሰቢያ፡- አከራይ ቤት ውስጥ ያሉ ተከራዮችን ይዞ መምጣት አለበት፡፡

- ከስብሰባው መጀመር በፊት ከጠዋቱ 12፡00 (12 ሰዓት) ሁሉም ነዋሪ [illegible] ግቢና በር ዙሪያ [illegible] ካለ [illegible] የተመረጠ ሥራ ይሆናል፡፡



ቀን14/10/2010 ዓ.ም

ለ----

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ለውይይት መጠራትዎን ስለማሳወቅ ይመለከታል

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሆኖ የወረዳ 01 ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት በደንብ ቁጥር 54/2005 በተቀመጠው መሰረት ከመንገድ ደህንነት ጋር በተያያዘ ሊያወያይዎ ስለፈለገ በቀን 16/10/2010 ዓ.ም በወረዳው ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ከጠዋቱ 2፡30 ሰአት ተገኝተው የውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናሳስባለን፡፡

የወረዳ 01 ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት

ምን ያህል ከወጣቱና ከቀሪው ህብረተሰብ ጋር ተራርቆ እንደኖረ በገሀድ አረጋግጧል፡፡

ያለመንግሥት ጥሪ፣ ያለ ፓርቲዎች ቅስቀሳ፣ አበልና ትራንስፖርት ሳይቀርብለት ከአራት ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ፣ ከ27 ዓመት በኋላ ባገኘው እውነተኛ መሪ ተደስቶ፣ ያለ ቀስቃሽ አደባባይ ወጥቷል፡፡ በዕለቱ ህብረተሰቡ ያደርግ የነበረውን የድጋፍ ሰልፍ በተመለከተ በተለያዩ ስፍራዎች ከተንቀሳቀሱት የግዮን መጽሔት ባልደረቦች መካከል ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የተካሄደውን ህዝባዊ ንቅናቄ በቦታው የታደመው ባልደረባችን የሰልፉን አንድምታ እንደሚከተለው ያስቃኘናል፡፡

ከበርካታ ስመ ጥር የኪነ ጥበብ ባለሙያዎቿ ባሻገር ፈረንሳይ የምርጥ የነፃነት ታጋዮች መፍለቂያ ምድር ናት፡፡ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በነፃው ፕሬስ ዘርፍ ከፍተኛ መሥዋዕትነት የከፈለውና “አሸባሪ” ተብሎ ስድስት ዓመት ከሰባት ወር የታሰረው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የፈረንሳይ ልጅ ነው፡፡ በ1997 ዓ.ም. ልዩ ንቅናቄ የፈጠረው የ“ቅንጅት” አባል ሆና ብቅ ያለችውና ወጣት ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ እንዲበዙ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተችው ብርቱካን ሚደቅሳ፣ የዚሁ ሰፈር ዓርማና መለያ ነች፡፡

የኢህአዴግ አምባገነን አገዛዝ ሲወገዝ ሁሌም ከፊት በመሰለፍ የሚታወቀው የፈረንሳይ ሕዝብ፣ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ለመደገፍና ሥርዓቱ ለውጥ እንዳያመጣ በተቃራኒ አቅጣጫ የተሰለፉትን ኃይሎች ለማውገዝ ቅዳሜ ከሌሊቱ 11፡30 ጀምሮ ነው በፈረንሳይ ለጋሲዮን - ኬላ አደባባይ ላይ የተሰባሰበው፡፡


በዕለቱ መሪውን ለማመስገን የወጣው የፈረንሳይ ለጋሲዮን ህዝብ፣ ፍፁም አስገራሚ በሆነ መልኩ ንፁሑን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለም ያለበትንና የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ በአደባባይ ይዞ ወጥቷል፡፡ “ኮከቡ” የሥርዓቱ ምልክት መሆኑን ከመግለጽ ባሻገር ኢትዮጵያዊነት ከምንም በላይ እንደሚቀድም በዝማሬ አረጋግጧል፡፡ ሰልፈኞቹ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ባሻገር በዚህች ሀገር ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረከቱትን የአቶ ለማ፣ ገዱ፣ ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ታማኝ በየነ፣ እስክንድር ነጋና አንዱዓለም አራጌ፣ ተመስገን ደሳለኝንና ደቡብ አፍሪካ የተገደለውን ነብሮን የመሳሰሉ የነፃነት ታጋዮችን ፎቶ የያዘ ግዙፍ ባነር በመያዝ “ጀግኖቹን” ከአድናቆት ጋር በአደባባይ አመስግኗል፡፡

የፈረንሳይ ለጋሲዮን ነዋሪዎች ልዩና ማራኪ በሆነ ብዛት ባለው የሕዝብ ሰልፍ እየታገዙ ከ6 ኪሎ፣ ከጃንሜዳ፣ ከመነንና ከሽሮ ሜዳ የመጡ ወጣቶችን በማሰባሰብ፣ ሀገራዊ ሕብረ ዜማዎችን እያዜሙና መፈክር እያሰሙ መስቀል አደባባይ ሲደርሱ በቦታው የነበረው ሕዝብ ከዳር ዳር በጭብጨባና በአድናቆት ተቀብሏቸዋል፡፡ የፈረንሳይ ልጆች በመስቀል አደባባይ ህብረተሰቡን በጭፈራ ሲያነቃቁና ህዝቡ በአንድነት መንፈስ የሚፈልገውን ነገር በነፃነት እንዲያስተጋባ ሲያነሣሡም አርፍደዋል፡፡

በአንፃሩ በፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የቀበሌ አመራሮች፣ የአካባቢው ኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ (ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ) አባላትና ከሦስት ወር በፊት የነበረው ኢህአዴግ አጎብዳጆች፣ ሰልፉ እንዲስተጓጎል አሳፋሪ ሥራ ለመሥራት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ በአጎብዳጅነትና “እከሌ ኢህአዴግን ይቃወማል” በማለት የአካባቢውን ነዋሪዎች ሲያስሩና ሲያስፈራሩ የነበሩ አንዳንድ የኮሚዩኒቲ ፖሊስ አባላትና የቀበሌ አቸፍቻፊዎቻቸው፣ አደገኛ ቦዘኔነቱንና አሸባሪነቱን ባረጋገጠው የህወሓት/ኢህአዴግ ሰዎች ድጋፍ የቀበሌ ቤት እንደተሰጣቸው የገለጹት የአካባቢው ነዋሪዎች፣ እነዚህ ሰዎች በመላው አዲስ አበባ የተላለፈውን ትዕዛዝ ጥሰው፣ ህዝቡ በዕለቱ ሰልፍ እንዳይወጣ “ስለ ልማት፣ ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ ጉዳይ እንነጋገር” በሚል የስብሰባ መጥሪያ ወረቀት ቤት ለቤት በትነዋል፡፡ የየካ ክ/ከተማ የወረዳ 1 የደንብ ማስከበር ሐላፊም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በዕለቱ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፡፡

ለሆዳቸው ያደሩትና ጠ/ሚኒስትሩን ጠልፎ ለመጣል፣ በአደባባይ እኩይ ተግባር የፈፀመው ቡድን ተላላኪ የሆኑት የየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 መስተዳድር ሠራተኞችና የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ አባላት ሐሳባቸው ባይሳካም በመጥሪያ ወረቀታቸው ላይ ነዋሪዎች በግቢያቸው ያለውን ተከራይ ጭምር ይዘው እንዲመጡ አሳስበው ነበር፡፡ እንደነዚህ ያሉ ያልተለወጡና ለጥፋት ያኮበኮቡ አሳፋሪ ሰዎችን ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከውስጡ በማጥራት የለውጥ ጉዞውን ማጠናከር ይገባዋል፡፡

በተጨማሪም፣ መላዋ አዲስ አበባ ቅዳሜ፣ በድጋፍ ሰልፉ ስትናጥ ውላለች፡፡ ከአውቶብስ ተራና መሳለሚያ አካባቢ ወደመስቀል አደባባይ የተመሙ ወጣቶች፣ ኮከብ አልባውን ሰንደቅ ዓላማ ለብሰው በመታየት የሰልፉ ድምቀት ሆነዋል፡፡ ከመገናኛ አካባቢ የተነሡ ወጣቶችም መስቀል አደባባይን ያደመቁ ክስተቶች ነበሩ፡፡ የጌጃ ሰፈሮች፣ የአዲሱ ገበያ ወጣቶችን ጨምሮ መላ ወደመስቀል አደባባይ በሚያስገቡት ሁሉም መስመሮች የገቡት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የሰልፉ ድምቀት ሆነው ውለዋል፡፡





ርዕሰ አንቀጽ

# ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር ወደ ፊት!!!

ቅዳሜ ሰኔ 16 /2010 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለሀገር መሪ ተለግሷል:: ሕዝብ አንድነቱን፣ ኢትዮጵያዊነቱን፣ ክብሩንና ሞገሱን የሚቸረው አስተዳዳሪ ካገኘ ለማመስገን ወደኋላ እንደማይል በዚህ ቀን አረጋግጧል::

ወያኔ/ኢህአዴግ 27 ዓመት ይህንን ሕዝብ ሲያስተዳድር ሀገሪቷን በመምራት የቆዩት ሁለቱም ጠ/ሚኒስትሮች እንዲህ አይነቱን ክብር ለማግኘት አልታደሉም:: በሽግግር መንግሥት ጊዜ ፕሬዝዳንት በኋላም ጠ/ሚኒስትር በመሆን ከሃያ ዓመት በላይ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ያለፉት አቶ መለስ ዜናዊ አንድም ጊዜ በዚህ መልክ ሕዝብ ፍቅር ሰጥቷቸው አያውቅም::

በእርሳቸው የሥልጣን ዘመን ኢትዮጵያዊነት ተረስቶ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገንነት በግልጽ የተንፀባረቀበት ወቅት በመሆኑ፤ በ50 ብር አበል ክፍያ ከየመንደሩ የሚሰበሰቡ ዕድሜ ጠገብ አሮጊቶችና በአቃጣሪነት የሚታወቁ ጥቂት ወጣቶች ይዘው ከመውጣት ውጭ ሕዝብ በየትኛውም አጋጣሚ ሲደግፋቸውና ሲያመሰግናቸው ለማየት አልታደሉም::

በቅርቡ "የለውጡ አባል ነኝ" በማለት በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን የለቀቁት አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ገና ሥልጣን ላይ በወጡበት ዕለት የመለስን ራዕይ አስፈፅማለሁ ብለው ቆርጠው በመነሣታቸው ሃያ ዓመት የዘለቀው የተሳሳተ ራዕይ እሳቸውንም ገደል ይዟቸው ገብቷል:: በአቶ ኃ/ማርያም የመጨረሻዎቹ ሁለትና ሦስት ዓመታት በመላ ሀገሪቱ ከፍተኛ የሕዝብ ንቅናቄ ነበር:: በጌታቸው አሰፋ የሚመራው የህወሓት የደህንነት ቡድን፣ ከኦሮሚያና ከአማራ የተለያዩ ክፍሎች ዜጎችን አፍኖ እያመጣ በጅምላ ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ሲፈጸምና በሽብርተኛነት ስም ዘብጥያ ሲወረውር፣ የደህዴን ፍሬ አቶ ኃ/ማርያም የዳር ተመልካችና ተባባሪ ከመሆን የዘለለ ነገር አልሠሩም::

ህወሓት/ኢህአዴግ በማን አለብኝነት ሀገሪቷን ለዓመታት መመዝበሩ ዜጎችን (በተለይም የአማራና የኦሮሞ ተወላጆችን) በጭቆና በትር ያለርህራሄ መቀጥቀጡ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱን ወደ አንድ ብሔር ተወላጆች ማዘንበሉና በአጠቃላይ ፍቅርና ዴሞክራሲ መጥፋቱን ተከትሎ የመጣውን የሕዝብ ጥያቄ በማድመጥ ብቅ ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ግን ለሃያ ሠባት ዓመት የራቀንን ኢትዮጵያዊነት መልሰውልናል:: ከምንም በላይ ሀገርና ሕዝብ እንደሚቀድም በተግባር አሳይተውናል::

ጥቅማቸው የቀረና የኋላ ታሪካቸው በሕዝብ ደምና ወንጀል የጨቀዩ ወገኖች ግን በተቃራኒ መስመር በመሰለፍ የአዲሱን ጠ/ሚኒስትር አካሄድ ለማበላሸትና በሚፈጠረው ግርግር ዳግም ወደ ቀደመ ስፍራቸው ለመመለስ ተደጋጋሚ ጥረት አድርገዋል:: እነዚህ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ዘረኝነትን ያስቀደሙ አካሎች በየአካባቢው ከመዶለትና ግጭቶችን ከመፍጠር በዘለለ ቅዳሜ ዕለት በመስቀል አደባባይ አስነዋሪ ተግባር ፈጽመዋል:: ድርጊቱ በሌሎች አባላት የተፈጸመ ቢሆንም፣ ላኪዎች ወይም አስፈፃሚዎች እነዚህ ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አለ::

ኢትዮጵያችንን ሲያምሷት፣ ሲያሸብሯትና ሲዘርፏት የኖሩት አካላት ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ በዘለቀ የሥልጣን ዘመናቸው ያልሰበኩትን ኢትዮጵያዊነት ከዳር ዳር ያስተጋቡት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ጥላቻን አስወግደን በፍቅርና በይቅርታ መንገድ እንጓዝ ማለታቸው በመለስ ራዕይ ተጠልፎ ከመውደቅ ይልቅ በመደመር ቅኝት መምጣታቸው ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታና ፍቅርን ቸሯቸዋል::

ያለመንግሥት ግፊት፣ ያለተፎካካሪ ፓርቲዎች ጥሪ በግለሰቦች አስተባባሪነት የተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ልዩ ነበር ማለት ይቻላል:: ሕዝብ ለመሪው ፍቅሩን ሲገልጽ በታሪክ የመጀመሪያ የሆነው ይህ ታሪካዊ ሰልፍ ብዙ ነገር አሳይቶን አልፏል:: በዕለቱ በአሸባሪዎች በተፈፀመ የቦንብ ጥቃት ወጣቶች መሪያቸውን ለአደጋ ላለማጋለጥ ራሳቸውን ለመሥዋዕትነት አቅርበዋል:: አጓጊና ፈታኝ የሆነውን የእድሜ ዘመናቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ፣ የራሳቸውንም ፍላጎት ሳያስቀድሙ ንፁሐን ዜጎች ከቦምብ ጣዮች ጋር አብረው በመውደቅ የለውጥ መሪያቸውን ታድገዋል::

ከቀናት በፊት በፓርላማ ላይ ሲያሸብር፣ ዜጎችን ሲያስር፣ ሲገርፍና ጨለማ ቤት ሲመረምር የነበረው ሥርዓቱ እንደሆነ በአደባባይ የመሰከሩት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፤ ይህ ነገር ዳግም በራሳቸውና በሕዝብ ላይ በይፋ ሲፈፀም ተመልክተዋል:: እንዲህ አይነቱን አስነዋሪና የዘቀጠ ተግባር የፈፀሙት ግለሰቦች በሕግ ቁጥጥር ላይ የሚገኙ ቢሆንም፣ ከሰዎቹ ጀርባ ያሉ አካላትና አመራር ሰጪዎች በፍጥነት ሊያዙና በሕግ ተገቢው ቅጣት ሊሰጣቸው እንደሚገባ እያሳሰብን፤ እኛ ግን አሁንም በተጠናከረ መልኩ ለመሪያችን ፍቅር ከመስጠት ባሻገር ከጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ጋር ወደ ፊት!!! ብለናል::

በመጨረሻም የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍል ሕዝብ ያለጉቦና አበል በራሱ መልካም ፍቃድ አደባባይ ወጥቶ ያመሰገናቸውን ጠ/ሚኒስትራችንና ሰልፉን የተመለከተ ይህንን ልዩ ዕትም ስናበረክት ለሕዝባችንና ለመሪያችን ያለንን አክብሮት ለመግለጽ ነው።


ግዮን መጽሔት

ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በየ 15 ቀኑ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል
zealias.w@gmail.com

**ዋና አዘጋጅ**
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

**አዘጋጆች**
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

**አምደኞች**
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
enqu2013@ gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤
አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10
የቤ.ቁ. 066/ሀ



# በአደጋው የተጎዱ ሰዎች ምን አሉ?

ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ በተጠራው ህዝባዊ የድጋፍ ሠልፍ ላይ ያልተጠበቀ ድንገተኛ አደጋ ተከስቷል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ላሳዩት የጅምር ለውጥ ምስጋና ለመቸርና ከእርሳቸው በተቃራኒ የቆሙ ወገኖችን ለማውገዝ ሕብረተሰቡ ከተለያየ አቅጣጫ በተሰበሰበበት በዚህ ዕለት የጥፋት ኃይሎች የሽብር ተግባር ፈፅመዋል::

በዕለቱ በቦምብ ጥቃቱ ከተጎዱና አደጋውን ተከትሎ በተፈጠረው ትርምስ ከፍተኛ የሆነ የመረጋገጥ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተገኝተን አነጋግረናል:: ዝግጅት ክፍላችን በህክምና ተቋማቱ በርካታ አሳፋሪና አስነዋሪ ችግሮችን ታዝቧል:: በየካቲት 12 አጠቃላይ ሆስፒታል፤ በዕለቱ ድንገተኛ አደጋው ደርሶባቸው የሄዱ ታካሚዎችን ራጅ ከማንሣትና ቁስላቸውን ከማሽግ ውጪ ፍንጣሪውን ከሰውነታቸው ሳያወጡላቸው ከህክምና ቦታው እንዲወጡ አድርገዋል::

"ፍንጣሪው ይውጣልን፣ ተቃጠልን፤ እባካችሁ እርዱን" እያሉ ተጎጂዎቹ ቢማፀኑም የየካቲት 12 ሆስፒታል ዶክተሮችና የህክምና ባለሙያዎች ግን፤ "ከዚህ ውጭ ምንም ልናደርግላችሁ አንችልም" በማለት፤ በተለይም ከባድ ጉዳት ያጋጠማቸው አካላት ወደመጡበት ክ/ሀገር እንዲመለሱ ተገደዋል:: የሆስፒታሉ የህክምና ሰዎች በዕለቱ ውስጥ ውስጡን በስውር ሲንቀሳቀሱ በነበሩ አንዳንድ የህወሓት ደህንነት ሰዎች ትዕዛዝ ሥር ወድቀዋል የሚሉ የተጎጂ ቤተሰቦችን አስተያየት በስፋት ሰምተናል::

ከአደጋው አድራሽ ኃይሎች ጋር በአቋም የሚዛመዱና እየፈራረሰ ያለው የኢህአዴግ ቅሪት የደህንነት ኃይሎች የግባቸው መጠን አድርገው ያሰቡት የሞት አደጋና የደረሰው ጉዳት አለመመጣጠን በእጅጉ ያበሳጫቸው በመሆኑ፤ ተጎጂዎች በፍጥነት ህክምና እንዳያገኙ ለማድረግ የተንኮል ተግባር ሲፈፅሙ፤ የህክምና ባለሙያዎቹ በተቻለ መጠን ዕርዳታ አድርገው (ከአቅማቸው በላይ ቢሆንም እንኳን) ለቀጣይ ወዬት መሄድ እንዳለባቸው ገልፀው መሸኘት ሲገባቸው የፈፀሙት ድርጊት ግን ህዝብና መንግሥትን በእጅጉ ያሳዘነ ሆኗል::

በራስ ደስታ ሆስፒታልም፤ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ አንዲት እናት በቦምብ ፍንጣሪ እግሮቻቸውን ተመትተው ህክምና ለማግኘት ቢሄዱም በዕለቱ የነበሩ የህክምና ባለሙያዎች "ይህ ተራ ነገር ነው" በማለት የረባ ህክምና ሳይሰጧቸው አሰናብተዋቸዋል:: ግለሰቧ እያለቀሱ "ድሀ ነኝ፤ በላስቲክ ቤት ነው የምኖረው፤ በዚያ ላይ የሙት ልጅ ይዤ ነው የምኖረው፤ ፍንጣሪውን አውጡልኝ" ቢሉም፤ ዶክተሩ ግን "አያገባኝም፤ ከፈለግሽ ክሰሺኝ" ብሏቸዋል:: ሴትየዋን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በአሁኑ ሰዓት ተቀብሎ ቀዶ ጥገና እያደረገላቸው ይገኛል::

በዚህ አጋጣሚ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በቦምብ የተጎዱ ወገኖቻችንን ቀን ከሌት ሲንከባከቡ ለነበሩ ለመላው የጥቁር አንበሳና ዘውዲቱ ሆስፒታል ዶክተሮች፣ የህክምና ባለሙያዎች እንዲሁም የአስተዳደር ክፍል ሠራተኞች ልባዊ ምስጋናችንን በህዝብ ስም እናቀርባለን:: ቸልተኝነት የተስተዋለበት ተግባር በፈፀሙት የህክምና ተቋማት ውስጥ በዕለቱ የነበሩ የህክምና ባለሙያዎች ጉዳይ ግን በመንግሥት በኩል በጥልቀት ሊመረመር ይገባዋል::

በፍንዳታው ጉዳት ካጋጠማቸው ወገኖቻችን በተጨማሪ፤ ወደህትመት እስከገባንበት ሐሙስ 7 ሰዓት ድረስ በአደጋው ሁለት ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል::

ሟቾቹ፣ ከጊምቢና ከወላይታ አካባቢ የመጡ መሆናቸውና አስከሬናቸውም በክብር ወደቤተቦቻቸው መሸኘቱ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ተዘግቧል:: ሆኖም የሟቾቹን ትክክለኛ ማንነት ለማወቅ ሰላማዊ ሰልፉን ወዳዘጋጀው ኮሚቴ አምርተን ነበር::

ይህ ኮሚቴ፣ አባላቱ በሟቾቹ ጉዳይ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ግልፅ የሆነ መረጃ እንዳላገኙና ፖሊስ፣ ወንጀሉን ለማጣራት በምርመራ ላይ በመሆኑ፤ "አሁን ምንም ዓይነት ማረጋገጫ አንሰጣችሁም" መባላቸውን አሳውቀውናል:: ወደፊት ዝግጅት ክፍላችን የሟቾቹን ትክክለኛ ማንነትና ቤተሰቦቻቸው ያላቸውን አስተያየት ይዞ ለመቅረብ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል::

በመስቀል አደባባዩ ሰልፍ በተፈጠረ የቦምብ ጥቃት ክፉኛ ከተጎዱ ወጣቶች መካከል አንዱ የሆነውና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመታከም ላይ የሚገኘው ፋንታዬ ደሳለኝ፤ አደጋው በተከሰተበት ዕለት ቀኝ እግሩ ከቁርጭምጭሚቱ ጀምሮ ተቆርጦ ተገቢው ህክምና ተሰጥቶት ነበር:: በዕለቱ፣ ምሽት ላይ ጠ/ሚስትር ዐቢይ ሲጎበኙት፤ "የተጎዳሁት ለፍቅርና ለአንድነት ነው፤ አይቆጨኝም፤ በሀገሬ ለውጥ ተስፋ አለኝ" በማለት በሚዲያዎች በኩል ጥንካሬውን ያስተጋባው ፋንታዬ ጉዳቱ በድጋሚ ኢንፌክሽን በመፍጠሩ፤ ማክሰኞ ሰኔ 19፣ 2010 ዓ.ም. በድጋሚ ሌላ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት፣ ጉልበቱ አካባቢ እንደተቆረጠ በቦታው ተገኝተን ታዝበናል::

ለተጎጂዎቹ ከፍተኛ ትብብር ላደረጉት ጥቁር አንበሳና ዘውዲቱ ሆስፒታሎች ልባዊ ምስጋና እያቀረብን ከተጎጂዎቹ መካከል የተወሰኑትን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

## "ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጥተው ሲጠይቁኝ ጉዳቴን አውጥቼ ጥዬዋለሁ"

### ሲምኔራ ስዩም



**ግዮን:- ሙሉ ስምሽንና ከየት አካባቢ እንደመጣሽ ብትገልጪልን?**

**ሲምኔራ**:- ሲምኔራ ስዩም እባለለሁ፤ ከቡራዩ፣ ከታ ነው የመጣሁት::

**ግዮን:- አደጋው በደረሰበት ጊዜ የት ቦታ ላይ ነበርሽ?**

**ሲምኔራ**:- አደጋው በደረሰበት ሰዓት ከመድረኩ በስተቀኝ ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ ነው የነበርኩት፤ ቦምቡ የፈነዳው ወደ 3:40 አካባቢ ነው:: መጀመሪያ ላይ ቦምብ አልመሰለኝም፤ ርችት ነበር የሚመስለው፤ ድምፁ እንደቦምቡ የተጋነነ አልነበረም:: ከኋላዬ ያሉት ሰዎች ስላወቁ እነሱ ሲሮጡ፣ እኔ ስላላወቅሁ አልሮጥሁም:: መጀመሪያ ላይ ጠባቂዎቹ በጣም ስለተቸገሩ ሁለት ብረት አድርገው ህዝቡን ወደፊት እንዳይጠጋ ሲገድቡ ነበር::

እዚያ ሁለት ብረት መካከል እግሬ ገባ፤ በዚያ ሰዓት ግፊያው በማየሉ ሰዎች ሲሮጡና ሲጋፉ ከነብረቱ ከሥር ወድቄ ረጋግጠውኛል:: በተለይ ብረቱን ሲረግጡት እግሬ ከውስጡ ያለ በመሆኑ ኃይለኛ ቅጥቅጥ ደርሶብኛል:: ግራ እግሬ ነው የተጎዳው::

**ግዮን:- የቦምብ ፍንጣሪው አግኝቶሻል?**





**ሲምኔራ**፡- ቦምቡ አልነካኝም፤ ከእኔ 20 ሜትር ርቀት ላይ ነው የፈነዳው፤ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ቦምቡ አላገኘኝም፡፡

**ግዮን፡- ወደ ሰልፉ ብቻሽን ነበር የመጣሽው?**

**ሲምኔራ**፡- ከአክስቴና ከጓደኛዬ ጋር ነው ወደሰልፉ የመጣነው፤ እነሱም መሬት ላይ ወድቀው ነበር፤ ሰዎች ሲገፋፉን ነው የተለያየነው፡፡ እነሱ ግርግሩ ሲፈጠር ከኋላዬ ነበሩ? ከወደቅሁኝ በኋላ ያነሱኝና ከብረቶቹ መካከል ያወጡኝ ሁለት ፌዴራሎች ናቸው፡፡ አንድ ከኋላዬ የነበረ ልጅ ያለሁበትን ሁኔታ በንቃት ሲከታተል ስለነበር እርሱ ነግሯቸው ነው በፍጥነት ብረቱን ያነሡልኝ፡፡

**ግዮን፡- አደጋው እንደደረሰብሽ ተገቢውን ህክምና በፍጥነት አግኝተሻል?**

**ሲምኔራ**፡- አዎ! በዚህ አጋጣሚ እዚህ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚሠሩትን በሙሉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በተለየ ሁኔታ ኪሩቤል የሚባል የተማሪዎች ካፌ ውስጥ የሚሠራ ልጅ፤ ፋርሃን ከሚባል ልጅ ጋር ተሸክመውኝ ለኤክስሬይ ላይ ታች ሲሯሯጡ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ይባርካቸው፤ እኔ ምንም ላደርግላቸው አልችልም፡፡

በሰዓቱ ‘የእኔ እብጠት ብቻ ስለሆነና ስላልደማ የከፋ ጉዳት የለውም’ ብዬ ለዶክተሮቹ የእኔን ተውትና ሌሎችን አስቀድሙ ስል ነበር፤ በኋላ ግን እግሬ ክፉኛ በመጎዳቱ የግድ ቀዶ ጥገና ማድረግ እንዳለብኝ ተነግሮኝ በጥሩ ሁኔታ ሰርጀሪ ሠርተውኛል፡፡ ዶ/ር ብሩክን ጨምሮ ሁሉንም የህክምና ሰዎች ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

**ግዮን፡- ወደ ሰልፉ ለመምጣት መነሻሽ ምን ነበር?**

**ሲምኔራ**፡- ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ላመሰግነውና በዚያውም ልደግፈው ስለፈለግሁኝ ነው የመጣሁት፡፡ አደጋው ከመፈጠሩ በፊት ሰልፉ ደስ ይል ነበር፤ ሰዎችን ስጠይቅ ሰልፉ እስከ ሰባት ሰዓት ነው ሲሉኝ ምናለ ከዚያ ባለፈና ቀኑን ሙሉ እንዲህ በፍቅር ብናሳልፍ ብዬ ተመኝቼ ነበር፡፡

**ግዮን፡- አደጋው ከደረሰ በኋላ በዚያው ምሽት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ተጎጂዎችን በሆስፒታል ጎብኝተዋል፤ ስታገኛቸው ምን ተሰማሽ?**

**ሲምኔራ**፡- በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ፎቶ ላይ ካያችሁ በጣም ስስቅ ነበር፤ እሳቸውን ሳገኝ ህመሜን ሁሉ ረስቼ ደስተኛ ነው የሆንኩት፡፡ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን በመተዋወቄና በማግኘቴ ልዩ ደስታ ነው የሚሰማኝ፡፡ ማንም ሠው ያላጋጠመውን ዕድል ነው ያገኘሁት፤ ሁሉ ነገሬን አስረስተውኛል፡፡ ጉዳቴን፣ ህመሜን ከውስጤ አውጥቼ ጥየዋለሁ፤ የእሳቸው መጠየቅ ለእኛ ትልቅ ብርታት ነው፡፡

**ግዮን፡- ሰላማዊ ሰልፉን ላዘጋጀው ኮሚቴም ሆነ ለመንግሥት በዚህ አጋጣሚ የምታስተላልፊው መልእክት ምንድን ነው?....ምን እንዲደረግልሽ ትፈልጊያለሽ?**

**ሲምኔራ**፡- መጥተው መጠየቃቸው ብቻ ለእኔ በቂ ነው፡፡ እዚህ ድረስ ወዲያውኑ መጥታችሁ መጠየቃችሁ በራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ሰውን እንዲህ አድርጉልኝ ማለት አይቻልም፤ ደስ ያላችሁን የፈቃዳችሁን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

የደረሰብኝ አደጋ ስብራት ነው፡፡ ሰርጀሪ ሠርተው ብረት አስገብተውልኛል፡፡ እግሬ በጣም አብጦ ስለነበር በካሜራ በመታገዝ በውጭ በኩል ነው ብረት ያስገቡልኝ፡፡ እስከ ስድስት ሳምንት ብረቱ ይቆያል፤ የሚወጣው ከዚያ በኋላ ሲሆን፣ እሱ እንደወጣ ጀሶ ለሁለት ሳምንት እናስርልሻለን ብለውኛል፡፡ .መሬት እንዳትረግጪ ተብያለሁ፤ ለመንቀሳቀስም ሰው ነው የሚረዳኝ፡፡

**ግዮን፡- ገና በለጋ ዕድሜሽ ወደዚህ ሰላማዊ ትግል ገብተሻልና ለዕድሜ አቻዎችሽ የምታስተላልፊው መልዕክት ምንድን ነው?**

**ሲምኔራ**፡- እንዲሁ እንዲሰበሩ፣ እንዲጎዱ ሳይሆን፤ እኔ ውስጥ ያለውንና ወደ ሰልፉ ያስወጣኝን እውነተኛ የሀገር ስሜት እንዲያገኙ ነው የምነግራቸው፡፡ ኢትዮጵያ የፍቅር ሀገር ናት፤ ከኩራቷ በላይ ምን አለ? ብሔር፣ ሃይማኖት ሳንለይ በፍቅር በአንድነት መኖር አለብን፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ወጣቶች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ኢትዮጵያውያን ከማንም የምንበልጥ ነን፤ እግዚአብሔር በእኛ መካከል አለ ነው የምላቸው፡፡

**ግዮን፡- እናመሠግናለን፡፡**

## የራስ ደስታ ዶ/ር “የቦንብ ፍንጣሪው ውጭ ብትሄጂ እንኳ አይወጣም” ብሎኝ ነበር
## አዳነች ዎብሎ



**ግዮን፡- እስኪ ራስዎን ያስተዋውቁን? የት አካባቢ ነው የሚኖሩት?**

**አዳነች**፡- አዳነች ዎብሎ እባላለሁ፤ አዲስ አበባ ሠንጋ ተራ አካባቢ ነው የምኖረው፤

**ግዮን፡- የደረሰብዎት አደጋ ምንድን ነው?**

**አዳነች**፡- የቦንብ ፍንጣሪ ነው እግሬን የመታኝ፡፡ በሰዓቱ አደጋው ሲደርስብኝ፣ ራሴን ስቼ ገነት ሆቴል አካባቢ የሚገኝ ጤና ጣቢያ ነው የገባሁት፡፡ በድንጋጤ መንገዱ እንዴትና ወዴት እንደሚወስድ እንኳን ማስታወስ አልቻልኩም፤ እየባነንሁ ነው የሄድሁት ጤና ጣቢያው ግቢ ሳልደርስ ጫፍ ላይ ወደቅሁ፡፡

ወጣቶች በአካባቢው ሲሯሯጡ “እባካችሁ ልበላሽ ነው፤ እርዱኝ” ብዬ እጄን ወደ ላይ ሳውለበልብ ወጣቶች “እናታችን የእኛ ደም ይፍሰስ” ብለው አንሥተው ነው ሆስፒታል ያስገቡኝ፡፡ ጤና ጣቢያ ማስታገሻ መርፌ ወግተው ወደ ጥቁር አንበሳ ላኩኝ፤ ወደ ጥቁር አንበሳ በአምቡላንስ መጣሁ፡፡ እዚህ በሰዓቱ በጣም የከፋ ጉዳት ያለባቸው ብዙ ሰዎች ስለነበሩ፣ እርስዎ ወደ ራስ ደስታ ሆስፒታል ይሂዱ፤ ሕይወታቸው አስጊ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ቅድሚያ እንስጥ አሉ፡፡ እኔም እሺ ብዬ ወደ ራስ ደስታ ሄድሁኝ፡፡

ራስ ደስታ ስደርስ ጊዜያዊ ህክምና ከማድረግ ውጪ፤ ራጅ፣ አላነሱኝም፤ የአጥንት ስፔሻሊስት የተባለው ዶ/ር ራሱ በስነ ሥርአት አልመረመረኝም፡፡ “ሰውነቴ ውስጥ ፍንጣሪ ገብቷል፤ ውስጥ ለውስጥ ሥር እንዳይሰድብኝ በቂ ህክምና አሁኑኑ አድርጉልኝ፡፡ ሰው የለኝም በላስቲክ ቤት የምኖር ድሀ ነኝ ተባበረኝ” ስለው፤ “የአንቺ የከፋ አደጋ አይደለም” ብሎ በቸልታ አለፈኝ፡፡

ቅዳሜና እሁድ እንዲሁ ሳለቅስ፣ ስሰቃይ ቤቴ ዋልሁኝ፤ 15 ዓመት ያልሞላው ትንሽ ልጅ ይዤ ያለሁት ከጎዳና በማይሻል የላስቲክ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ያኔ ራስ ደስታ ዶክተሩን ደራሽ ወገን የሌለኝ መሆኔን እየነገርሁት፤ እንባዬን እያየ፤ የልጄን እንባ እያየ፤ ከሁለቱም እግሮቼ ደም እየፈሰሰ ነው ሂጂ ያለኝ፡፡ እንዲያውም በማን አለብኝነት ከፈለግሽ ክሰሺኝ ብሎኛል፡፡

ሰኞ ጠዋት፣ ሁለት ሰዓት፣ በድጋሚ ራስ ደስታ ሆስፒታል ሄጄ በነርሶች አስጠርቼው ሲያናግረኝ፤ “እዚህ ውስጥ ያለውን ፈንጅ እያንዳንዱን ስለቃቅም ሌላ ከባድ ነገር ሊተላላፍብኝ ይችላልና አልለቅምም” አለኝ፡፡ “ታዲያ ማነው እኔን የሚያክመኝ፤ እግር እያለኝ፣ መንቀሳቀስ እየቻልሁ፤ በድህነቴ ላይ ሽባ ሆኜ ልኑር ወይ?” ብዬ እያለቀስኩ ብለምነው “አሁን ምንም ላደርግ አልችልም፡፡ ሰኔ 28 ይመለሱ” አለኝ፡፡ የሚገርመው “እዚህ ሀገር የትም ሆስፒታል ይሄ ነገር አይወጣልሽም፡፡ አቅም አለኝ ብለሽ ውጭ ሀገር ብትሄጅም መዳን አትችይም” እያለ ነበር ተስፋ የሚስቆርጠኝ፡፡ አንድ የህክምና ባለሙያ ላይ ያለ ሰው እንዴት እንዲህ ይናገራል?

**ግዮን፡- ዶ/ሩ በራስ ደስታ ሊያክምዎት ካልቻለና ፈቃደኛ ካልሆነ ለምን ወደ ሌላ ቦታ ሪፈር እንዲልክዎት አልጠየቁም?**

**ወ/ሮ ታደለች**፡- ደጋግሜ ለመንሁት፤ አብሮኝ የሄደው ይሄ ትንሽ ልጅ ራሱ ተናገረ፤ ዶ/ሩ ግን ሊሰማኝ አልቻለም፡፡ በኋላ አማራጭ ሳጣ፣ በቃ ቤቴ ልግባ እዛው እሞታለሁ፤ መንግሥት ከጎዳና ወደ ቤት በሚሰበስብበት በዚህ ሰዓት ሆስፒታሎች በእንዲህ ዓይነት ክፉ ሰዎች መሞላቱ ያሳዝናል፡፡ እኔ ብሞትም ግድ የለኝም፤ ግን ገና በተወለደ በሁለት ወሩ፣ አባቱ የሞተበትን ልጅ በየሰው ቤት ልብስ እያጠብሁና እየተንከራተትሁ፤ በላስቲክ ቤት ውስጥ ብርድና ፀሐይ እየተፈራረቀብኝ ያሳደግሁት ልጄ ዘጠነኛ ክፍል ደርሶልኛል፤ ትንሽ መቆየት የፈለግሁት ለሱ ነበር፡፡ መስመር ይዞልኝ እኔ ብሞትም ግድ የለኝም፡፡

ቀጣዩን ቃለ ምልልስ በገጽ 12 ይመልከቱ



# ከቦምቡ ጥቃት በስተጀርባ

- የጥቃቱ ዒላማ ማነው?
- የይስሙላ 'ጥበቃ' ለምን?
- ጣቶች ወዴት ይጠቁማሉ?
- ኤፍ. ቢ. አይ. ምን ይሠራል?



"የፖለቲካው ትኩሳት ከፍ ወዳለ ግለት በተቀየረበትና ዘርና ብሔር ለይቶ መቧደን በነገሠበት በዚህ ዘመን፤ ከነተለያየ የፖለቲካ አመለካከቱ መስቀል አደባባይ የወጣው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ አንድ ሆኖ መዋሉ ብቻ ሳይሆን በሰላም ተበትኖ ወደየቤቱ መግባቱን ከተአምር ለይቼ አላየውም" ይላል በቅርቡ ከአሜሪካ ለቤተሰብ ጥየቃ ወደኢትዮጵያ የመጣው ትውልደ ኢትዮጵያዊው አቶ ዘሩባቤል ነጋሽ፡፡

ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. መስቀል አደባባይ ላይ ተካሂዶ በነበረው ታላቅ ህዝባዊ ሰልፍ ላይ እንደሚገኝ ሲናገር አሜሪካ የሚገኙት ቤተሰቦቹ በሙሉ እንደተቃወሙት አልሸሸገም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ "በሰልፉ ላይ ችግር ቢፈጠር ለጉዳት ትዳረጋለህ" የሚል ስጋት ነው፡፡

"አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሀገር ውስጥ ለሚካሄደው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሩቅ ስለሆኑ ስጋት ቢኖራቸው አይገርምም፡፡ ዘመዶቼና ባለቤቴም እዚህ ያለውን የህዝብ ስሜት ስላልተገነዘቡት ለደህንነቴ ቢፈሩ አልፈርድባቸውም፡፡ ነገር ግን ፍቅር፣ መደመር፣ ይቅርታ በሚሰበክበትና መሬት እስኪጠብ ድረስ ሁሉም ሰው አንድነትን እየዘመረ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ለመደገፍ በወጣበት በዚያ ዕለት ሰይጣን ካልሆነ በቀር ክፋት የሚያስብ የሰው ልጅ ይኖራል ብዬ በህልሜም በእውኔም አላሰብኩም ነበር" ይላል ዘሩባቤል፡፡

መስቀል አደባባይ ሲደርስ የገጠመውን ሲናገር፣ "ከአእምሮዬ በላይ ነው" ይላል፡፡ "ይህንን መቼም የሚደገም የማይመስል ታላቅ ታሪክ በቦታው ቆሜ ለማየት በመብቃቴ እድለኛ ነኝ" ይላል ዘሩባቤል፡፡

ያ የህዝብ ማዕበል የተሳተፈበት ታላቅ ህዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ እንደዘሩባቤል ምኞት ያለምንም እንከን ቢጠናቀቅ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምኞት ነበር፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ አንድነት፣ በአዲሱ መሪዋ የህዝብ ወገንተኝነት፣ በሀገሪቱ በተሰበከው ፍቅርና ይቅርታ እንዲሁም በተግባር በተወሰዱ ከቀድሞ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የራቁ እርምጃዎች ደስ ያልተሰኘ አንድ ቡድን ያንን የመሰለ ዓለም ኢትዮጵያን ባነሣ ቁጥር ሁሌም ሲያስታውሰው ሊኖር የሚችል ታላቅ ታሪክ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ አለፈ፡፡ የቦምብ ጥቃት ተፈጸመ፡፡

እንደሰልፉ አስተባባሪዎችና ብዙ ዜጎች ግምት ይህ ጥቃት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ለመግደል የተቀነባበረ የእኩዮች የሸብር ተግባር ነው፡፡ የኢትዮጵያን አዲስ ዘመን ለመዋጀት በተነሡት ጠቅላይ ሚኒስትር ሕይወት ላይ ለመፍረድ ክፋት የጠነሰሰው ይህ የሽብር ቡድን ዒላማውን ማሳካት ባይችልም ባደረሰው የቦምብ ጥቃት ግን የሁለት ዜጎችን ነፍስ ሲቀጥፍ ብዙዎችንም አቁስሏል፡፡

የክፋቱ ጠንሳሾች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ካደረሱት ጉዳት ባሻገር የዚህ ቀን ታሪካዊነት በዕለቱ በተደረጉ ንግግሮች፣ በተሰበከው ፍቅርና አንድነት፣ እንዲሁም በህዝቡ የመደመር ቃል ኪዳን እንዲከበር ሳይሆን፤ በጥቃትና በቁጭት እንዲታሰብ የወጠኑት ክፋት ግን የተሳካላቸው ይመስላል፡፡


ዓይናቸውን ሁሉ አዲስ አበባ ላይ አድርገው የነበሩ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ገና ሁነቱን ለመዘገብ መረጃ በማጠናቀር ሂደት ላይ ሳሉ የተከሰተው ፍንዳታ የዜና አቅጣጫቸውን ወደቦምብ ጥቃት እና የአደጋ ዘገባ እንዲያዞሩ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም በስፍራው የተገኙ የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎችም ይሁኑ መረጃዎቹን ከሌሎች ያገኙ መገናኛ ብዙኃን "አዲሱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ከተቃጣባቸው የቦምብ ጥቃት አመለጡ" በሚሉና በመሰል ዜናዎች የአየር ሰዓታቸውንና ገጻቸውን አጨናንቀው እንዲውሉ አድርጓቸዋል፡፡

እንደብዙዎች አነጋገር "ይህ ቡድን ያልተሳካለት የፍቅር ሰባኪውን ጠቅላይ ሚኒስትር ሕይወት መንጠቅ ብቻ ነበር፡፡ የትኛውም አይነት ጉዳት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ተከስቶ ቢሆን ኖሮ ዳፋው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካ ፖለቲካዊ መረጋጋት ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ በቀላሉ የማይገመት ይሆን ነበር"

ለመሆኑ ለዚህ ግዙፍ ህዝባዊ ንቅናቄና ሰላማዊ ሰልፍ የተሰጠው የጸጥታ ጥበቃ ትኩረት ምን ያህል ነበር? መንግሥት ስለጥቃቱ መረጃ ነበረው? ጥቃቱን ማን ሊፈጽመው ይችላል? ለዚህ ጥቃት የእጅ ቦምብ መጠቀም ለምን አስፈለገ? ጥቃቱ ዒላማ ያደረገው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ነው? ከጥቃቱ በኋላ የተወሰዱ እርምጃዎች ምንድናቸው? የአሜሪካው የፌዴራል ምርመራ ቢሮ ለምን መጣ? የሚሉና ሌሎችም ጉዳዮችን በዚህ ጽሑፍ እንዳስሳለን፡፡

## የሰልፉ አጀማመር

የዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ መነሻ ሐሳብ የመጣው መንግሥት የአልጀርሱን ስምምነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመፈጸም መወሰኑን በመቃወም ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም. በአዲስ ▶



አበባ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ መወሰናቸውን አዲስ አበባ የሚኖሩ የትግራይ ኢሮብ ማህበረሰብ ህዝቦች ለመገናኛ ብዙኃን የሰጡትን መግለጫ ተንተርሶ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በሰጠው መግለጫ፣ "የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ የአልጀርሱን ስምምነት ወደተግባር ለመተርጎም የሰጠው መግለጫ ወቅቱን ያልጠበቀና በተለይም በድንበር አካባቢ የሚገኘውን ነዋሪ ህብረተሰብ ያላወያየ ነው" ብሎ መውቀሱ፣ ይህም ብቻ ሳይሆን የድርጅቱ አባላትና የሶሻል ሚዲያ አክቲቪስቶቹ በባድመ አካባቢ የሚኖረው ህዝብ መሬቱን ላለማስቀማት ትግል ቢያደርግ "ሕጋዊ መብቱ" እንደሆነ በመጥቀስ በመገናኛ የሰላም ሐሳቡን የሚያደናቅፍ መረጃ አናፍሰዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከጉዳዩ ጀርባ ለህዝብ የማሰብ ሳይሆን "የፖለቲካ ሽፍጥ አለ" ብሎ ያመነውን አብዛኛውን ዜጋ አበሳጭቶታል፡፡

በተለይም በኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ በዘጠኝ አባላቱ የተወከለው ህወሓት ከሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ጋር በጋራ የወሰነውና ያጸደቀው ስምምነቱን የማስፈጸም ውሳኔ በመገናኛ ብዙኃን ሲገለጽ፤ መቀሌ ላይ ስብሰባ በማድረግ ራሱን ከዚህ ስምምነት ተቃራኒ የቆመ አስመስሎ ከማቅረቡ ባሻገር ከግንባሩ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ሌሎች አወዛጋቢ ጉዳዮች የታጨቁበት መግለጫ ማውጣቱም ብዙዎችን ግራ አጋብቷል፡፡

"ህወሓት ከፌዴራሉ ሥልጣን አንድ አንድ እየተባለ መቀነሱ ብቻ ሳይሆን መሥራች አባላቱ ጭምር ከፖለቲካው መድረክ በጡረታ መገለላቸው ስላስኮረፈው ህዝብን የተከለለ ተንኮል እንዲጠነስስና ይህንን መግለጫ እንዲያወጣ ዕድል ሰጥቶታል" ብለው የሚያምኑም ጥቂት አይደሉም፡፡

በዚህ ሳቢያ በቀዳሚነት የኢሮብ ህዝቦች የህወሓትን መግለጫ ደግፈው ጥያቄያቸውን እንዲያሰሙ ሁኔታዎች በመመቻቸታቸው በሁለት ረድፍ ተሰልፈውም ቢሆን ተቃውሟቸውን የአልጀርሱ ስምምነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲተገበር ውሳኔ አሳልፈዋል ብለው ባመኑባቸው (ህወሓትን ያላካተተ) የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ላይ ባሉበት ሆነው ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፡፡ በማስከተልም የዚህ ህዝብ አካል የሆኑት የአዲስ አበባዎቹ 180 የኢሮብ ህዝብ ተወላጆች መነሻውን ፒያሳ ያደረገና በቸርችል አደባባይ አድርጎ መስቀል አደባባይ የሚደርስ ተመሳሳይ ሰልፍ፣ እሁድ ሰኔ 10 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. ሊያካሂዱ መሆኑን፣ ይህንን ዓላማ የሚደግፍ አካልም እንዲቀላቀላቸው በመግለጫ ይፋ አደረጉ፡፡

ይህንን ተከትሎ "ህወሓት በጋራ የወሰነውን ውሳኔ መቀሌ ሄዶ እንደማያውቀው ሆኖ ተቃውሟል፤ ይህ ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የአንድነት እና የመደመር እቅድ ላይ የትግራይን ህዝብ ለመቀነስና የሰላም ጉዞውንም ለማስተጓጎል የተሸረበ አሻጥር ነው፤ የኢሮብ ተወላጆች ያዘጋጁት ሰላማዊ ሰልፍም ከዚህ የተለየ አጀንዳ የለውም" ብለው ያመኑ ዜጎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ "ከጎንህ ነን" የሚል የድጋፍ ድምጽ ለመስጠትና ለማመስገን በሳምንቱ ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ እንደሚያደራጁ አሳወቁ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ የኢሮብ ተወላጆች ሊያካሂዱ ያሰቡትን ሰልፍ መሰረዛቸውን ይፋ አደረጉ፡፡ የሰልፉ አስተባባሪ ምክንያታቸውን ሲናገሩ "በዚያው ሳምንት በሶሻል ሚዲያው ሰልፉ የሚካሄደው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ለመቃወም ነው የሚል ከአጀንዳችን ውጪ የሆነ መረጃ ስለተነዛብን፣ ፍቃድ ሰጪው ክፍልም የጸጥታ ችግር እንዳይፈጠር እንድንሰርዘው ስለጠየቀን ነው" ብለዋል፡፡

የሰኔ 16ቱ ሰልፍ አስተባባሪዎች ግን የቅዳሜው ሰልፍ ከኢሮብ ተወላጆች ሰልፍ ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ እንደሌለና ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይንና የመደመር አጀንዳቸውን ለመደገፍ ብቻ የሚካሄድ ነው" በማለት በዝግጅቱ ቀጠሉበትና ከከተማው ሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ አውጥተው፣ የመንግሥትንም ይሁንታ አግኝተው ዝግጅቱን አካሄዱ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ለሰልፉ አንድ ቀን ሲቀረው በቦታው እንደሚገኙ በማሳወቃቸው ሁሉም ዜጋ እንዳየው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ፎቶግራፍና "እናመሰግናለን፣ እንደመራለን" በሚሉ መልዕክቶች ባሸበረቀ ህዝብ ከተማዋን ያንቀጠቀጠና በታሪክ ከዚህ ቀደም ያልታየ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የታደመበት ሰልፍ ተካሄደ፡፡

## ይህ ጥበቃ ጠቅላይ ሚኒስትሩን አይመጥናቸውም!!

በአዲስ አበባም ይሁን በሌላ ስፍራ ይህንን መሰል ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሲካሄድ፣ በተለይ የጊዜው ሁኔታ ግምገማ ከጸጥታ ጥበቃ ጋር ሲገናዘብ አሉታዊ ሆኖ ከተገኘ አጋጣሚውን በመጠቀም ያልተፈለገ ተግባር ለመፈጸም የሚሞክሩ አካላት እንደሚኖሩ እንኳን የጸጥታ አካላት ቀርቶ ማንም ተራ ሰው አስቀድሞ የሚገምተው ነገር ነው፡፡ ይህ እንዳይሆን ደግሞ በተለመደው አሠራር አስቀድሞ ዝግጅት ይደረጋል፡፡

እስከቅርብ ጊዜ በነበረው አሠራር መሰረት በከተማዋ እንደአፍሪካ መሪዎች ስብሰባና መሰል ትላልቅ ኹነቶች ሲካሄዱ፣ የጸጥታውን ተግባር በበላይነት የሚቆጣጠረው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ (ለጽሕፈት ቤቱ) የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ የጸጥታ ኮማንድ ፖስት ነው፡፡ ይህ ኮማንድ ፖስት ከመከላከያ ሠራዊት፣ ከብሔራዊ ደህንነት፣ ከፌዴራል ፖሊስ እና ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የተውጣጣ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜም ማዘዣ ጣቢያውን አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ ያደርጋል፡፡

ኹነቱ በመስቀል አደባባይ ሲካሄድ ደግሞ የዝግጅቱ እንግዶች በሚቀመጡበት ስፍራ አስቀድሞ የአካባቢ ፍተሻ የሚካሄድ ሲሆን፤ ቦታው ከማንኛውም አስጊ ነገር የጸዳ መሆኑ ሲረጋገጥ ከኹነቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ቦታው በቋሚ ጥበቃ ቁጥጥር ሥር ይውላል፡፡ በዕለቱ የከተማዋ ፖሊስ ኃይል በሙሉ ኃይሉ እንዲሰማራና ተጠባባቂ ኃይል (ስታንድ ባይ) እንዲደራጅ የሚደረግ ሲሆን፣ በኹነቱ ስፍራ የድንገተኛ የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ እንዲሁም የቀይ መስቀልና የፖሊስ አምቡላንሶች ከሙሉ ኃይላቸው ጋር ዝግጁ ሆነው እንዲጠባበቁ ይደረጋል፡፡ የአድማ በታኝ ስኳድ ሙሉ ትጥቁን አድርጎ በተጠባባቂነት ከዝግጅቱ ስፍራ ኋላ እንዲጠባበቅ ሲደረግ፣ የተወሰነ ስኳድ ደግሞ ዝግጅቱ ስፍራ ላይ እንዲታይ ይደረጋል፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ የሚደረገው ኃይልን ለማሳየትና ክፋት ያሰቡ ኃይሎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ መልዕክት ለማስተላለፍ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም አላስፈላጊ ችግር ቢከሰት፣ ወዲያው የቴክኒክና የታክቲክ ምርመራ ለማካሄድ ብቃት ያላቸው የፖሊስ ወንጀል ምርመራ ባለሙያዎች የተሟላ የአሻራ እና መሰል ቴክኒክ መመርመሪያ መሣሪያ ከተገጠመለት ተሽከርካሪያቸው ጋር እስከዝግጅቱ ፍጻሜ በተጠንቀቅ ይጠባበቃሉ፡፡ አካባቢውንና ህዝቡን በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚቀርጹ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎችም የሚመደቡ ሲሆን፣ ስፍራው CCTV የሚባለው የሰርቪላንስ ካሜራ ከተገጠመለትም በሚገባ መሥራቱ አስቀድሞ በባለሙያ ይረጋገጣል፡፡


ይህ የጸጥታ ጥበቃ ዝግጅት ለማንኛውም በሀገር ደረጃ ከፍ ያለ ነው ተብሎ ለሚገመት ኹነት የሚካሄድ ሲሆን፣ በኹነቱ ስፍራ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚገኙ ከሆነ ደግሞ በበለጠ ጥብቅነት እና ከፍተኛ ዝግጁነት ስፍራው "ይወጠራል"፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የጸጥታ ኃላፊ ከዕለቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ከሚመለከታቸው የኮማንድ ፖስቱ አመራሮች ጋር በስፍራው በመምጣት በመሣሪያ የታገዘ የፈንጂና ተቀጣጣይ ነገሮች ፍተሻ ያደርጋል፡፡ ቦታው ለጥበቃ አመቺ መሆኑን፣ የታጠቁ ጥበቃዎች የሚቆሙበትን ስፍራ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግል አጃቢዎች የሚቆሙበትን ስፍራ ይወስናል፡፡ አስፈላጊውን የጥበቃ ፕላን ያወጣል፡፡ ይህ ሓላፊ የሀገሪቱን ከፍተኛ የሥልጣን ቁንጮ ሕይወት የመጠበቅ ሓላፊነት ያለበት በመሆኑ ሁኔታው ለእይታ እና ቁጥጥር እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመጠበቅ አመቺ ሆኖ ካላገኘው የዝግጅት ስፍራ እስከማስቀየር ድረስ ሥልጣን አለው፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የመከላከያ ሠራዊት፣ የቤተ መንግሥት ጥበቃ አልሞ ተኳሾች በስፍራው ባሉ ሕንጻዎች ላይ ራሳቸውን ከዕይታ ከልለው በዝግጅቱ ቦታ የሚከናወነውን ማንኛውንም ነገር አቅርቦ በሚያሳይ መነጽር (BINOCULAR) ለማየት የሚያመቻቸውን ስፍራ እንዲይዙም ይደረጋል፡፡

ይህ ሁሉ ዝግጅት ተካሂዶና ሁኔታው አስተማማኝ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጦ ካልሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደስፍራው እንዲመጡ አይደረግም፡፡ ከዚህ አንጻር የሰኔ 16ቱ የጸጥታ ጥበቃ ሁኔታ ምን መልክ ነበረው? የሚለውን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

አንደኛው ክፍተት የፖሊስ ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመመደቡ ነው፡፡ መስቀል አደባባይ ላይ የተሰማራው የፖሊስ ኃይል ቢበዛ ከአንድ ክፍለ ከተማ ወረዳዎች ብቻ የተውጣጣና ከህዝቡ ቁጥር አንጻር እዚህ ግባ የማይባል ነበር፡፡ እንዲህ አይነት የፖሊስ ኃይል የሚጠይቁ ዝግጅቶችን ከዐሥሩም ክፍለ ከተሞች የፖሊስ ኃይል በማሰባሰብ መሸፈን የሚቻልበት ዕድል ነበር፡፡ በዚህ ሳቢያ ቦምብን ያህል ነገር እስኪያልፍ ድረስ ከፍተኛ የፍተሻ ልልነትና ክፍተት ተፈጥሯል፡፡

ሁለተኛው ክፍተት ከአምቡላንስ በስተቀር ከላይ የተገለጹትና አደጋ ቢያጋጥም ፈጥነው መንቀሳቀስ የሚችሉት እንደ ፖሊስ ምርመራ ቡድን፣ የእሳት አደጋ መከላከያ እና አድማ በታኝ ስኳድ በስፍራው አልነበረም፡፡

ሦስተኛው ክፍተት በስፍራው የተገጠሙና ወደህዝቡ አነጣጥረው የሚቀርጹ ሰርቪላንስ ካሜራዎች አለመኖራቸው እየታወቀ፣ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑ የፖሊስ የጥበቃ ካሜራ ባለሙያዎች አለመመደባቸው ነው፡፡ ይህም ፍንዳታው የተከሰተው በቅርብ ርቀት እንደመሆኑ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ሊገኝ



የሚችለውን ሁነኛና የማያጠራጥር የቪዲዮ ማስረጃ አስቀርቶታል፡፡

አራተኛው ክፍተት ስፍራው ለማንኛውም እንቅስቃሴ ዝግ መሆንና መታጠር ሲገባው (ባልተጣራ መረጃ) ቦምብ አፈንጂዎቹን ይዞ ወደመድረኩ ለመጠጋት አልፎ ገባ እየተባለ የሚነገረው የፖሊስ መኪና ሳይቀር የጥበቃ ክልሉን ጥሶ ለመግባትና ለመቆም አስችሎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመድረኩ አናት ላይ የሚያልፈው የባቡር ሐዲድ ዝግ መሆን ሲገባው ትኩረት የሰጠው ባለመኖሩ ዝግጅቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ እንኳን ባቡር ሲያልፍበት ታይቷል፡፡ ይህንንም የጸጥታ ልልነት አልተጠቀሙበትም እንጂ አሸባሪዎች ሳይቸገሩ ዒላማቸውን ከላይ ሊያገኙበት የሚችሉበት ትልቅ ዕድል ፈጥሮላቸው ነበር፡፡

አምስተኛው ክፍተት በተለምዶ ክቡር ትሪቡን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞ ቦታ በባቡሩ ሐዲድ ሳቢያ ለዕይታ አመቺ ባለመሆኑ ምክንያት አማራጭ ተደርጎ የተገነባው መድረክ ከፍታ ከ2 ሜትር የማይበልጥ መሆኑ በመድረኩ ላይ የሚገኝ ማንኛውንም አካል በቀላሉ ዒላማ ለማድረግ አመቺ ማድረጉ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ሲያደርጉ ብቻ ከቆሙበት ጥይት መከላከያ መስተዋት ውጪ ሲወጡ የተቀመጡት ከፊትም ይሁን ከኋላ ለማንኛውም ጥቃት ዒላማ መሆን በሚችሉበት ግልጽ ቦታ ላይ ነበር፡፡

ስድስተኛው ክፍተት በህዝቡና መድረኩ መካከል ከ30 እስከ 40 ሜትር ርቀት ባዶ ስፍራ መከለል ሲገባው ሰዎች በጣም በቅርብ ርቀት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማየት በሚችሉበት ቦታ ላይ እንዲቆሙ ተደርጓል፡፡ ይህም በአጋጣሚ አልተሳካም እንጂ የእጅ ቦንቡ ቢወረወር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አካባቢ በቀላሉ ለመድረስ እንዲችል ምቹ ሆኗል፡፡

እንግዲህ ምላሽ የምታሳልፍ ክፍተት የማይገመት አደገኛ ችግር የምትፈጥርበት የጸጥታ ጥበቃ ሳይንስ እንዲህ ተዝረክርኮ አንድን የሀገር መሪ በዚህ አይነት ንዝህላል የጸጥታ ጥበቃ ለአደጋ መዳረግ፤ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ሴኩሪቲ ታሪክ ያልነበረ ተግባር ነው፡፡

ምናልባትም በዚህ የተነሣ ሊሆን እንደሚችል በሚገመት ሁኔታ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ ረዳት ኮሚሽነር ግርማ ካሣን ጨምሮ ዘጠኝ የፖሊስ አመራር አካላት በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው ነው፡፡

## መንግሥት ስለጥቃቱ መረጃ ነበረው?

ብዙ ሰዎች ፕሮግራሙ 4 ሰዓት እንደሚጀመር ተገልጾ ሳለ ቀደም ብለው መገኘታቸውንና ንግግር አድርገው ማጠናቀቃቸውን በማየት "የጠቅላይ ሚኒስትሩ የጸጥታ ኃይሎች ስለጥቃቱ መረጃ ነበራቸው" የሚል ግምታቸውን ሲናገሩ ተሰምቷል፡፡ ይህንን ግምት ግን ከላይ የገለጽናቸው የጸጥታ ክፍተቶች ፉርሽ ያደርጉታል፡፡

በርግጥ ቅድመ ደህንነት ጥበቃ በኹነቱ ስፍራ ከሚካሄድ የአካል ፍተሻና የመሣሪያ አሰሳ ጎን ለጎን ከቀናት አስቀድሞ እስከዝግጅቱ ማጠናቀቂያ ድረስ የራዲዮ ሞገድ ላይ የሚገኙና በስልክ መስመር የሚመጡ የተመረጡ ድምጾችን (ለምሳሌ ቦምብ፣ ፍንዳታ ወዘተ) በመጥለፍና በመተንተን እንዲሁም የተጠረጠሩ ምልልሶችን በማድመጥ አደጋ መታቀድ አለመታቀዱን ለመገመት ያስችላል፡፡ በጂፒኤስ በመመራትም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አካላት በቁጥጥር ሥር አውሎ ማጣራት ይቻላል፡፡ በብዙ የዓለም ሀገራት ከተሞች እንደተለመደው አዲስ አበባ ውስጥም የቦምብና ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን እንቅስቃሴ የሚከታተልና የሚጠቁም (ዲቴክት የሚያደርግ) መሣሪያ አለ፡፡ ይህ መሣሪያም ቅድመ አደጋን ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

በዚህ ስሌት የጸጥታ ኃይሉ ቅድመ መረጃ ቢኖረው ኖሮ እጅግ ጥብቅ የሆነ ፍተሻ ሲያካሂድ፣ አካባቢውን በብዙ ኃይል ሲከብብ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከዕይታ ሲከልል እናየው ነበር፡፡ ይህ ግምት ቢኖር ኖሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባሉበት አካባቢ እንኳን በዚህ ቅርበት በሩቅም መጠጋት አይቻልም ነበር፡፡ ጸጥታ ኃይሉ አደጋው አሥጊ ነው ብሎ ካመነና አደጋ አድራሾቹን መያዝ፣ ካልቻለም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአካባቢው እንዳይገኙ እስከማድረግ የሚደርስ እርምጃ ይወስድ ነበር፡፡ ያየነው ግን ለአንድ ሚኒስትር የማይደረግ የተከፋፈተና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለአደጋ ያጋለጠ ጥበቃ ነው፡፡

## ጥቃቱን ማን ሊፈጽመው ይችላል?

በአሁኑ ወቅት ብዙዎች ከምርመራው ውጤት ጓጉተው የሚጠብቁት የዚህን ጥያቄ መልስ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍንዳታው አንድ ሰዓት በኋላ በሰጡት መግለጫ ላይ "የታቀደና የተቀነባበረ" እንዲሁም "ሙያቸውን በመተገን" የሚሉ ቃላት መጠቀማቸው፤ ድርጊቱ በቅጥረኛ የጸጥታ አካላት (በሥራ ላይ ያሉ ፖሊሶች ወይም በቅርቡ የተበተኑት የቀድሞ የደህንነት አባላት) የተከናወነ ለመሆኑ ፍንጭ ሰጥቷል ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ ጥቃት አድራሾቹ ከኢህአዴግ ከራሱ ውስጥ ያኮረፉ ኃይሎች ናቸው የሚል ግምታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡ ጥቂቶች ጥቃቱ የተሸረበው ለፖለቲካ ፍጆታ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቡድን አካባቢ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የሰልፉ አዘጋጆች ላይ ጣታቸውን ይቀስራሉ፡፡ ዞሮ ዞሮ ይህንን ትንተና መሥራት የሚቻለው ከውጤቱ መታወቅ በኋላ በመሆኑ፣ የምርመራው ሂደት ላይ ተጽዕኖ ላለማሳደር የተሰነዘሩ ግምቶችን በዚህ ጽሑፍ ላይ ማካተት ተገቢ አይሆንም፡፡

## ጥቃቱ ዒላማ ያደረገው ማንን ነው?

ይህ ጥያቄ አወዛጋቢ ነው፡፡ ጥቃቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ዒላማ አድርጎ ከሆነ "በቅርብ ርቀት ያለ ሰው ቦምቡን ወደጠቅላይ ሚኒስትሩ መድረክ መወርወር እየቻለ ለምን እዚያው አፈነዳው?" የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡ በሌላ በኩል የሰልፉ አስተባባሪ ኮሚቴ በመግለጫው፣ "ግለሰቡ ቦምቡን ሊወረውረው ሲል ሰዎች ተረባርበው አስጣሉት" የሚል መረጃ መስጠቱ አደጋው ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የታለመ ነው ያስብላል፡፡ ያኮረፈውን የኢህአዴግ ኃይል በዚህ ወንጀል የሚጠረጥሩ ሰዎች "ጥቃቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ዐልሞ ቢሆን ኖሮ የሚደርሰው ጥፋት እና ጥርጣሬው የሚያነጣጥርበት ስፍራ የት እንደሆነ ስለሚታወቅ፣ ተጠርጣሪው አካል ራሱን ለግልጽ አደጋ አጋልጦ የሚሰጥበት ሞኝነት የለበትም" በማለት ግምቱ ስህተት እንደሆነም የሚያብራሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ዘይኑ ጀማል እንዳሉት፤ ይህ ጥያቄ ከምርመራ በኋላ የሚመለስና ድርጊቱ በትክክል "ነው / አይደለም" ብሎ ለመገመት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያላሟላ ነው፡፡

## የአሜሪካው የፌዴራል ምርመራ ቢሮ ለምን መጣ?

ይህ ቦምብ ጥቃት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመግደል ታስቦ ከሆነ የሀገሪቱን ሰላም ወዳልተጠበቀ ብጥብጥና ምናልባትም ወደርስ በርስ ጦርነት የሚከተት፣ የአፍሪቃ ቀንድ ሀገራትን ሰላምም በእጅጉ ሊያደፈርስ የሚችል እጅግ አደገኛ ሙከራ ነው፡፡ ስለሆነም ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የወንጀሉ ዓላማ በሠለጠኑ የምርመራ ባለሙያዎችና በሰለጠነ ፎረንሲክ ጠርቶ መውጣት ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የጸጥታ ኃይሉም በራሱ ተጠርጣሪ በመሆኑ ጉዳዩ በገለልተኛ ኃይል እንዲጣራ ማድረግ የተመለደ አሠራር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ አስተማማኝ ተቋም ኤፍ ቢ አይ ነው፡፡ ይህ ተቋም ማጣራቱን በብቸኝነት የሚያካሂድ ሳይሆን፤ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እንዲሁም ከፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በተውጣጡና በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ይታገዛል ተብሏል፡፡ ከወዲሁ ግን የዚህን ተቋም ወደኢትዮጵያ መምጣት አጥብቀው የተቃወሙና ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል የራሳቸውን ግምት ያስቀመጡ አክቲቪስቶች መኖራቸው የሥጋቱ አቅጣጫ የት እንደሆነ ያመላክታል ይላሉ ጉዳዩን የሚከታተሉ ዜጎች፡፡

የአሜሪካ ብሔራዊ የምርመራ ቢሮ (ኤፍ ቢ አይ) ባለሙያዎች ሥራ ጀምረዋል፡፡ ምርመራው የድርጊቱ ፈጻሚ ማነው? የድርጊቱ ዒላማ ማን ነበር? በድርጊቱ ውስጥ የፖሊስ ተሳትፎ አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጥያቄዎችን ለመመለስ ያለመ መሆኑን ኮሚሽነር ጀማል ለጋዜጠኞች ሰሞኑን ተናግረዋል፡፡

## ጣቶች ወዴት ይጠቁማሉ?

የምሥራቅ አፍሪቃ የጸጥታ ጉዳዮች ተንታኝ አቶ ሃሌ ሉያ ሉሌ ለአልጀዚራ ቴሌቪዥን እንደተናገረው፤ የጥቃቱ ፈፃሚ ማንነት ገና በፖሊስ ምርመራ የሚጣራ ቢሆንም፣ ያኮረፉ ቡድኖች አሉ ከመባሉ ጥርጣሬ አንጻር በገዢው ግንባር መካከል ያለውን ያለመተማመን ግን ያሰፋዋል፡፡ "ፍንዳታውን ተከትሎ መግለጫ የሰጡ የኦህዴድ ከፍተኛ ሹማምንቶች፤ ይህ ነገር ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመግደል የተደረገ ነገር ነው ሲሉ ተሰምተዋል፡፡ ይህ በኢሕአዴግ አራቱ አባል ፓርቲዎች መካከል ያለው በተለይ ደግሞ በህወሓት እና ኦህዴድ መካከል ያለው አለመተማመን እና ልዩነት እየሰፋ እንደመጣ የሚያሳይ ምልክት ይመስለኛል" ብሏል ሃሌ ሉያ፡፡

የኦህዴድ ሹማምንት፣ "ይህ ተቋም፣ ይህ ፓርቲ" ብለው ጣት የጠቆሙበት የለም ያለው ሃሌ ሉያ "ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት የቦምብ ጥቃቶች ወይም የአሸባሪ ጥቃቶች ብሎ መንግሥት የሚፈርጃቸው ነገሮች ሲከሰቱ፣ ብዙ ጊዜ ጣት የሚጠቆመው በግንቦት ሠባት፣ በኦነግ፣ በኦብነግ ወይም ደግሞ በኤርትራ ላይ ነበር" የሚለው ተንታኙ እነዚህ ኃይሎች የመንግሥትን የለውጥ እንቅስቃሴ በመደገፋቸው አሁን ጣት የሚቀሰረው ራሱ ግንባሩ አካባቢ ነው ይላል፡፡



**ልዩ ዕትም**



ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

# በፈርዖን ቤት ያደገው ሙሴ

የታሪክ ድርሳናትና የሃይማኖት ቅዱሳት መጻሕፍት ስለሙሴ ልደትና እድገት በሰፊው ዘግበዋል፤ ኦሪት ዘጸአት በሚል በሚታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የሙሴ ታሪክና የፈርዖን አገዛዝ በሰፊው ታትቷል:: የዕብራይስጡ "ኤላህ ሽሞዝ" በሚል የሚታወቀው መጽሐፍም የሙሴንና የፈርዖንን ታሪክ ይተርካል:: በቅዱስ ቁርዓን ደግሞ "አል ካኽፍ" በተባለው ሱራ ላይና በተለያዩ የቁርዓን ሱራዎች ላይ ስለሙሴ ታሪክና ማንነት ተጽፏል:: የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስለሙሴ መተረክ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በሙሴ ኃይል፣ መንፈስና አምሳል እኛ ኢትዮጵያውያንን ማርና ወተት ወደምታፈስ ከነዓናዊት "ዴሞክራሲ" ሊያሻግሩን እግዚአብሔር መራሔ መንግሥት አድርጎ የሰየማቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን በተመሳሳይነት ለማነጻጸር ነው::

ስለሰው ማንነት መናገር ሲጀመር ስምን አስቀድሞ መተርጎም ልማድ ነው፤ የሙሴ ስም መጠርያ ከተወለደበት ዘመን ጋር ታሪካዊ ትስስር አለው፤ ፈርዖን ከእርሱ ሌላ ወንድ ተወልዶ፣ አድጎ እንዳይነግሥና በመንግሥቱ ላይ እንዳያምጽ በማሰብ በግብጽ ፈርዖናዊ አስተዳደር ዕብራውያን ሴቶች የሚወልዱት ወንድ የኾነ እንደኾነ፤ በዐባይ ወንዝ ውስጥ ተጥሎ እንዲገደልና ትእዛዙ እንዲፈጸም በአዋጅ አዋላጆች ተነግሮአቸው ነበር:: ሙሴ የተወለደው በዚህ የመከራ አዋጅ ዘመን ነበር፤ ሙሴ በግብጽ፣ ዐባይ ወንዝ ላይ ተጥሎ የፈርዖን ሴት ልጅ ስላገኘችው ልጄ ነው ብላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እየተባለ አደገ:: በባሕር ላይ በመገኘቱ ስሙ ሙሴ ተባለ፤ "ሙሴ" የሚለው መጠርያ ስሙም በራሱ "ከውኃ ውስጥ መውጣትና ከመከራ አልፎ መገኘት" የሚል ፍቺን ያስገኛል::

ሙሴ በሕጻንነቱ ከዐባይ ውኃ የመትረፉ ትርጉም፤ በኋላ ዘመን ያንን ውኃ በእምነት ዕብራውያንን እንደሚያሻግርበት ለማመላከት ነበር:: በሙሴ አምሳል ማንነታቸውን የምናነጻጽረው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ልደትና ስማቸውን ስንመለከት ተነጻጻሪነት አለው:: ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ1967 በኋላ ከሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሥ፤ ወደ ሥዩመ ወታደር ማርክስ ተሸጋግራለች፤ ይህ ዘመን የመከራ ዘመን ነበር፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ከተወለዱበት ዓመት ቀደም ባሉት ዓመታት ጀምሮ የሰው ልጆች ከአማራ ነጻ እንውጣ ብለው ጫካ ገብተው መመሸጋቸውን አሜሪካዊው ዶናልድ ሊቨን ጽፏል:: የኢትዮጵያ ምሁራን ጉድጓድ እየተማሰባቸው በአሰቃቂ ሁኔታ የሚቀበሩባቸው ዓመታት ነበሩ:: በዚህ ዘመን ወንድ ልጅ ወልዶ ማሳደግ እጅግ ከባድ ፈተና የሚታይበት ጊዜ ነበር::ሸ

በነዚህ አስከፊ ዓመታት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ተወለዱ፤ ስማቸውም ዐቢይ ተባለ፤ "ዐቢይ" የሚለው ስምም መገኛው ግእዝ ሲኾን፣ ፍቺውም በዐይኑ "ዐ" "ዐቢይ" ተብሎ ሲጠራና ሲጻፍ፤ ትርጉሙ "ትልቅ" ማለት ነው፤ ስሙ ትልቋን ኢትዮጵያ ለመመለስ የተወለዱ መኾናቸውን ያሳያል:: የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ እናት በዚህ አስከፊ ዓመታት ትልቅ የሚኾነውን ልጃቸውን ወልደው አሳደጉ፤ የሙሴ እናት የፈርዖን ቤት አገልጋይ ኾና ሙሴን እንደአሳደገችውና፤ የአባቶቹን ታሪክ እንደነገረችው ተጽፏል:: እንደዚሁ ሁሉ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ እናት፣ ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር እንደኾነች፣ ዶ/ር ዐቢይም ታላቅ እንደሚኾኑና እንደሚነግሡ ተናግረውላቸዋል፤ የታላላቆቹን የኢትዮጵያ አንድነት ነገሥታትን ታሪክ፤ ለምሳሌ፡- የእነእምዬ ምኒልክን ታሪክ አስጠንተዋቸዋል::


የአሁኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ የመንግሥት አስተዳደርና ተጥባበ ነገራቸው (ዲፕሎማሲ)፤ የእምዬ ምኒሊክን ፈለግ መከተሉ ያለምክንያት አለመኾኑን እንረዳበታለን፤ ይልቁንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ መንበረ ሥልጣኑን በጨበጡ ዕለት ስለ እምዬ ምኒልክ በአድናቆት ተናግረዋል:: እርሳቸውም ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ በመግዛትና በማስተዳደር ሣልሳዊ ምኒልክ ተብለው የመጠራት ማዕረግን ያገኛሉ ብዬ አምናለሁ:: እንዲህ ያለውን የመንግሥት አስተዳደር ትምህርት፣ በቤታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ከእናታቸው ካልተማሩት በስተቀር፤ በፈርዖናውያን አገዛዝ ት/ቤቶች ማግኘት እንዴት ይቻላቸው ነበር? ሙሴ ስለእነአብርሃም አባቶቹ ያወቀውና ማርና ወተት ስለምታፈሰው ስለከነዓን ምድር የተረዳው እናቱ ስላስተማረችው ነበር፤ ነገር ግን በፈርዖን ካድሬዎች ይሰጥ የነበረው ትምህርትማ ጥቅም የሌለው የአስማትና የጥላቻ ተረት ነበር፤ እንደዚሁ ሁሉ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ሃያ ሰባት ዓመታት ሙሉ በካድሬዎች ከሚነገረው "አማራና ኦሮሞ፤ እሳትና ጭድ ናቸው" ከሚለው የሐሰት ትምህርትማ ኹላችንም ተላቀናል፤ ምክንያቱም አማራና ኦሮሞ እንደጭቃና ጭድ ተባብረው ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ተደምረው የጋራ ቤታቸው ኢትዮጵያን የጠበቁ ነባር ኢትዮጵያውያን መኾናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አስቀድመው ከእናታቸው የተማሩ ስለመኾናቸው እንረዳለን:: እርሳቸው በኢትዮጵያውያን እናቶች ልቡና ውስጥ የተሳለውን የእናታቸውን ራእይ ለመተግበር እግዚአብሔር በጥበብና በሞገስ ስላሳደጓቸው "ዐቢይ" መባላቸው ሲያንስ እንጂ አይበዛባቸውም::

ሙሴ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ከሚገኝ የሌብነት ክብርና ድሎት ይልቅ ከሕዝቡ ጋር መከራን ስለመቀበሉ ተጽፎለታል:: እንደዚሁ ሁሉ፣ ዶ/ር ዐቢይም በፈርዖናውያን አገዛዝ ውስጥ ከሚገኘው ሹመት፣ ሽልማት፣ አበልና አባልነት፤ እንዲሁም በሙስና ከመበልጸግ ይልቅ ከኢትዮጵያውያን ጋር መደመርንና ፍቅር መመሥረትን ፈለጉ:: "ሌብነትም ጽዩፍ እንጂ ኩራት እንደማይኾን" ለኢትዮጵያውያን አወጁ:: "ስንኖር ኢትዮጵያዊ፤ ስንሞት ኢትዮጵያ" መኾናችንን ሲነግሩን ኢትዮጵያዊነትን በዘረመላችን ውስጥ ዘሩበት::

ነቢዩ ሙሴ በሥነ ፍጥረት ታሪክ የገለጻት ያልተሸራረፈችውና ያልተገነጣጠለችው ኢትዮጵያና ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ የሚያውቋት ኢትዮጵያ አንድ ናቸው:: ኹለቱም የሚያውቋት ኢትዮጵያ መታወቅያዋና መቀነትዋ ዐባይ የኾነላት ጥንታዊት ኢትዮጵያ ናት:: እርሷም "ኢትዮጵያ ዘየአውዳ ግዮን፤ የዐባይ ወንዝ የሚከባት ኢትዮጵያ" በመባል ትታወቃለች:: ይህች ኢትዮጵያ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሰፋች የጥንቷ ኢትዮጵያ ናት:: እዚህች ኢትዮጵያ ውስጥ በሙሴ የተገለጹት ሀገሮች ሁሉ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ኢትዮጵያ ውስጥም ተጠቃለዋል፤ ሱዳኖች ተካትተዋል፤ ኤርትራ በፍቅር ተደምራለች፤ ሶማልያና ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጋር ሳይፋቱ ተባብረዋል፤ ኬንያ አንድ ኾናለች፤ ግብጽ መልእክተኞቿን ልካ ከኢትዮጵያ ጋር ውኃ ለመቅዳት በዐባይ ተጎራብታለች::

ይህቺ ኢትዮጵያ፣ ሙሴ እንደነገረን በመጀመርያ የተፈጠረው ሰው አዳም ይኖርባት የነበረችው፤ የኢትዮጵያ ወንዝ ግዮን የተባለው ዐባይ የሚያጠጣት ገነት ናት:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም ሰኔ 16 ቀን፣ በመስቀል አደባባይ ባደረጉት ንግግር፤ "ይህቺ የፈጣሪ ጥበብ መጀመርያ"፤ "ይህቺ የሰው ዘር መገኛ"፤ …በማለት እየነገሩን የነበረው የሙሴን ቃል መሠረት ያደረገና በሳይንስ የተረጋገጠውን የኢትዮጵያዊነት መገለጫችንን ነበር::

በዚህች የሰባት ሺህ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ኤርትራ ብቻ ሳትኾን የመንም በኢትዮጵያዊነት ቅርጽ ነበረች:: እንደ ታሪክ ምንጮቻችን "ኤርትራ" ማለት በላቲን ቋንቋ የቀይ ባሕር መጠርያ እንጂ የሀገር መጠርያ አልነበረም፤ ቀድሞ እንኳን ሙሴ እኛ ኤርትራን ስናውቃት፣ ስሟ ኢትዮጵያ ኾኖ ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም፣ በሙሴ የታሪክ መረጃ ሀገር ያልነበረችውን የትላንቷን ኢትዮጵያን የዛሬይቱን ኤርትራ በመደመር ከኢትዮጵያዊነት ቀላቅለዋታል:: ከዐባይ ወይም ከተከዜ በስተቀር በሥነ ፍጥረት ታሪክ ለኢትዮጵያ ካርታ መታወቅያነት አልጠቀሰም:: ►



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም የሚነግሩን “አማራ በመኾን”፤ “ትግሬ በመሆን”፤ “ኦሮሞ በመኾን”፤ “ጉራጌ በመኾን” እና በመሳሰሉት ብሔሮች እየታጠረች፣ በዘር ተተብትባ እያነሰች የመጣችው ትናንሿ ኢትዮጵያ ሳትኾን፤ በሙሴ የተገለጸችውን ኢትዮጵያን ያቀፈችና ድሙራን የኢትዮጵያ ግዛቶችን ያጠቃለለች የሰባት ሺህ ዓመታት ታሪክ ያላትን ታላቋን ኢትዮጵያን ነው::

ለምሳሌ የኢዝንበርግን የታሪክ ሰነድና የጀምስ ብሩስን ምስክርነት ከተቀበልን በዘመነ መሳፍንት “ትግሬ መኾን” የሚል ጽንሰ ሐሳብ ተፈጥሮ ነበር፤ ይህ የማኅበረሰብ አደረጃጀት ጽንሰ ሐሳብ እየዳበረ ወሰኑን ተከዜ በማድረግ የአንድ ማኅበረሰብ መጠርያ ኾኖ ተገለጸ:: በዚህም አካሄድ ከተከዜ በስተደቡብ ያለውን ሀገር ብቻ አሳንሶ፤ ሀገረ አምሐራ የማለት ዝንባሌ እየተፈጠረ እንዲመጣ ከፍተኛ ጥረት መደረጉና የቅኝ ግዛት መስመር መሰመሩ ተጽፏል:: ይህ የቅኝ ገዢዎች መስመር ስለመኾኑ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ዕውቀት ያልተሰወረ መኾኑን ዐውቀነዋል::

ይኹንና የሀገራችንን መልክአ ምድራዊ ገጽታና ወሰን ስንመለከት፤ ከጥንቱ የእንግሊዞች ተንኮል ከፊል የወሰን አከላለልን በመውሰድ፣ ከቅርቡ የጣልያን ወረራ ወቅት የጎሳ ክልል አፈጣጠርን ከነልዩ ልዩ ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሐሳቡን በማቀናጀት የተንጸባረቀችው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አንሳለች:: እኛም በዚህች በዘር ባጠበብናት፣ ባነሰችው ኢትዮጵያ፤ በዘር፣ በጎሳ ስንፋጅባት ዓመታትን አስቆጥረናል:: ሥዩመ እግዚአብሔር የኾኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ግን ኢትዮጵያ ስንል ሙሴ በሚያውቃት የኢትዮጵያ ገጽታና ካርታ መገለጥ እንዳለባት ስለሚያምኑ፤ የታላቋ ኢትዮጵያን ግዛት ለመመለስ መደመርን መርጠዋል:: ይህም በፈርዖን ቤት እንዳደገው ሙሴ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ ቢያድጉም በልዩነት ኢትዮጵያን በመግለጽ ከሙሴ ጋር ተባብረዋል::

ሙሴም ኾነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይን የሚያስተባብራቸው ሌላኛው ገጽታ ደግሞ በጋብቻ የተጣመሯቸው የኢትዮጵያውያን ሴቶች አድራሻ ነው:: እንደ አምላካውያት መጻሕፍት ምንጭነትና እንደ ግብጽ የታሪክ ምሁራን ሙሴ የተከዜን ባሕር በእግሩ ተሻግሮ ኢትዮጵያ በመምጣት ከኢትዮጵያዊቷ ሲፓራ ጋር ተጋብቷል፤ ከአባቷ ከካህኑ ከዮቶር ሥርዐተ መንግሥትን ተምሯል:: በዚሁ አንጻር የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይን ሕይወት ስንመለከት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም ሙሴ በተጓዘበት መንገድ የጥንቷን የሊቃውንት መፍለቅያ ጎንደርን እስከ ተከዜ ድረስ ዐይተዋል፤ ከጎንደር የዘር ሐረጓ የሚመዘዘውን ቤጌ ምድሬዋን ልዕልት ቀዳማዊት እመቤትን አግብተዋል::

ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን በማግባቱ “ለምን ጥቁር አገባ?” የሚል አስተሳሰብ የገዛ ወገኖቹ የተቃውሞ ሐሳብ እንደነበራቸው በመጽሐፍ ተጽፏል:: በዚህ መስመርም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይን እንደ ኦሮሞ ብቻ ስለቆጠሩአቸው “ለምንድን ነው የራሳቸውን ክልል ሰው ያላገቡት?” ብለው ጥቂቶች ሊያጉተመትሙባቸው ይችሉ ይኾናል:: በዚህም ብቻ ሳይኾን ሙሴን በፈርዖን ቤት ከማደጉ የተነሣ 430 ዓመታትን ካስቆጠረው ከግብጽ ባርነት ለማውጣት ከፈርዖን የተለየ አስተዳደር አያመጣም ብለው በጉዞ ላይ የነበሩት ዕብራውያን በሙሴ ላይ ማንጎራጎራቸው ተጽፏል::

ሙሴ ግን ስለሕዝቡ ክፋት ይጸልይ ነበር፤ “ሕዝቤን ከምታጠፋ እኔን ከሕይወት መጽሐፍ ሰርዘኝ” ይል ነበር:: በዚሁ ልክ የፖለቲካ ኪሳራ ከገጠማቸው መካከል፤ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ወይም ሆን ብለው፤ በኢሕአዴግ ውስጥ ያደገ ሰው እንዴት ከኢሕአዴግ የተለየ የለውጥ ፕሮግራም ሊያመጣ ይችላል? ድራማ ነው! ውሸት ነው! በማለት የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይን የለውጥ ጉዞ ለማደናቀፍ ጥቂቶቹ ማጉረምረማቸው አልቀረም:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ግን ልክ እንደሙሴ ሁልጊዜ የምሕረትና የይቅርታ ሰው መኾን እንዳለባቸው ለሕዝቡ ሳያስታወቁ ያለፉበት መግለጫ የለም::

የዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ኪሳራ ውጤት የኾነው ጥላቻ በሙሴ ላይ ከገዛ ወንድሙና እኅቱ ሳይቀር ተሰንዝሮበታል፤ ጥላቻውም በአንድ በኩል ከቅናት የሚመነጭ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፈጣሪ ለሙሴ “የፈርዖን አምላክ አደርግሃለሁ” የሚለውን ስጦታ ካለማወቅ የተነሣ የሚመጣ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም የፈጣሪን ስም መራሔ መንግሥት በኾኑበት ዕለት መጥራታቸው እግዚአብሔር እስከዛሬ ገዢዎች በነበሩት ላይ እንዳነገሣቸውና የኢትዮጵያ መራሔ መንግሥት አድርጎ እንደሾማቸው ያላወቁ ሕልም የመሠላቸው የፖለቲካ ቁማርተኞች ዛሬም ሻጥር ይሠራሉ፤ ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ እንዳሉት፣ እነዚህ ቁማርተኞች “ትላንት አልተሳካላቸውም፤ ዛሬም አልተሳካላቸውም፤ ነገም አይሳካላቸውም::”

የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ልዕልና ያበሳጫቸውና የፖለቲካ ኪሳራ የደረሰባቸው በቅንዓትና በምቀኝነት ከሰውነት ባሕርይ ወጥተው እንደናቡከደነጾር ወደ እንስሳነት ባሕርይ ተቀይረው አዲስ አበባን እየለቀቁ ጫካ የገቡም ጥቂቶች አይደሉም:: ኢየሱስ ክርስቶስ “ሥልጣን አልለቅም” ያለውን ሔሮድስን ቀበሮ እንዳለው ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም በበኩላቸው ለዓመታት ሥልጣን ላለመልቀቅ አሸባሪ የኾኑትንና የሰው ደም የሚጠጡትን “የቀን ጅቦች” ብለዋቸዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም ግንቦት 11 ቀን ከእንደራሴዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፤ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚደረገውን ሔሮድሳዊ የመብት ጥሰትን “አሸባሪነት” ነው ሲሉ አብራርተዋል:: ለመንግሥት ለውጥና የህዝብን ፍላጎት ለማርካት ነቢዩ ሙሴ ሰባ ሰዎችን መርጦ፣ ፈርዖናዊውንም መዋቅር ጥሶ እንደወጣ ሁሉ፤ እርሳቸውም በኢትዮጵያዊነታቸው የሚታመኑባቸውን ሰዎች ይዘው የፈርዖናውያንን አፈ ሙዝ ሳይፈሩ በለውጥ ጎዳና ወጥተዋል:: ከዘር አደረጃጀት ፓርቲ ይልቅ የአስተሳሰብ ብዝኃነት ያለው የመድብለ ፓርቲ ሥርዐት መበረታታት እንዳለበት በሕዝብ እንደራሴዎች ፊት በዕለተ ሲመታቸው ባደረጉት ንግግራቸው ላይ አስተጋብተዋል:: እውነት ነው! ሙሴም ቢኾን በቤተ መንግሥት የፈርዖን የልጅ ልጅ ከመባል ይልቅ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት የሕዝቡን መከራ ትኩር ብሎ በመመልከቱ ለሥልጣን መብቃቱ ተጽፎለታል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም በኢትዮጵያ የንግድ ሥርዐት አንዱ እየገበረ ሌላኛው ሳይገብር የሚያጭበረብርበት ሂደት ያመጣውን የነጋዴውን መከራ ትኩር ብለው ተመለከቱ:: “መሬት የእግዚአብሔር፤ ፎቅ የገብረ እግዚአብሔር” እየተባለ የአንድ ብሔር ዘር ብቻ የበላይ የኾነበትን ብልጽግና ትኩር ብለው ተመለከቱ:: “ዘረኝነት ይጥፋ፤ ሙስና ይውደም”፤ “ደሃ ተበደለ፤ ፍርድ ተጓደለ”፤ የማይሉ ቤተ እምነቶችን በተለይ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን፣ የጳጳሳት አስተዳደርን ትኩር ብለው ተመለከቱ:: ይህንን ትኩር ብለው የተመለከቱትን፤ የህዝብ መከራና ችግር ሊያስወግዱ፣ በፍቅር ወደ ነጻነት እንዲያሻግሩ እግዚአብሔር ጠራቸው:: “እናስርሃለን፤ እንገድልሃለን፤” የሚሏቸውን ፈርዖናውያን ሳይፈሩ ከሕዝቡ ጋር በመደመር በዘረኝነት ከተተበተበው ቀንበር ወጥተው መንበረ ሥልጣኑ ላይ ተሰይመው መራሔ መንግሥት ኾኑ::

ሙሴ ሕዝቡን ከፈርዖናዊነት ወደ ሙሴአዊነት እየመራ አሻጋግሮታል:: ዕብራውያን ከሙሴ ጋር አንድ ኾነው በባሕር መካከል አልፈዋል፤ ሕዝቡ ከሙሴ ጋር በባሕር መካከል ማለፋቸው የሙሴ ተባባሪዎች አሰኝቷቸዋል፤ መራሔ መንግሥታችን በተገኙበት ሰኔ 16 የነበረው የሕዝብ ለሕዝብ መደመር ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ጋር ለመተባበር እጅ ለእጅ ተያይዘን ቃል ኪዳን ያደረግንበት ዕለት ነው:: ምክንያቱም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ መራሔ መንግሥት ከኾኑበት ዕለት ጀምሮ ስለሠሩት አስደናቂ ሥራ፤ የሰኔ 16ቱ የእውቅናና የድጋፍ ሰልፍ ሲደረግ፤ ከደመና በታች የነበረው የፈጣሪ ጥበቃ አልተለየንም ነበር፤ ፈርዖናውያን የቀን ጅቦቹ የወረወሩትን ፍላጻ ፈጣሪ በተአምር አክሽፎታል:: ሕዝቡ ደረቱን ለጦር፤ ግንባሩን ለጠጠር በመስጠት ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ ፍቅሩን የገለጸበት ነው:: በዕለቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም ሁላችንንም ኢትዮጵያውያንን በፍቅርና በመደመር ወደ ይቅርታ፣ ፍቅርና ነጻነት ማማ ላይ አውጥተውናል:: ከበቀል ሕግም ወደ ፍቅር ሕግ አሻጋግረውናል:: በፍቅርና በይቅርታ ብቻ ኢትዮጵያዊነታችንን እንድንገልጸው ተጠርተናል:: ፍቅርና ይቅርታ በክርስትናውም ኾነ በእስልምናው የፈጣሪ ስም መገለጫ ኾኖ መጻፉን የማያውቅ የለም:: በክርስትና መጻሕፍት ውስጥ “በስመ እግዚአብሔር መሐሪ ወመስተሳሕል፤ ይቅር ባይና ርህሩህ በሆነው በእግዚአብሔር ስም…” ሲል፤ የቁርዓን ሱራዎችም “ቢስሚላሂ ረህማን ረሂም፤ በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ርህሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ በኾነው…” ብለው ሲጀምሩ ይቅርታንና ፍቅርን ማወጃቸው ነው:: ይህ የግእዙም ኾነ የአረብኛው መግቢያ የእግዚአብሔር ስም መሐሪና ይቅር ባይ መኾኑ የተገለጸበት የይቅርታ መንገድ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም እየሠሩ ያሉት እኛ ኢትዮጵያውያን ይህን የእግዚአብሔርን ስም መገለጫ እንድናጸባርቅ ነው:: ሙሴ ዕብራውያንን ባሕሩን ካሻገራቸው በኋላ የሰጣቸው በፍቅር ሕግ የሚታሠሩ ትእዛዛትን ነው፤ እንደዚሁ ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይም ወደ አማናዊ ዴሞክራሲ ካሻገሩን በኋላ የሰጡን ሕግ ፍቅርንና ይቅርታን ነው:: “ስለፍቅር በስመ አብ ይቅር” እንደሚባለው ዓይነት ብሂል፤ ሃይማኖት፣ ቀለም፣ ጎሳ፣ ወዘተ ሳንለይ “ኢትዮጵያዊ ወገኔ ተነካ፤ ኢትዮጵያ ተነካች ብለን” እርስ በርስ እንድንዋደድና እንድንተዛዘን፤ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ በፈርዖን ቤት ካደገው ሙሴ ጋር ቃል ኪዳን ገብተናል:: ይቆየን….

“ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንዑ::”

ገለቶማ!

/ር ዘሪሁን ሙላቱ
የጥንታውያን ቋንቋዎችና ጽሑፎች ተመራማሪ





**ግዮን፡- አሁን ያገኘንዎት ጥቁር አንበሳ ነው፤ የህክምና ሂደቱ ምን ይመስላል?**

**ወ/ሮ ታደለች**፡- ሰኞ ዕለት ማታ 11 ሰዓት አካባቢ ነው ሰዎች ወደ ጥቁር አንበሳ ያመጡኝ:: እዚህ ስደርስ ሃኪሞቹ በፍቅር ነው የተቀበሉኝ:: ያኔም ከኔ የባሱ ስለነበሩ ነው አስረድተው ወደ ራስ ደስታ የላኩኝ:: ጥቁር አንበሳ እንደመጣሁ፣ ተገቢው ህክምና እየተደረገልኝ ነው:: አሁን ውስጥ ያሉትን ፍንጣሪዎች ሊያወጡልኝ ወደ ኦፕራሲዮን ክፍል ልገባ ነው:: ስፔሻል ዶክተሮችም ሆኑ ሌሎች የህክምና ባለሙያዎች በየሰዓቱ እየመጡ ከመመርመር ባሻገር ተገቢውን መድኃኒት እየሰጡኝ ነው፤ እግዚአብሔር እድሜ ከጤና ጋር ይስጣቸው::

**ግዮን፡- ቅዳሜ ዕለት እንዴት ነበር ሰልፍ የወጡት?**

**ወ/ሮ ታደለች**፡- መሪያችንን ለማመስገን ነው የወጣሁት:: ጠ/ሚኒስትሩ በዚህ አጭር ጊዜ የወደድናቸው፤ እውነተኛ የሀገር እና የሕዝብ ፍቅር ያላቸው መሪ መሆናቸውን በማረጋገጣችን ነው:: እንዲህ ዓይነት ፍቅር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሰጣቸው፤ ቀጣይ ብዙ ነገር ይሠራሉ:: ልጆቻችን የተሻለ ሕይወትና እድል ይገጥማቸዋል ብለን ስለምናምን ጭምር ነው በይፋ ልንደግፋቸው አደባባይ የወጣነው፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

## "ሕዝቡ በዚያ ቀውጢ ሰዓት የኛን ሕይወት ለማትረፍ ተረባርቧል"

## ያህያ ሂካ



**ግዮን፡- በቅድሚያ ራስህን አስተዋውቀን?**

**ያህያ**፡- ያህያ ሂካ እባላለሁ፤ ከቡራዩ ነው የመጣሁት:: ጠ/ሚ ዐቢይን በሚደግፈው ሰልፍ ላይ ተገኝቼ ነው በቦምብ ፍንጣሪ የተመታሁት::

**ግዮን፡- ጉዳት የደረሰብህ ምንህ ላይ ነው?**

**ያህያ**፡- መስቀል አደባባይ ከመድረኩ በስተቀኝ በኩል ነበር ያለሁት:: በወቅቱ በተጣለው የቦምብ አደጋ ሁለት እግሬ በፍንጣሪው ተጎድቷል:: እዚህ ጥቁር አንበሳ ተገቢው ህክምና ተደርጎልኝ ፍንጣሪዎቹ ሙሉ ለሙሉ በቀዶ ጥገና ወጥተውልኛል:: ግራ እግሬም ተቀጥቅጦ ጉዳት ደርሶብኛል::

**ግዮን፡- አደጋው በደረሰብህ ጊዜ ማነው አንሥቶ ወደ ሆስፒታል ያመጣህ?**

**ያህያ**፡- በዚያ ሰዓት ምንም ዓይነት የፀጥታ ኃይሎች በቦታው ላይ አልተመለከትሁም:: አደጋው የደረሰብንን ሰዎች አንሥተው፣ አምቡላንስ ውስጥ በማስገባት ወደዚህ እንድመጣ ያደረጉኝ በሰልፍ ላይ ያሉ ወጣቶች ናቸው:: የሰዎችን ሕይወት ለማትረፍ በዚያ ቀውጢ ሰዓት ምንም ሳይረጋጋ ሁሉም በቆራጥነት እኛን ለመርዳት ይረባረብ ነበር:: ይህ ሁሌም የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት የሚንቀሳቀስ መሆኑን ያሳያል::

**ግዮን፡- ወደ ሰልፉ ብቻህን ነው የመጣኸው?**

**ያህያ**፡- ከጓደኞቼ ጋር ነው የመጣሁት:: ያነሣሣኝ ደግሞ አሁን ያለው የሀገሪቱ ሰላም ወደተረጋጋ ሁኔታ እየመጣ ስለሆነ፤ ጠ/ሚኒስትሩን ለመደገፍና እንደማንኛውም ዜጋ ያለብኝን ግዴታ ለመወጣት ነው ወደ መስቀል አደባባይ የወጣሁት:: እየታየ ያለው ፈጣን ለውጥ ወደፊት የተሻለ ነገር እንደሚጠብቀን አመላካች ነው:: የዚህ ጅምር ተስፋ ፈንጣቂ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሆናቸው በዕለቱ እኔና ጓደኞቼ እንደሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ለሰልፍ ወጥተናል::

**ግዮን፡- ከአደጋው በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሆስፒታል ተጎጂዎችን ጎብኝተዋል፤ እርሳቸውን ስታገኛቸው ምን ዓይነት ስሜት ፈጠረብህ?**

**ያህያ**፡- ጠ/ሚንስትሩ በዚያኑ ቀን ሆስፒታል ድረስ በመምጣት በአደጋው የተጎዳነውን ሰዎች ጎብኝተውናል:: ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው በመጠየቃቸው፤ እውነተኛ የሀገርና የህዝብ መሪ መሆናቸውን አረጋግጠውልናል:: በጣም ደስ ብሎኛል፤ ገና ከጉዳታችን ሳናገግም፣ ስቃይ ውስጥ እያለን፣ ፍፁም ባልጠበቅነው ሁኔታ፤ እርሳቸውን ከአጠገባችን ስናገኝ አደጋው የደረሰብን ሰዎች በሙሉ ሁሉን ነገር ረስተናል:: እንዲህ ዓይነት ለዜጎች ፍቅርን የሚሰጥ፣ ሀገሩን የሚወድ፣ ከሁሉም ጋር ፊት ለፊት ለመገናኘት የማይታበይ፣ ልበ ቀና የሆነ መሪ መሆኑን ሁላችንም በገሃድ ዐይተናል:: ይህ ትልቅ ነገር ነው:: ሕዝቡ እሳቸውን ደግፎ አደባባይ የወጣው፣ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ባሳዩት መልካም ጅምር ነው:: አሁን የተጀመረው ለውጥ ወደፊት መጓዝና እስከመጨረሻው ድረስ መቀጠል አለበት:: ባለፈው ሩብ ክ/ዘመን አንዳችም ኢትዮጵያዊ መንፈስ በዚህች ሀገር ላይ አልነበረም:: ሁሉንም ነገር ከዚህ ትግል ጋር የቀየሩትና መስመር ያስያዙት እርሳቸው ናቸው:: እርሳቸውን መደገፍ ኢትዮጵያዊነት ነው::

**ግዮን፡- ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት፤ የኦሮሞና የአማራ ወጣቶች አምባገነኑ ሥርዓት እንዲለወጥና እንዲወገድ ጭምር ትልቅ መሥዋዕትነት ከፍለዋል:: ከዚህ አኳያ የምታስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?**

**ያህያ**፡- አሁን እየተረጋጋች ነው ያለችው:: እኔ በበኩሌ አሁን የታየውን የለውጥ ጅምር ከልቤ እደግፋለሁ:: በርግጥ ይህ የተገኘው ባለፉት ዓመታት በኦሮሞና በአማራ ክልል በተከፈሉ ጠንካራ መሥዋእትነቶች ነው:: ያለፈው የአምባገነኖች አካሄድ እንዲመለስ አንፈልግም:: ለዘመናት ያሳለፍነውን የከፋ ጭቆና የመጠፋፋትና ዜጎችን በመሣሪያ ኃይል ረግጦ የመግዛት ዕድል ከዚህ በኋላ ይኖራል ብዬ አልጠብቅም:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ ኢትዮጵያን ወደተረጋጋችና ፍቅር ወደተሞላባት አገር እየመለሷት ይገኛሉ:: የጥላቻን መንፈስ አስወግደን የመደመርን መንገድ እንከተል ብለዋል:: በርግጥም የሚያስፈልገው ይህ ነው:: ወጣቶች በአንድነት መንፈስ ለተሻለች ኢትዮጵያ ከጠ/ሚንስትሩ ጎን በመሆን የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ቢያደርጉ፣ የምንመኘው ለውጥ በአጭር ጊዜ ይመጣል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

## "'መድኃኒት እናዝልሃለን፤ እሱን ውሰድ' ብለው በግድ ከህክምና ቦታው እንድወጣ አድርገውኛል"

## አብዱራህማን ከድር

**ግዮን፡- ስለራስህ ንገረን፤ ከየት ነበር የመጣኸው?**

**አብዱራህማን**፡- አብዱራህማን ከድር እባላለሁ፤ ከሻሸመኔ ነው ሰልፉን ለመታደም ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት:: በዕለቱ ሕዝቡ ከተለያየ ቦታ የተሰባሰበ ቢሆንም በፍቅርና በመተሳሰብ ድጋፉን ለጠ/ሚኒስትሩ እየሰጠ ነበር::

ይሁንና፣ በሰዓቱ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ይዘውት የመጡት የለውጥ መንገድ ያልተመቻቸው ወገኖች፤ እጅግ በጣም አስነዋሪ የሆነውን የቦምብ ጥቃት፤ በንፁሐን ዜጎች ላይ ፈፅመዋል:: በዚህ ሂደት እኔም ሁለት እግሮቼ ተጎድተው በሰዎች እርዳታ ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ተወስጄ ነበር::

**ግዮን፡- የካቲት 12 ሆፒታል እንደደረስህ ያገኘሸው ህክምና ምን ይመስላል?**

**አብዱራህማን**፡- የካቲት 12 እንደገባሁ በጣም ብዙ ደም ፈሶኝ ስለነበር ቁስሌን አሽገው ግሉኮስ ሰጡኝ:: ራጅና አልትራሳውንድ ተነሳሁ:: እግሬ ውስጥ በተለይ ጉልበቴ አካባቢ ፍንጣሪዎች እንዳሉ በግልጽ ያሳይ ነበር፤ ዶክተሮች ግን "ይህ ቀላል ነገር ነው፤ መድኃኒት እናዝልሃለን፤ እሱን ውሰድ" ብለው በግድ ከህክምና ቦታው እንድወጣ አድርገውኛል::

**ግዮን፡- ፍንጣሪ መኖሩ ከተረጋገጠ ለምንድን ነው የሕክምና ባለሙያዎች ሊያወጡልህ ፈቃደኛ ያልሆኑት? መርዙ እየተባዛና ሥር እየሰደደ**



**እንደሚሄድ ለማንም ግልጽ ይመስለኛል፤**

**አብዱራህማን፡-** "ፍንጣሪው ሰውነቴ ውስጥ ገብቶ እያቃጠለኝ ራሴን ሲያስተኝ እያያችሁ እንዴት ነው ውጣ የምትሉኝ" ብዬ ጠይቂያቸዋለሁ:: ሌሎች የተጎዱ ሰዎችም ተመሳሳይ ጥያቄ ለዶክተሮቹ አቅርበዋል:: እነሱ ግን "ይህን የምናዝልህን መድኃኒት ከፋርማሲ ገዝተህ እየተጠቀምክ በየጊዜው ሊወጣልህ ይችላል" የሚል አስነዋሪ ምላሽ ነው የሰጡኝ:: ታማሚዎችን ለመንከባከብ መጀመሪያ ላይ በዶክተሮች በኩል የነበረው ጠንካራ ፍላጎት፤ ከተወሰነ ሰዓታት በኋላ በምን ዓይነት መንገድ እንደተቀየረ ሊገባኝ አልቻለም::

ችግሩንና መፍትሔውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ለማድረግ አቅሙ ያላቸው ዶክተሮች እያሉ፤ እኛ በስቃይ ውስጥ ሆነን እንድንወጣ ተደርገናል:: የአልትራ ሳውንድ ውጤቱን ይዞ የመጣው ዶክተር ሲያናግረኝ "የአንተ ጉዳት በግልጽ ይታያል፤ ፍንጣሪውም የት ቦታ እንዳለ ስለሚታይ ያወጡልህ" ብሎኝ ነበር:: እኔም በዚያ መሠረት "ፍንጣሪዎቹን አውጡልኝ" ስል የየካቲት ሐኪሞች ግን "ወጣም፣ አልወጣም ችግር የለም፤ አንተ ዝም ብለህ ያዘዝንልህን ማስታገሻ ውሰድ" ነው ያሉኝ::

ብንጮህ ሰሚ ስላላገኘን 12፡30 ሲል አስወጡን:: አብረውኝ የነበሩ ሰዎች፣ አውቶብስ ተራ አካባቢ አልጋ ይዘው ጠበቁኝ፤ እዚያ አድሬ በማግስቱ ወደ ሻሸመኔ ተጓዝኩ:: ህመሙ በጣም ከባድ ነበር:: ዝዋይ አካባቢ ስደርስ ስቃዩን መቋቋም አልቻልሁም፤ እዚያ ከመኪና ወርጄ፣ አምቡላንስ ተልኮልኝ ወደ ቤቴ ወሰዱኝ:: ወዲያው ሆስፒታል ብገባም ዶክተሮችን ማግኘት አልቻልሁም::

**ግዮን፡- አሁን ያለኸው አርሲ ነገሌ ሆስፒታል ነው፤ እዚህስ የተደረገልህ ህክምና ምን ይመስላል?**

**አብዱራህማን፡-** አርሲ ነገሌ ሆስፒታል የገባሁት ሰኞ ጠዋት ነው:: ወደ ዐሥር ሰዓት አካባቢ ኦፕሬሽን ተደርጌ ጉልበቴ ውስጥ የነበሩትን ፍንጣሪዎች አውጥተውልኛል:: ቀኝ ጉልበቴ ላይ ስብራት ነበረ፤ እሱንም አክመው አሽገውልኛል:: አብዛኛው ፍንጣሪ ወጥቷል:: አንድ የቀረ አለ፤ እሱን "ብዙ ችግር አይኖረውም፤ ካስቸገረህ እኔ ሁሌም እዚሁ ነኝ፤ አወጣልሃለሁ" ብሎ በየጊዜው እያየኝ ነው:: ብብቴ ውስጥ ደግሞ ሁለት ፍንጣሪ ነበር፤ በስተቀኝ በኩል ያለውን አውጥተውልኛል:: በስተግራ በኩል ያለውን የየካቲት 12 የህክምና ባለሙያዎች ሳያወጡ ነው የሰፉት፤ "በዚህ በኩል አካልህ ተጎድቷል:: ስለዚህ በሌላ ትሪትመንት እንድትከታተል እናደርግሃለን" ብለውኛል::

**ግዮን፡- የየካቲት 12 ሆስፒታል ዶክተሮች ፍንጣሪዎችን ሳያወጡ ነበር የሰፉት?**

**አብዱራህማን፡-** ምንም አላወጡልኝም:: በፈንጂ የተጎዳነውን ሰዎች እንድንወጣና ወደ ቤታችን እንድንሄድ ቢያስገድዱንም፤ እኔን በአቅም ደረጃ ከእነሱ ያነሰው የአርሲ ነገሌ ሆስፒታል አስፈላጊውን ትብብር አድርጎልኛል:: እኔ በአደጋ ላይ ሆኜ እንዲህ አይነት ነገር ከገጠመኝ፣ ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚጉላሉ አስቡት:: መንግሥት በእንደዚህ ዓይነት የህክምና ባለሙያዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት::

# ሕዝብ ለዴሞክራሲ ያሳየውን ፍቅር በጥላቻና በሽብር መግታት አይቻልም! አርበኞች ግንቦት 7

ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓም በሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ መስቀል አደባባይ ወጥቶ በዶ/ር ዐቢይ አሕመድ መሪነት ለተጀመረው የለውጥ ሂደት ያለውን ድጋፍ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት እና ጨዋነት ገልጿል። ኢትዮጵያውያን ልዩነቶቻቸውን አቻችለው የፈቀዷቸውን ሰንደቆችና ዓርማዎች ይዘው አደባባይ ወጥተዋል፤ የተለያዩ ዜማዎችን አዚመዋል። ዛሬ ኢትዮጵያውያንን አገራዊ አንድነት፤ የነፃነት ፍላጎት እና የለውጥ ተስፋ አስተባብሯቸዋል። የዶ/ር ዐቢይ የለውጥና የመቻቻል መርህ ገዢ ሀሳብ ሆኖ ቀርቧል።

ይሁን እንጂ፣ ይህ ፍጹም ሰላምተኛ ሕዝብ በተሰበሰበበት፤ ለውጥ፣ ፍቅርና መቻቻል በተሰበኩበት መድረክ ላይ የቦምብ ጥቃት ተፈጽሟል። በዚህም ምክንያት በሰው ሕይወትና አካላት ላይ ጉዳት ደርሷል።

አርበኞች ግንቦት 7 የአንድነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን የሽብር ጥቃት በጽኑ ያወግዛል። ድርጊቱ ተጣርቶ የጥቃቱ ፈፃሚዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይጠይቃል።

ንቅናቄዓችን አርበኞች ግንቦት 7 እንዲህ አይነቱ እኩይ ድርጊት እንዲፈጸም ሃሳብ የሚያመነጩ፣ የሞራልና የቁስ ድጋፍ የሚያደርጉ፣ ድርጊቱን የሚፈጽሙትን አካላት በሙሉ፣ ይህ የጥላቻና የጠብ መንገድ ከማንም በላይ በመጨረሻ የሚጎዳው ራሳቸውን እንደሆነ "የጫረው እሳት ሲፈጀው ታየ" በሚለው የአባቶቻችን አባባል እያስገነዘበ፣ አደብ እንዲገዙ ያሳስባል።

አርበኞች ግንቦት 7 ለሞቱት ወገኖቻችን ቤተሰቦች መጽናናትን ይመኛል፤ እነዚህ ወገኖች ለለውጥ፣ ለፍቅርና መቻቻል የከፈሉት ዋጋ ሲዘከር ይኖራል። ንቅናቄዓችን በዚህ አደጋ ለቆሰሉት ወገኖቻችን የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን ይገልፃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በደረሰው አደጋ ሳይደናገጥ፤ ስሜቱም ሳይረበሽ የለውጡን ሂደት እንዲያፋጥን አርበኞች ግንቦት 7 ያሳስባል። ለሰላምና ለዴሞክራሲ ሁላችን ዘብ እንቁም።

አንድነት ኃይል ነው!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

# የግጭት ፖለቲካ ይከፋፍለናል እንጂ አይደምረንም

የግጭት ፖለቲካ ይከፋፍለናል እንጂ አይደምረንም

አዲስ የተሾሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደሥልጣን ከመጡ ጀምሮ የጋራ ንቅናቄያችን በድርጅት ደረጃ ሲያራምዳቸው የቆያቸውን መሪ ሐሳቦች እርሳቸው በመንግሥት ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸውን ስንመለከት ጊዜ ሳንወስድ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለንን አድናቆትና ድጋፍ ሰጥተናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ያከናወኗቸውን ጅምር ተግባራት በጥሞና ሲከታተል የቆየው አስተዋዩ የአገራችን ሕዝብ፤ ቅዳሜ ሰኔ 16፤ 2010 ዓ.ም በተለያዩ ከተሞች የምስጋና ሰልፍ አካሂዷል። የድጋፍ ሰልፎቹም ቀጣይነት እንደሚኖራቸው እምነታችን ነው። ለማህበራዊ ፍትሕ መስፈንና ለሰብዓዊ መብት መከበር የሚሟገተው ድርጅታችን፣ ይህንን በሕዝብ አነሳሽነት የተዘጋጀ ትዕይንተ-ሕዝብ፤ ከማንኛውም መንግሥታዊም ሆነ ፓርቲ ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ሰልፍ እንደሆነ በማመን፤ በቅንነትና በሙሉ ልቡ በመቀበል የድጋፍ ሰልፉን ደግፏል፤ እንደተሚጋች ድርጅት የሚያምንባቸውን ሀሳቦች በአገር ቤቱ ሰልፍ ላይ አንጸባርቋል። የጋራ ንቅናቄያችን ይህንን የምስጋና ትዕይንተ-ሕዝብ የደገፈው በሁለት ምክንያቶች ነው፤ አንደኛው ከላይ እንደተመከተው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባጭር ጊዜ ውስጥ ላከናወኑት ፈጣንና ድፍረትን ለተላበሱ የለውጥ ተግባራት ተገቢውን ምስጋና ለማቅረብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በጀመሩት ፍጥነት አድማሳዊ የሰብዕና መለኪያዎችን በመላበስ ሥር-ነቀል ማሻሻያዎቹን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማበረታታት ይጠቅማል ከሚል እምነት በመነጨ ነው። በመደመር ፖለቲካ ውስጥ እኛ ኢትዮጵያውያን የደረጃ ዜግነታችን ቀርቶ ማህበራዊ ፍትሕ በማግኘት ሰብዓዊ መብታችንን እንደምናስከብር እምነታችን በመሆኑ ድጋፋችን ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በክልል ከተሞች የተካሄዱ የድጋፍ ሰልፎች በሠላም መጠናቀቃቸው አስደሳች ቢሆንም፤ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሕዝብን ምስጋና ለመቀበልና አገራዊ መልዕክት ለማስተላለፍ በተገኙበት በአዲስ አበባው መስቀል አደባባይ ሰልፍ ላይ የደረሰው የቦንብ ጥቃት ግን እጅግ አሳዛኝ ሆኖ አግኝተነዋል። ኢትዮጵያን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ሊያሻግራት የሚችል ሕዝባዊ መነቃቃትና በአንድነት ጥላ ሥር የመሰባሰብ ህዝባዊ ፍላጎት ጎልቶ በወጣበት ቀን የደረሰው የቦንብ ጥቃት፤ ከተቀበረበት ለመነሣት እየታተረ ያለውን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ መልሶ ለመቅበር የተቃጣ እኩይ ድርጊት በመሆኑ የሽብር ድርጊቱን አጥብቀን እናወግዘዋለን። በጥቃቱ ሕይወታቸው ላለፈ ወጣቶች፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን መጽናናትን እንመኛለን። የእነርሱ ጉዳት የእኛም ጉዳት ሆኖ ተሰምቶናል። ከቁጥር የተቀነሱት ሰማዕታት በውስጣችን ተደምረዋል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገላለጽ፤ ይህ ሙያን ተገን አድርጎ የተፈጸመው ጥቃት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የእርቅና የምህረት ዘመኑን በደስታ እንዳያጣጥሙ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ በአዙሪት የታጀበውን የአገሪቱን የፖለቲካ ባህል ባለበት እንዲረግጥ የሚያደርግ እኩይ ድርጊት ነው። ሚሊዮኖች የታደሙበትን ታሪካዊውን ቀን በሽብር ተግባራችሁ ያጠለሻችሁ ተሸናፊ ኃይሎች፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋና ራዕይ ነጥቃችሁ ኀልውና ይኖረናል፤ ዳግም ወደሥልጣን መንበር እንመለሳለን ብላችሁ ባታስቡ መልካም ነው። ብሔራዊ ቅራኔዎች ባልረገቡባት አገር ይህን መሰል መዋቅራዊ የሽብር ጥቃት መፈጸም ህዝብን ለእልቂት፣ አገርን ለብተና ከመዳረግ ያለፈ ፖለቲካዊ ትርፍ የለውም። ታንክ ተደግፈን መጽሐፍ አንብበናል፣ በቦንብ ጥርሳችን ፍቀናል፣ ክላሽ አንግበን ዳገት ቁልቀለቱን ወጥተን ወርደናል ወዘተ... የምትሉ በ"ነፃ አውጪ" ሥም የምትነግዱ የፖለቲካ ኃይሎች፤ የፖሊስ፣ የመከላከያና የደህንነት ነባር መዋቅሮችን በመጠቀም አገር ከማተራመስ ተግባራችሁ እንድትቆጠቡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሥም እንጠይቃለን። በትንንሹ እዚህና እዚያ ሆነን ተሸራርፈን ኅብረት አለን ከምንል፤ በይቅርታ፣ በፍቅር እና ፍትሕ ላይ በተመሠረተ ብሔራዊ እርቅ ሳንሸራረፍ ምሉዕ እንሁን። በጥላቻ፣ በተንኮልና በክፋት ከምታተርፉት እጅግ የበለጠ ጥቅምና ትርፍ በመደመር፣ በአብሮነት ከሁሉም በላይ ደግሞ በሰብዓዊነት ታገኙታላችሁና ሰከን በሉ። የመበሻሸቅ፣ የመነታረክ፣ የግጭት ፖለቲካ ይከፋፍለናል እንጂ አይደምረንም፤ ይቀንሰናል እንጂ አያባዛንም። ስለዚህ ለፍቅርና ለሰብዓዊነት መሸነፍ ድክመት ሳይሆን ዘመኑን የሚመጥን ድፍረትና ጀግንነት መሆኑን አስባችሁ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደሚሉት ያምርብናልና "እንደመር"።

*ፈጣሪ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!*

*ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)*





*ቅዳሜ፣ ሰኔ 16/2010 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ታሪክ ደማቅ የሆነ ሕዝባዊ ሰልፍ ተካሂዷል፡፡ የድጋፍ ሰልፉ ገና በሦስት ወር የሥልጣን እድሜያቸው 27 ዓመት ርቆን የነበረውን ኢትዮጵያዊነት የመለሱልንን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ለማመስገን መሆኑ ደግሞ ለየት ያደርገዋል፡፡*

*በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መሪውን "እንወድሃለን፤ እናከብርሃለን፤ እናመሰግንሃለን" ብሎ አደባባይ ወጥቶ አልታየም፡፡ በወያኔ/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ የተሰላቸው ሕዝብ ላለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ያደረገውን ታላቅ ተጋድሎና ከፍተኛ መሥዋዕትነት ተከትለው ወደ ሥልጣን የመጡት ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ ግን ከጥላቻና ከጥፋት መንፈስ አውጥተው ወደ ፍቅርና መደመር መልሰውናል፡፡*

*እኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ መሪ ለማመስገን የድጋፍ ሰልፉን ያዘጋጁት ስድስት ኢትዮጵያውያን ግለሰቦች ናቸው፡፡ "ለውጡን እንደግፍ፤ ዴሞክራሲን እናበርታ" በሚል መርህ ያለ መንግሥትና ፓርቲዎች ድጋፍ በግለሰቦች የተጠራው ሰልፍ፣ በጥፋት ኃይሎች በተሰነዘረ የቦንብ ጥቃት የተወሰኑ ዜጎች ለአካል ጉዳትና ለሕይወት መጥፋት ቢዳረጉም፤ ሰልፉ ሙሉ በሙሉ የታለመለትን ግብ ባሳካ መልኩ ተጠናቋል፡፡ እኛ ደግሞ ስለ አጠቃላይ ዝግጅቱ፤ በዕለቱ ስለደረሰው ጥቃትና ተዛማጅ ጉዳዮች ከአስተባሪዎቹ መካከል ክንፈ ሚካኤል ደበበን (አበበ ቀስቶ)፣ ስንታየሁ ቸኮልንና፣ ስዩም ተሾመን አነጋግረናቸዋል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡*

# "ሆን ተብሎ የሽብር ሥራ ሲሠራ እንደነበር መገመት ይቻላል"

## ስዩም ተሾመ

**ግዮን፡- በመጀመሪያ፣ ሰላማዊ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴውን በምን ዓይነት መንገድ እንደተቀላቀልህ ብትገልጽን?**

**ስዩም**፡- ኮሚቴው የተመሰረተው በአጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል:: ጠ/ሚኒስትሩ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ መልካም ነገሮች በመታየታቸው ያንን የደገፉ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ሁሉ በህወሓት ወገኖች በኩል ደግሞ የሰውን መልካም ገጽታና የርሳቸውን የተሳካ መንገድ ለማበላሸት የሚደረግ እንቅስቃሴ በመኖሩ ምክንያት፤ ሕዝብ ከርሳቸው ጎን በመቆም አጋርነቱን እንዲያሳይ "ለውጥን እንደግፍ፤ ዴሞክራሲን እናበርታ" በሚል መርህ ሰልፍ መዘጋጀት ስላለበት ነው ኮሚቴውን የተቀላቀልኩት::

በመጀሪያ ስንታየሁ ቸኮል፣ አበበ ቀስቶና ሌሎች ሰዎች በጋራ ሆነው ሰኔ 17 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. የድጋፍ ሰልፉን ለማድረግ እንዳሰቡ ገልፀውልኝ፣ በእኔ ፌስ ቡክ ላይ ፖስት ሳደርግ፤ "እኛም ደግሞ በ16/2010 ዓ.ም. ልናደርግ አስበናል" የሚሉ ጉደታ እና አየለ የሚባሉ ሰዎች ያሉበት ሌላ ኮሚቴ መጣ:: እኔ በግሌ በማህበራዊ ሚዲያ ቅስቀሳ ለማድረግ ነበር መጀመሪያ ላይ ያሰብሁት:: ግን በኋላ ሁለቱም ወገኖች አንድ በመሆን እንዲገናኙና እንዲነጋገሩ በማድረግ ወደ አንድ ሐሳብ ሲመጡ እኔም በዚሁ ሂደት ውስጥ የኮሚቴ አባል በመሆን መሥራት ጀመርሁ::

**ግዮን፡- ኮሚቴው ስምምነት ካደረገ በኋላ የቀን ለውጥ ለምን ተደረገ?**

**ስዩም**፡- ይህን ሰልፍ ለማካሄድ አዘጋጅ ኮሜቴዎቹ መጀመሪያ ላይ ለሚመለከተው አካል ሄደው ባሳወቁበት ሰዓት ሰኔ 17፣ እሑድ ዕለት በአዲስ አበባ ስታዲየም የምስጋና ቀን በሚል መንፈሳዊ ፕሮግራም ስላለ በ100 ሜትር ርቀት ውስጥ እንዲህ ያለ ኤቨንት ማካሄድ በሕጉ መሰረት ተቀባይነት እንደሌለው ስለተነገራቸውና አሳማኝም ስለሆነ ነው የድጋፍ ሰልፉ ወደ ቅዳሜ ሰኔ 16/2010 ዓ.ም. የተዘዋወረው::

**ግዮን፡- ሰልፉ እንዲህ ባለ ታሪካዊ የሕዝብ ብዛት ይታጀባል ብለህ ጠብቀህ ነበር?**



**ስዩም**፡- እኛ እንደአዘጋጅ፤ ሕዝቡ ባየው አስደናቂ ለውጥ እንደተደሰተና ወደፊትም ኢትዮጵያ ላይ ትልቅ የለውጥ ተስፋ ይኖራል በሚል እምነት በጋራ ጠ/ሚኒስትሩን ለመደገፍ ይወጣል የሚል ሀሳብ ይዘን ነበር ሕዝብ ተባብሮና ተደጋግፎ የሚወጣበትን አቅጣጫ መስመሩን የዘረጋነው:: ሆኖም ግን እኛም ሆንን የትኛውም አካል በዚህ ደረጃ ይህን ያህል ሕዝብ ይወጣል ብለን አልጠበቅንም:: በእርግጥ ሁለት ሦስት ሚሊዮን ሕዝብ ይወጣል ብለን ተስፋ አድርገን ነበር:: በመጨረሻ ግን ከአራትና ከአምስት ሚሊዮን በላይ በድጋፍ ሰልፉ ላይ ታይቷል:: በዋናነት ላለፉት 13 ዓመታት ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጎ ስለማይታወቅ እንደዚህ ታሪካዊና ደማቅ ሰልፍ ይካሄዳል ብሎ የጠበቀ አልነበረም::

**ግዮን፡- በሰዓቱ የቦምብ ጥቃቱን በመፈፀም የተጠረጠሩትን ሰዎች የያዛችኋቸው እናንተ ነበራችሁ?**


**ስዩም**፡- ሕዝቡና በአካባቢው የነበሩ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች ናቸው ጥቃት ፈፃሚዎቹን የያዟቸው:: አደጋው ሲፈፀም እኛ ወደ ኋላ ሸሽተን ግዮን ሆቴል ውስጥ ነው የሄድነው:: በርግጥ ወደ ኋላ ተመልሼ ሰዎቹን ለማረጋጋት ሞክሬያለሁ:: ጠ/ሚኒስትሩ ላይም ሆነ አብረዋቸው የነበሩት ሰዎች ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳልደረሰ ስሜታዊ ሆነው ወደ መኪናዋ ሲሮጡ ለነበሩ ልጆች ተናግሬያለሁ::

በመቀጠልም ለተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ስልክ በመደወል ጠ/ሚኒስትሩ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳልደረሰ በመግለጽ እና መረጃ በመስጠት ሕዝቡን በማረጋጋት በኩል ትልቅ ሚና እንዲጫወቱ ግፊት አድርጌያለሁ:: በሦስተኛ ደረጃ ሕብረተሰቡ ያለውንና የደረሰውን የጉዳት መጠን አውቆ በተገቢው መንገድ እንዲንቀሳቀስና ወደ ግጭቶች እንዳያመራ የማድረግ ሥራ ነበር:: በእኔም ሆነ በኮሚቴው አባላት የተደረገው ይኸው ነው::

**ግዮን፡- እንደ ኮሚቴ አባልነታቸው በዕለቱ በፈንጂ ሕይወታቸውን ያጡትንና ለጉዳት የተዳረጉትን ብዛትና ማንነት በትክክል አረጋግጣችኋል?**

**ስዩም**፡- አስተባባሪዎቹ ይህንን ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ ልንቆጣጠር የምንችልበት አቅምም አሠራርም የለንም:: ይህንን ጉዳይ በዋናነት የሚያውቁት የፀጥታ ኃይሎችና እንደ እናንተ ያሉ የሚዲያ ተቋማት ናቸው:: እንደ ማስረጃ ሊቆጠር የሚችለው የፌዴራል ፖሊስ የሰጠው አስተያየት ነው:: ከዚህ በተረፈ ከተጎጂ ሰዎች ጋር ተያይዞ ያለውን ትክክለኛ መረጃ ሊያወጡ የሚችሉት የሕክምና ተቋማት ናቸው:: ከመንግሥት ተቋማትም ተመሳሳይ ነገር ሊኖር ይችላል::

ከዚያ ውጭ ግን አስተባባሪ ኮሚቴው ይህንን ነገር በከፍተኛ ሁኔታ ለማካሄድ አቅም የለውም:: በዕለቱ በሚዲያዎች በኩል ህዝቡን የማረጋጋት ሥራ ከተሠራ በኋላ እኔና የተወሰኑ የኮሚቴ አባላት፤ መጀመሪያ ዘውዲቱ፣ ቀጥሎ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመሄድ ጉዳት ደርሶባቸው የነበሩትን ሰዎች አጣርተናል:: በማግስቱም▶



ሁላችንም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመሄድ ተጎጂዎቹን ጎብኝተናል:: እኛ ማድረግ የምንችለው ይህን ነው::

**ግዮን፡- ከፖሊስ የሚወጡት መረጃዎች ብዙ ጊዜ የተሳሳቱ ናቸው:: ከዚህ በፊት በልምድ እንደምናውቀው፤ የሞተንም ሆነ የቆሰለን ሰው ከግማሽ በላይ ቀንሶና አሳንሶ ነው ለሕዝብ የሚገልፀው:: በሆስፒታሎች ተዘዋውሮ የተጎዳን ሰው መመዝገብ ምንም አቅም አይጠይቅም:: እናንተን የቸገራችሁ ምንድን ነው?**

**ስዩም**፡- ተዘዋውሮ መመዝገቡን አካሂደናል:: በየሆስፒታል እየዞርን፣ የራሳችንን ወኪሎች እየላክን ከነስማቸው ከነስልካቸው እየመዘገብን ነው ያለነው:: በመጀመሪያ ቀን ጥየቃ ነው ያካሄድነው:: በማግስቱ ግን አስተባባሪዎችን እየላክን የተጎዱትን ሰዎች በተለይ (በፈንጂ ፍንጣሪ) በአጠቃላይ ከነአድራሻቸው መዝግበናል:: ቤተሰቦቻቸውን እያነጋገርን ነው ያለነው፤ ይህ መረጃ ሙሉ በሙሉ ተጠናክሮ ሲወጣ ለህዝብ ይፋ እናደርጋለን::

**ግዮን፡- በዕለቱ የቦምብ ጥቃት የተፈፀመው በፀጥታና ደህንነት ረገድ በቂ ጥበቃ ባለመደረጉ ነው?**

**ስዩም**፡- በዚህ ህዝባዊ ሰልፍ ላይ ሊደረግ የሚገባው የፀጥታ ጥንቃቄ ተደርጓል ማለት አልችልም:: በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ነገር ሊከሰት እንደሚችል፤ ነገሮች በትንሽ ትንኮሳ ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ ሊያመሩ እንደሚችሉ ሥጋት ነበር:: በዚህ ረገድ ዋና መተማመኛችን የነበረው ህዝቡ ነው:: በሰልፉ ላይ ግጭት ሊያመሩ የሚችሉ ነገሮች ሲኖሩ በአስቸኳይ ለአስተባባሪዎች በመጠቆም ችግሮች በቀላሉ እንዲወገዱ በተደጋጋሚ ስንገልጽ ነበር::

ሰልፉ ከመካሄዱ ከሁለት ቀን ቀደም ብሎ፤ ሰኔ 14/2010 ዓ.ም. በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የአስተባባሪ ኮሚቴው ተወካዮች ከፖሊስ ኮሚሽን ስለሚገባው ጥንቃቄ፣ ሊመጣ ስለሚችለው አደጋ ከፀጥታ ኃይሎችም ሆነ ከአስተባባሪ አባላት ጋር በግልጽ ተወያይተናል:: በስብሰባውም ላይ ህዝቡ በጣም ጨዋ በመሆኑ የራሱን ደህንነት በራሱ የማስከበር ጽኑ እምነት እንዳለኝና የፖሊሶች ዋና ትኩረት መሆን ያለበት ታቅደው የሚፈፀሙ ተግባራት እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሆነ ገልጬ ነበር::

በዚህ በኩል የፖሊስ ኮሚሽነሮችም ሆኑ የደህንነት ሓላፊዎች ሐሳባችንን ተቀብለው፤ ጉዳዩም እነሱን እንደሚመለከትና አስፈላጊውን ጥበቃ እንደሚያደርጉ አምነው ነው የተለያየነው:: በዚያው መጠን ይህን ያህል ህዝብ መውጣቱ ለፀጥታ ኃይሎች አስቸጋሪ ነው ብለው የሰልፉን መካሄድ ተቃውመው የነበሩ ኮሚሽነሮች አሉ:: ለምሳሌ፡- የፌደራል ፖሊስ ዋናው ኮሚሽነር ዓርብ ዕለት በመስቀል አደባባይ ጋዜጣዊ መግለጫ ስንሰጥ በቦታው ተገኝቶ ሲታዘብ ነበር፤ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የተቻላቸውን ሲያደርጉ እንደነበር አይቻለሁ:: በሌላ መልኩ በሰልፉ መካሄድ ደስተኛ ያልሆኑ ወገኖችም አሉ::

በዕለቱ ሰልፉ ላይ ምንም ዓይነት ረብሻ እንዳይኖር ለፌደራል መንገድ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰልፉ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትኛውም ዓይነት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲቋረጥ ጠይቀናል:: ፌዴራል ፖሊስም ደብዳቤ ጽፏል:: በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወስድ በደብዳቤ ጠይቀን ተቀብለውናል:: የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አጠቃላይ ትራንስፖርት እንዲቋረጥ መመሪያ መላክ ነበረበት፤ ያ አልሆነም:: እንዳየሁት ባቡር በአናታችን ላይ እንደልብ ሲንቀሳቀስ ነበር:: እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለጠ/ሚኒስትሩም ሆነ ለሕዝቡ ደህንነት በጣም አሥጊ መሆኑ ይታወቃል::

በዕለቱ ግጭት ለመፍጠር በቅንጅት የተሠራ ነገር እንደነበር ያሳያል:: እኛ ጠዋት 12 ሰዓት ወደ መድረኩ ስንገባ አይገባም ተብለን ተከልክለን ሳለ፤ ያ ቦንብ ጭኖ የነበረው መኪና ግን እንዲገባ ተፈቅዶለታል:: ሆን ተብሎ የሸብር ሥራ ሲሠራ እንደነበር መገመት ይቻላል:: ህዝቡ ከፀጥታው አባላት ብዛት ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ በተመሳሳይ የፀጥታ ዘርፍ ላይ ያሉ አካላትን በዕለቱ ከፖሊስ ጋር ማዋሐድ ያስፈልግ ነበር:: ሆኖም ግን፣ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የፀጥታ ዘርፍ ለደንብ አስከባሪዎች ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ስብሰባ ጠርቷል:: ሁሉም የፀጥታ አካል ለዚያ ቀን ተባብሮ ይሥራ እየተባለ የየካ ክ/ከተማ የፀጥታ ዘርፍ ደንብ አስከባሪዎችን በተመሳሳይ ሰዓት ስብሰባ ለምን ጠራ? ይሄ አሁንም በሕግ በኩል ሌላ ችግር እንዳለ ይጠቁማል::

ስለዚህ በዕለቱ አደጋው የደረሰው በፀጥታና ደህንነት ጉድለት ነው:: እሱ የተፈጠረው ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦና ተቀነባብሮ ነው:: ሁሉም ነገር ወደ ፊት በሕግ አካላት ግልጽ ይሆናል ብለን እንጠብቃለን::

**ግዮን፡- ጠቅላይ ሚኒስትሩን በአካል ስታገኛቸው ምን ነበር ያልሃቸው?**

**ስዩም**፡- (ሳቅ) … ያልኳቸው… ስዩም ተሾመ እባላለሁ፤ እንኳን ደህና መጡ፤ ስለመጡ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፤ …ነው ያልኳቸው:: እሳቸውም፣ በጨዋ ደንብ ቢሮክራሲ በሌለው ሁኔታ ፍፁም ሰው አክባሪነት በሚታይበት እውነተኛ ስሜት ጨብጠው፣ አመስግነው ተለያይተናል:: ደስ የሚል መንፈስ ነበረው::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን**

# “ሁለት ታጣቂዎች መድረኩ አካባቢ ከጠ/ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ጋር ተጋጭተዋል”

**ስንታየሁ ቸኮል**


**ግዮን፡- ቅዳሜ፣ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. የተካሄደውን የድጋፍ ሰልፍ ያዘጋጀው ኮሚቴ በምን ሁኔታ ነው የተሰባሰበው?**



**ስንታየሁ**፡- በጥቂት ለውጥ ፈላጊ ግለሰቦች ተነሳሽነት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው:: ብዙዎቻችን ስንታሰር የነበርን፤ ከሥርዓቱ ጋር ስንታገል የቆየንና ከሥርዓቱ ጋር የሐሳብ ልዩነት ያለን ሰዎች ነን:: እስካሁን ድረስ የተቃውሞ ሰልፍ ነው ሲደረግ የነበረው፤ የአሁኑ ግን የድጋፍ ሰልፍ ነው:: ይህንን ሐሳብ ይዘው የመጡትና ወደ ተግባር የለወጡት ደግሞ ፖለቲካዊ የሐሳብ ልዩነት ያላቸው መሆኑ በራሱ ፕሮግራሙን ታሪካዊ ከማድረግ ባሻገር አስገራሚ ያደርገዋል::

የህወሓት መንግሥት ሥልጣኑን ከተነጠቀ በኂላ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን በመቃወም ከጀመሩት የኢትዮጵያዊነት መንገድ አስፈንጥሮ ለመጣል የአማራ ተወላጆችን በተለያዩ አከባቢዎች በማፈናቀል፣ በደቡብ እና በሱማሌ ክልል ግጭት በመፍጠር ያዘጋጁት ሴራ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሠርቶላቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ሰልፎችን በየክልሎቻቸው እያካሄዱ ጠ/ሚኒስትሩ ላይ ጫና ለማሳደርና ችግሩን ለማባባስ ቀን ከሌሊት በመባዘን ላይ ናቸው:: ይህ የድጋፍ ሰልፍ እንዲካሄድ በዋናነት ያስገደደው ይህ ነው::

እኚህን ጠ/ሚኒስትር በመደገፍ ሰላማዊ ትግሉ የበለጠ ስኬታማ እንዲሆን ያስፈልጋል:: ሰላማዊ ትግል ማለት በውጭ ብቻ የምናገኘው ትግል ሳይሆን በውስጥም በኩል የምናገኘው ትግል ድምር ውጤት ነው:: ሁለቱንም አብረን መጠቀም መቻል አለብን ብለን ስንነሣ ትልልቅ ሚዲያዎች ሳይቀሩ ሐሳቡን በመደገፍና ሼር በማድረግ በሶሻል ሚዲያ ተቀባበሉት:: በዚህ መሰረት በአጭር ቀናት ውስጥ ከእነ አቤ ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ኮሚቴ አቋቋምን:: በኂላ ሌሎች ወገኖችም በዚህ መንገድ ለመንቀሳቀስ መሞከራቸውን የሚገልፅ





መረጃ በማግኘታችን ሐሳቡ የሚበረታታ ነውና አንድ ላይ ከእነርሱ ጋር በመዋሐድ ኮሚቴው ሰልፉን ለማካሄድ በቅቷል::

**ግዮን፡- የድጋፍ ሰልፉ ከዚህ በፊት ከታዩ ሰላማዊ የሕዝብ ሰልፎች በምን ይለያል ትላለህ?**

**ስንታየሁ፡-** ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ያስጠበቀ፤ በታሪክም ታይቶ የማይታወቅ፤ የተለያዩ ጫፍና ጫፍ የቆሙ አስተሳሰቦች በአንድ ላይ ለአንድ ሀገር የዘመሩበት ቀን ነው:: በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከ27 ዓመት በፊት ባልነበረ መልኩ በመለስና በጓደኞቹ የመጣብንን የዘረኝነት ፖለቲካ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳይሠራ ሆኖ መቃብር የገባበት ታሪካዊ ሰልፍ ነው:: ይኼ ሰልፍ እንዲህ ባለ መልኩ ስኬታማ የሆነው በቅንነት ስለተነሳን ነው:: ሕዝብም በቅንነት ከጎናችን ሆኖ ህዝባዊ አንድነቱን አሳይቷል::

እንደምታውቁት ይህን ሰልፍ እኛ ይፋ ስናደርገው ምንም ነገር ይዘን አይደለም:: የማስተባበር አቅሙ በተወሰነ ደረጃ ጉድለት ነበረው፤ የፋይናንስ አቅምም አልነበረንም:: ይህንን ጉድለታችንን የሚሸፍንልንና አቅም የሚጨምርልን ህዝባችን ነው የሚል እምነት ስለነበረን ሰልፉ ተሳካልን:: በፈረንሳይ ለጋሲዮንና በሽሮ ሜዳ አካባቢ እኛ አይደለንም ሰልፉን የጀመርነው:: ራሳቸው ጀመሩ፤ ራሳቸው ጨረሱት:: ቲሸርትና ባነር በማሳተም፣ የመኪና ቅስቀሳ በማድረግ፣ ሕዝቡን በማስተባበር ሰውን አሰልፈው ይዘው የመጡት ራሳቸው ናቸው፤ እኛ መንገዱን ብቻ ነው የቀደድንላቸው::

**ግዮን፡- በዕለቱ ጠ/ሚኒስትሩ ወደ ሰልፍ ቦታው ሲመጡ የነበረውን ድባብ አስታውሰን እስቲ?**

**ስንታየሁ፡-** ለዚህ ሰልፍ አጠቃላይ የማስተባበሩን፣ አክቲቪስቶችን የማደራጀትና ሚዲያውን የማስተባበር ሥራ ለተከታታይ ቀናት ስንፈፅም ስለነበር ከፍተኛ ድካም ተሰምቶኛል:: በዋዜማው ምሽት ላይ ወደ ቤት ሄጄ ትንሽ አርፌ ነበር:: ሰዎች ግን ሌሊት ላይ ደውለው ሰልፉ ስድስት ሰዓት ተጀምሯል፤ ህዝብ በብዛት ወደ መስቀል አደባባይ እየጎረፈ ነው ብለውኛል:: እኛ ጠዋት ከአንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ሰባት ሰዓት በተሰጠን ፈቃድ ነው ሰልፉን የጠራነው:: ዴሞክራሲና ነፃነት የተራበው ሕዝብ ግን እስኪነጋ ትዕግስት አጣ::

ይህ ህዝባችን በኢ-ፍትሐዊነት እንደተሰቃየ ያረጋግጣል:: ሰው ከሌሊት ጀምሮ መፈክር ይዞ ነው ያደረው:: ከአንድ ሰዓት በፊት በመስቀል አደባባይ ቦታ አልነበረም:: ከአንድ ሰዓት በኋላ የመጣውን ህዝብ ግን ልንቆጣጠረው አልቻልንም:: ከደቂቃ ደቂቃ እየጨመረ ነው የመጣው:: በዚህም የተነሣ ጠ/ሚኒስትሩ ይመጣሉ ተብሎ ከታሰበበት ሰዓት አስቀድመው እንዲመጡ ለሚመለከተው አካል ደውለናል:: በዚያ ሁኔታ ጠ/ሚኒስትሩ በጊዜ መጥተው ንግግራቸውን አድርገው ከጨረሱ በኋላ ያልታሰበ ክስተት ነው የተፈጠረው:: ህዝቡ ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ ነው የተቀበላቸው:: ሰልፉ ለእሳቸውም፣ ለአዘጋጅ ኮሚቴውም፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብም ታሪካዊ ሆኖ ነው ያለቀው::

**ግዮን፡- ወደ አደጋው ሰዓት እንመለስ፤ ምን ተሰማህ?**

**ስንታየሁ፡-** ሁለት የታጠቁ ሰዎች ጠ/ሚኒስትሩና ካቢኔያቸው በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ከተቀመጡ በኋላ መድረኩ ላይ መግባት አለብን እያሉ ከጠ/ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ጋር ይጋጩ ነበር:: "ታጥቃችሁ አትገቡም" ሲሏቸው፤ "የጥበቃ አባል ነን" የሚል ምላሽ ይሰጧቸዋል:: እነሱም "እስኪ መታወቂያ አሳዩን" ሲሉ የሰጧቸው መልስ ስለሌለ የግል ጠባቂዎቹ ተከላክለው መልሰዋቸዋል:: ሁኔታውን በግልፅ ቦታው ላይ ስለነበርኩ ለመታዘብ ችያለሁ:: አደጋው ሆን ተብሎ ለጠ/ሚኒስትሩ የተሸረበና የተዘጋጀ፤ እሳቸው እንዳሉት በሙያ የታገዘና ጥቅማችን ጎደለ በሚሉ ኃይሎች የተቀነባበረ እንደሆነ ግልፅ ነው::

በሰዓቱ ሆን ተብሎ ህዝብን ለመረበሽ ከሌላ ህንፃ ላይ የተለየ ድምጽ እንዲገባ ይደረግ ነበር:: የሕወሐት ካድሬዎች ሕዝብ አንቀበለውም የሚለውን ጀንያ ሙሉ ኮከብ ያለበት ባንዲራ ህዝቡ ውስጥ ሆን ብለው ይበትኑ ነበር:: የጥበቃ ሴኩሪቲዎች አንድ መኪና ለይተው "የፖሊስ ናት" በሚል መድረኩ አካባቢ አስገብተዋል:: ጥበቃና ቁጥጥሩ የላላ እንዲሆን ተደርጓል:: ሰዎች የተለየ እቃ ይዘው ሲገቡ "ተዋቸው ይግቡ" ይሉ ነበር:: እኛ እንደ አዘጋጅ ኮሚቴ በሰዓቱ ብናሳስብም ምንም የተቀየረ ነገር አልነበረም::

**ግዮን፡- አደጋው ከደረሰ በኋላ በተጎጂዎች ዘንድ ያለው ስሜት ምን ይመስል ነበር?**

**ስንታየሁ፡-** ሁሉም የራሳቸውን ጉዳት ረስተው ጠ/ሚኒስትሩ እንኳን ተረፉ ነበር የሚሉት:: "መሥዋዕት የሆንነው ለሠላምና ለፍቅር ለሚደክሙ መሪ ነው" ብለውናል:: ህዝቡን የጭቆናው ሁኔታ ምን ዓይነት ሁኔታ አድርሶት እንደነበር የተጎጂዎች ሞራላዊ ጥንካሬ ያረጋግጣል:: ብዙዎች ያለሙትን ተስፋ ነው ያዩት:: እነዚህ ንፁሕ ዜጎች ሁሌም በታሪክ የሚዘከሩ ናቸው::

ጠ/ሚኒስትሩም ምሽቱን በሆስፒታሎች በመገኘት ተጎጅዎችን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል:: ደም ለግሰዋል:: በማግስቱ ለአስተባባሪ ኮሚቴው ጊዜያዊ ሊቀ መንበር ለአቶ ጉደታ ገላልቻ ስልክ በመደወል አዘጋጆችን በሙሉ አመስግነዋል:: ይህ በራሱ ትልቅ ነገር ነው::

**ግዮን፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "ለተጎጂዎች 10 ሚሊዮን ብር መድቤያለሁ፤ የዕርዳታ አካውንትም አቋቁሜያለሁ" ብሏል:: ከዚህ በፊት በዚህ መልክ ገንዘብ ያሰባሰበው መስተዳድሩ፣ በቆሼ የተጎዱ ወገኖችን በአግባቡ ባለመርዳቱ ተጎጅዎችን ክፉኛ አስለቅሷል፤ አሁንም ተመሳሳይ ነገር እንዳይደረግ ምን ለመሥራት አስባችኋል?**

**ስንታየሁ፡-** መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ሰዎችም እየተባበሩን ነው፤ በዚህ የድጋፍ ሰልፍ ላይ የተጎዱ ወገኖችን በተመለከተ፣ በዋናነት የሚመለከተው ይህ አዘጋጅ ኮሚቴ ነው:: ይህን ኮሚቴ ባላማከረበት ሁኔታ፣ አ/አ መስተዳድር 10 ሚሊዮን መድቤያለሁ ማለቱ ሰብአዊነት ከሆነ ሚዛን ይደፋል:: ሲደግፍ ግን ከጉዳዩ አጀንዳ ባለቤቶች ጋር ነው መሥራት ያለበት:: ከዚህ በፊት በታየው ልምድ ቆሼ ላይ የተጎዱ ሰዎች በስማቸው ተነግዶ ሜዳ ላይ ወድቀዋል:: የተረዱት ጥቂቶች ብቻ ናቸው:: ከዚያ በመነሣት በመንግሥት አሠራር በኩል ክፍተት ስላለ እነሱን በደብዳቤ እንጠይቃለን:: በተጎጂዎች ዙርያ በቂ መረጃ እንሰባሰባለን:: ሕጋዊ አካውንት ተከፍቶ እርዳታው ይሰበሰባል:: በመጨረሻም፣ ለሚመለከታቸው ሰዎች ግልጽ በሆነና ህዝብ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በሚያውቅበት መልኩ እናስረዳለን:: ይህ በቅርቡ ይፋ ይሆናል::

**ግዮን፡- አመሰግናለሁ::**

**ግዮን፡- የሰልፉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዴት ነበር የተሰባሰባችሁት?**

**አበበ፡-** መጀመሪያ ላይ የተለያዩ ሰዎች አሁን ያለውን የሀገሪቱን እንቅስቃሴ ለውጥ ህዝብ እንዴት ባለ መልኩ ነው ሊገልጽ የሚችለው እያልን በግለሰብ ደረጃ እንነጋገር ነበር፤ ሁሌም እየተገናኘን ኢህአዴግ ውስጥ ያለውን ክፍፍል እንገመግም ነበር:: በጠ/ሚኒስትር ዐቢይና በሌሎች የኢህአዴግ ሰዎች መካከል የስትራቴጂ ልዩነት ነው ያለው:: አንዳንዴም የፖሊሲና የአስተሳሰብ ልዩነት ይታያል:: ጠ/ሚኒስትሩም ኢህአዴግ ውስጥ ቢሆኑም የተለየና ለሕዝብ የሚጠቅም አስተሳሰብ ይዘው ሊመጡ እንደሚችሉና ኢህአዴግንም በመቀየር ለኢትዮጵያ በሚጠቅም የአሠራር መንገድ ለውጡን ሊያመጡት ይችላሉ የሚል እምነት በመያዛችን የድጋፍ ሰልፍ ለማድረግ አሰብን::

ሌላኛው ወገን ደግሞ ይህንን ለለውጥ የተነሣውን ኃይል በተለየ መንገድ አጥቅቶ እንዳያጠፋው እሳቸውን በመደገፍ አጋርነታችንን ለማሳየት ነው የተሰበሰብነው:: የአስተሳሰብ ልዩነት ቢኖረንም የጠ/ሚኒስትሩ አካሄድ ግን የግድ የሕዝብ ድጋፍ ሰልፍ እንደሚያስፈልገው አምነንበታል:: መሪ ሲለወጥ ነው ድርጅት የሚለወጠው፤ የተለወጠ መሪን ማመስገን መልመድ አለብን::

**ግዮን፡- ሰልፉ በታሪክ ትልቅ መሆኑ በግልጽ ታይቷል፤ መጀመሪያ ወደ እንቅስቃሴ ስትገቡ ይህ ይሆናል ብላችሁ ገምታችሁ ነበር?**

**አበበ፡-** እኛ ሰልፉን ለማካሄድ አስበን እንቅስቃሴ ስንጀምር የተለያዩ ሀሳቦች በነፃነት የሚስተናገዱበት እንዲሆን ፍላጎት ነበረን:: ከዚህ በፊት በተካሄዱ ሰልፎች የጠሪው አካል እሳቤና ፍላጎት ብቻ እንዲንፀባረቅ ነበር የሚደረገው:: "አንተ ይህንን ዓርማ ያዝ፤ አንተ ያኛውን ሰንደቅ ዓላማ አውርድ" የሚባል ነገር ነበርና ከዚህ በተለየ በዕለቱ ኢትዮጵያውያን አንድ ላይ አሉን የምንላቸውን አጀንዳዎች ይዘን አደባባይ እንውጣ፤ እንጋጫለን አንጋጭም የሚለውም ነገር ግልጽ የሚሆንበት አጋጣሚ ነው ብለን አምነናል::

እውነት እስከዛሬ የሚያጋጨን የሐሳብ ልዩነት ነው ወይስ መሪዎች ናቸው የሚያጋጩን የሚለው ጥያቄ ቅዳሜ መልስ አግኝቷል:: ሰልፉ ፈፅሞ ከጠበቅነው በላይ ነው:: በሰልፉ ላይ ከብርሀኑ ነጋ እስከ ተመስገን ደሳለኝ ድረስ ሁሉም የፈለገውን ፎቶ ይዞ ወጥቷል:: የእኛ ሰንደቅ ዓላማ፣ ኢህአዴግ የእኔ ነው የሚለው፣ የኦነግ፣ የገዳ ሰንደቅ ዓላማዎች ሁሉም በአደባባይ ሲንፀባረቁ ህዝባችን አንዱንም አውርድ ሳይል ሰልፉ መካሄዱ እስካሁን ድረስ ያለው ችግር የሕዝብ አለመሆኑ ተረጋግጧል::

በመጀመሪያም ኢትዮጵያን የመገነጣጠል አጀንዳ የህዝብ አይደለም:: ሁለተኛ የዚህ ትውልድ አጀንዳ አለመሆኑ ተረጋግጧል:: ያ ትውልድ ከሩሲያ የተበደረው የስታሊን አጀንዳ ነው:: እኛ በስታሊን አጀንዳ ከአርባ ዓመት በላይ ስንታመስ ኖረናል:: በሕገ መንግሥት ጭምር በአንቀጽ 39 ተቀምጦ "መገንጠልን ይጠይቃል፤ መገንጠልን አይጠይቅም" የተባለው ህዝብ አንድ ላይ ሆኖ ቃል ኪዳን ሲገባ ቅዳሜ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነው:: ሁለተኛው በታሪካችን መሪ አመስግነን አናውቅም:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ያመሰገንነው ነቢይ ወይም ጻድቅ ስለሆነ አይደለም:: መልአክ ሆኖም አይደለም:: በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ህዝብ የሚፈልጋቸውን ነገሮች



# “የሐሳብ ልዩነቶች ሳይሆኑ፣ መሪዎች እንደሚያጋጩን ቅዳሜ ተረጋግጧል”

*ክንፈ ሚካኤል ደበበን (አበበ ቀስቶ)*

ስለሚናገሩና ያንን ለመተግበር ስለጣሩ ነው:: ለዚህ ጥረታቸውና በውስጣቸው ያለውን ጠላት ለማሸነፍ የሚችሉት ህዝብ ድጋፉን በአደባባይ ሲገልፅላቸው በመሆኑ ያንን በእኛ በኩል አድርገናል::

በዕለቱ አርበኞች ሳይቀሩ ኮከብ የሌለውን ሰንደቅ ዓላማ ወደ መድረክ ይዘው ወጥተው ሲያሳዩ፤ መሪው ተዉ እንኳን ሳይል ሁሉን ነገር እያየ፤ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የውህደት መልዕክት አስተላልፈዋል:: አንድም ጊዜ የብሔር ነገር ሳይነሣ እርቅና መቻቻል አስተምሮ በዚያው መጠን እውነተኛ ፍቅርንና ክብርን ከህዝብ ተምሮ የወረደበት አጋጣሚ በመሆኑ በጣም ደስ ብሎናል::

**ግዮን፡- ሰኔ 16 የፍቅርና የነፃነት ቀን እንዲሆን በስፋት እየተወራ ነው፤ እናንተ ይህን ነገር በብሔራዊ ደረጃ ለማስወሰን ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አበበ**፡- እንደአዘጋጅ ኮሚቴነታችን በዚህ ጉዳይ ላይ መክረናል:: በመጀመሪያ ደረጃ ለተወካዮች ም/ቤት፣ ለፌደሬሽን ም/ቤት፣ ለጠ/ሚኒስቴር ጽ/ቤት ቀኑ ብሔራዊ በዓል እንዲሆንና ይህ ታሪካዊ ቀን በመላ ኢትዮጵያ ፍቅር፣ መቻቻል፣ አንድነት የሚሰበክበት ሆኖ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከበር ጥሪያችንን እናቀርባለን:: በእኛ በኩል ሐሳቡ አለ::

በሌላ በኩል፣ ጠ/ሚኒስቴር ቢሮ ቀኑ ብሔራዊ በዓል እንዲሆን መወሰኑን ሰምተናል:: ወደ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአጭር ቀን ውስጥ ቀርቦ፣ ታውጆ ይከበራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: ኢትዮጵያ ሌላ ግንቦት ሃያ የሚባል በዓል አያስፈልጋትም:: ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ሌላ የፍቅር በዓል ነው:: ይህ የነፃነታችን ቀን ነው:: ወዳጅ ዘመድ ስጦታ የሚለዋወጥበትና እንኳን አደረሰህ የሚባባልበት የፍቅር ቀን ሆኖ ቢከበር ደስ ይለናል:: ይኼ የየትኛውም ፓርቲ የድል በዓል አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን፣ አንድነቱንና ፍቅሩን ለዘላለም ለማስጠበቅ በጋራ ያካሄደው ሰልፍ ነው::

በተጨማሪ ይህ ዕለት ሁልጊዜ በጭፈራና በደስታ ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያውያን ደም የሚሰጣጡበት፤ ልክ በዚያ ቀን በዓሉ ሲከበር በሁሉም ከተሞች ላይ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ አንድ አንድ ብር ቢያዋጣ ለበጎ አድራጎት ሥራ ይውላል ብለን እናስባለን:: ጠ/ሚኒስትሩ ግን አስቀድመው የእኛን ሐሳብ ወደ ብሔራዊ በዓል በመቀየራቸው በጣም ልናመሰግናቸው እንወዳለን::

**ግዮን፡- ብዙ ጊዜ በዚህ መንግሥት ታስረሃል:: ከሰባት ዓመት እስር በኋላ ከወራት በፊት ነው የተፈታኸው:: ከኢህአዴግ መካከል እንዲህ ዓይነት የሀገርና የወገን ተቆርቋሪ ሰው ይወጣል ብለህ ታስብ ነበር?**



**አበበ**፡- እስር ቤት ውስጥ እያለን የለማና የገዱ ቡድን ውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሆነ እናውቃለን:: ያኔ ነባሮችን በጥርጣሬ እንወያይባቸው ነበር፤ ነገር ግን የዓለም ተሞክሮ የሚያሳየው አምባገነን መሪዎች ዕድሜ ልክ ለመንገሥ በሚያስቡበት ሀገር ከሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከመሪም ይመጣል:: ለምሳሌ ሩሲያ ውስጥ ወደ ዴሞክራሲ ለመሄድ በር የከፈቱት የኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎች ጎርባቾብና ቦሪስ ሄልሲን ናቸው:: ወደ ምሥራቅ ጀርመን ስትመጣ የበርሊን ግምብ የፈረሰው ኤሪክ ኤከርን ያወረደው ኮሚኒስት ፓርቲው ነው:: ከዚያ በኋላ ነው ጀርመን የምትባለው ሀገር በውህደት የተፈጠረችው::

አሁንም ኢህአዴግ ውስጥ ለውጥ የመጣው ውስጡ ያለው መሪ ትንሽ ሰከን ያለና ሀገራዊ ፍቅር ያለው በመሆኑ እንደሆነ ይታመናል:: ስለዚህ ይህ ሰው ድጋፍ ብንሰጠው እንኳን ኢትዮጵያን፤ የተለየችንን ኤርትራን ያዋህዳል ብለን ተስፋ አድርገናል:: መሪ የመሆን ፍላጎት ካለህ ትረበሽ ይሆናል፤ ነገር ግን ሀገሪቱን የመገንባት ዕድል ሳያመልጠን ልንጠቀምበት ይገባል ብለን እናምናለን:: በየትኛውም አምባገነን ሥርዓት ለውጥ ከውስጥ ይመነጫል::

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ለውጡን ብቻቸውን ያመጡታል ብለን አናስብም:: ሁላችንም የየድርሻችንን መወጣት አለብን:: ምርጫ እስከሚደርስ፣ ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ ጠ/ሚኒስትሩን በመደገፍ ፖዘቲቭ ሕጎች እንዲሻሻሉና ጠማማ ሕጎች እንዲቀየሩ ብናደርግ ውጤታማ እንሆናለን ብዬ ስለማስብ ነው ማድረግ ያለብኝን ያደረግኩት::

**ግዮን፡- በዕለቱ የተከሰተው አደጋ ከመነሻው ጀምሮ ምን ዓይነት ገጽታ ነበረው?**

**አበበ**፡- እኔ በሕይወቴ እንዲህ አይነት ንዝህላል የደህንነት ጥበቃ አይቼ አላውቅም:: ለምሳሌ እኛ ሰልፉን የጠራነው ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ነው:: አደባባዩ ላይ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ጀምሮ ሰው ነበር:: በዚያ ሰዓት ጥበቃዎች አካባቢው ላይ አልነበሩም፤ ማንም የፈለገውን ሊያደርግ ይችላል:: ዐሥር ሰዓት ላይ መድረኩ እንኳን በአግባቡ በፀጥታ ኃይሎች እየተጠበቀ አልነበረም:: ሌሊት ወታደሮች መድረክ ላይ ወጥተው ሲፈትሹ ብርድ ልብስ ለብሰው የተኙ ሰዎች ነበሩ:: መሪ የሚቀመጥበት ቦታ ላይ አራት ሰው ተኝቶ በዓይኔ አይቻለሁ::


የይለፍ ወረቀት እያለን መኪናችን አትገባም በመባሏ ፍንፍኔ ጋር ነው ያቆምናት፤ ያቺን የፖሊስ መኪና ለምን ገባች ብሎ የጠየቀ አንድም የፀጥታ አካል የለም:: ሁለተኛ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች እዚያም እዚያም ይታዩ ነበር፤ ይህንን ምርመራው ለሚያካሂደው አካል እንተወውና በእኔ ግምት የደህንነቱና የፀጥታው ችግር በቀድሞ ቅሪቶች የታሰበ ይመስለኛል:: የእሳቸው ጠላት ውስጣቸው ያለው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም:: የውስጥ ተሸናፊው ኃይል በሆነ አጋጣሚ እንዳያጠፋቸው ራሳቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ባህል አምጥቷል:: ፈንጂ ወደፈነዳበት ቦታ በመሄድ መሪውን ሲታደግ ተመልክተናል:: ጠ/ሚኒስትሩን ዐቢይ ዐቢይ እያለ ቤተ መንግሥት አስገብቷቸው የተመለሰ ወጣት ዐይተናል:: ም/ጠ/ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንን ህዝብ ነው ተሸክሞ መኪና ውስጥ ያስገባቸው:: አቶ ደመቀ ከዚህ በፊት የነበራቸው ስምና አሁን ሕዝብ እንዳይጎዱ ተሸክሞ መኪናው ውስጥ ሲከታቸው ማየት ለውጡ የሕዝብ ጭምር እንደሆነ ያሳያል:: ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይጠብቃታል የሚለው ነገር በዕለቱ በገሃድ ታይቷል::

**ግዮን፡- ይህን ሰልፍ ስታካሄዱ ከፍተኛ ገንዘብ ከተለያዩ ግለሰቦች በበጎ ፈቃደኝነት ተበርክቶላቸዋል የሚባል ነገር አለ፤ በዚህ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?**

**አበበ**፡- ይህ ኮሚቴ ከገንዘብ ጋር ፈጽሞ አልተነካካም:: አንዳንድ ወጪዎችን ለመሸፈን፤ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ ግለሰቦች ድጋፍ አድርገዋል:: ለምሳሌ፡- ኢሌሌ ሆቴል ፕሮቶኮሉን የጠበቀ አዳራሽ በመፍቀድ ባሻገር፤ ጽ/ቤትም እንድንጠቀም አድርጎናል:: በሌላ መንገድ ለተለያዩ ወጪዎች የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሸፍነውልናል:: በገንዘብ ደረጃ ገንዘቡን ሲቀበል የነበረ ሌላ አካል ነው:: እያንዳንዱን ወጪ መዝግቧል፤ ምን ያህል ተሰበሰበ ምን ያህል ወጣ የሚለውን ኦዲት አድርገን በቅርቡ ይፋ እናደርጋለን:: በነገራችን ላይ ይህ ኮሚቴ ሰልፉን በተዋጣ መንገድ ለማካሄድ የቻለው ከገንዘብ ንክኪ ነፃ ስለሆነ ነው:: ለዚህ ሐላፊነት የሰጠነው ሌላ ሰው አለ:: ሐቁ ግን በቅርብ ይገለፃል::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



ልዩ ዕትም

# መደመር ብቻ ለምን?



ሁሴን ከድር

በታሪክ የምንሰማው ካልሆነ በቀር እንደሰሞኑ አንድነት ታርቆን የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ እስከዛሬ በፕሮፓጋንዳ ይነዛ የነበረው የላንቲካው አንድነት አሁን የምር በሀገራችን ሕዝቦች ረብቦ ነው ያየነው፡፡ ያውም በራሱ ጎንቁሎ፣ አድጎና ጎምርቶ የታየ አንድነት፡፡ መልካም ነው፡፡ ለዓመታት ስንጮህለት የነበረ ሕብረት በመሆኑ በተለይ በጠ/ሚ ዐቢይ አማካይነት መምጣቱ፤ "ለውጡ የምር እንደሆነ" ለማመን እየዳዳን ነው፡፡ ቦታውን የያዙት ነባር ታጋዮች ሆነው ቢሆን ኖሮ መች የሆድ የሆዳችንን ባወራን፡፡

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሕግ ጥሰት የደረሰባቸውን ከየቦታው እየፈለፈለ ማቅረብ ጀምሯል፡፡ በተለይም በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሕግ ጥሰት ተፈጽሞብናል፤ በሕግ ቁጥጥር ውስጥ ሆነንም ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እየተፈጸመብን ነው፡፡ ይኸው የዘር ፍሬያችን ተኮላሽቷል፤ ይኸው የአጥንት መሰበር እንዲደርስብን ተደርገናል፤ ይኸው የሰውነታችን ጠባሳ፣ የሥነ ልቦናችን መሰበር ...ወዘተ ብለው የሚናገሩ ግፉዓንን እያቀረቡ፤ "አይዟችሁ ተናገሩ" በሚል እያደፋፈሩ ለሕዝብ ይፋ እያደረጉ ነው፡፡ ከሣምንት በፊትም በአፉታ (ይቅርታ) የተለቀቁ ታራሚዎችን የእስር ቤት አያያዝን እንዲናገሩ በማስደረግ የኢትዮጵያን የወሕኒ ቤት ገመና አጋልጠው የሹክሹክታውን አፈንድተውት ነበር፡፡ በርግጥ "ይህ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነው ወይስ ኢሳት?" ብለን እስከመጠርጠርም አድርሶን ነበር፡፡

"የሞተ ተጎዳ፤ መሰንበት ደግ ነው" እንዲሉ በመኖር ብዙ ዐይተናል፡፡ አላህ ካለ ወደፊትም እናያለን፡፡

"ከትከት ብላ ሳቀች ዓለም ጥርስ አውጥታ፤
አሳሪው ሲታሰር ታሳሪው ሲፈታ" አሉ፡፡

ባለሥልጣናት ወደውም ሆነ ተገደው ከወንበራቸው እየተፈነገሉ ነው፡፡ በተለይም የመደመር እንቅፋት የሆኑት ቀድሞም ዐቢይን ሲያሰናክሉ የነበሩ የራሱ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት "ወደን ፈቅደን ነው" በሚል ሸፋን ክብራቸውን ከላያቸው ላይ አውልቀው እያስቀመጡ ከደረጃቸው እየተንከባለሉ ነው፡፡ በተለይም የአዋሳው በአንድ ብሔር ላይ የተነጣጠረና በኢትዮጵያ ታሪክ ያልተመዘገበ አንድን ብሔር የማጥቃት እኩይ ተግባር በርካታ የኢህአዴግ ሹሞችን እንዲረመረሙ አድርጓቸዋል፡፡ ባለፉት ሁለት ወራት በወልቂጤ የተፈጠረው የቀቤናና የጉራጌ ብሔረሰብ ግጭት ዐቢይን ከተፈታተኑ ጉዳዮች አንዱ ነበር፡፡ በጥበብና በአርቆ አስተዋይነት ፈታው እንጂ፡፡

የዐቢይ ጠላቶች በየቦታው የጫሩት እሳት ሳያንስ፣ ከደርግ ዘመን ጀምሮ ሰላማዊ ሰልፎች ሲደረጉ አንድም ጊዜ የቦንብ አደጋን ያላስተናገደው አብዮት አደባባይ፣ ዐቢይን ለመግደል በታቀደ የቦንብ ውርወራ ሁለት ሰዎች ሲሞቱ በርካቶች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል፡፡ ይህ ድርጊት ብዙዎችን ያስደነገጠ፣ምናልባትም ዐቢይንም ጭምር "ከዚህ በላይ መጋለጥ ቀላል ያልሆነ ዋጋ ያስከፍላል" ያስባለው ይመስላል፡፡ ይህም ሆኖ ከሕዝባዊነቱ ሸርተት አላለም፡፡

ተቃዋሚ ተብለው የተፈረጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ተደምረው ከመቃረን ወደ መጣመር እየተሸጋገሩ ነው፡፡ ትናንት በሽብር፣ በሀገር ክህደት ወንጀል፣ በአክራሪነት ይጠረጠሩ የነበሩ ተቃዋሚ የተባሉ ፓርቲዎች፤ ጦረኞች ጦራቸውን እንዲያስቀምጡ፣ ጠይዎችም ጥላቻቸውን ገፍፈው እንዲደመሩ በር ተከፍቶላቸዋል፡፡ በዚህም ከ25 ዓመት በላይ ጠላት ተደርጎ የነበረው ኦነግ በተከፈተው በር ኮራ ብሎ ገብቷል፤ አርበኞች ግንቦት ሠባትም ጥሪውን ተቀብያለሁ ብሏል፡፡ በዚህ መሃል የይስሙላ ተቃዋሚዎችም (በኢህአዴግ የተሠሩ Made in EPRDF) ራሳቸውን በተቃዋሚነት በመጠርጠር የመደመሩ አካል ለመሆን ሲፍጨረጨሩ ይታያሉ፡፡ ጊዜው "የሾላ በድፍኑ..." በመሆኑ እንዲደመሩ ተደርገዋል፡፡

ከሁሉ በላይ "ሌቦች ሲሰርቁ ተዋድደው፣ ሲካፈሉ ይጣላሉ" ተብለው የተተረተባቸው ‹‹የህወሓትና የሻእቢያ ጥላቻ ይሰረዝ፤ ኤርትራም ከኢትዮጵያ ትደመር" በሚል የሰላም እጅ ተዘርግቶላታል፡፡ እሷም የተዘረጋላትን እጅ ሳትገፉ፣ ጥሪውን ተቀብላ ልኡካኗን ወደ አዲስ አበባ ልካለች፡፡ ለዓመታት ተንጠልጥሎ የቆየው የባድመ ጥያቄም በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሰረት እልባት ያግኝ በማለት ውሳኔው ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የህወሓት ጎምቱዎች ግን ከሻእቢያ ጋር የሚደረገው መደመር ከብዷቸው አፍንጫቸውን ነፍተው በተዓብዮ ኩርፍ ብለው መዳፉን እንደሚተመትም ዕቡይ ፈንጠር ብለው እያጥላሉ ይታያሉ፡፡ ጥላቻዋ ግን ገፍታ አልወጣችም፡፡ ምልክቷ ቢሆን እንጂ፡፡

በዚህ ሁሉ ለውጥ ያልተደሰቱ በየተቋሙ፣ በተለይም በህወሓትና በደቡብ ሥር የተሰገሰጉ ጥቅመኛ የቀን ጅቦች ተቀጣጣይ የነገር ፈንጂዎችን እየቀበሩ ይገኛሉ፡፡ ይህንንም ጀሌዎቻቸውን በየማኅበራዊ ዘዴ በመላክ በአግቦ፣ በሾርኔ፣ በአሽሙር እንዲተነፍሱ እያደረጓቸው ነው፡፡

ዛሬም የፌዴራል ፖሊስና የደህንነት ቢሮ ውስጥ የቀን ጅቦቹ አልተመነጠሩም፤ ዛሬም ከኢሚግሬሽን፣ከአየር መንገድ፣ ከተለያዩ ከፍተኛ የመንግሥት እርከኖች፤ ሆዳሞቹና የሀገር እንቅፋቶቹ አልተወገዱም፡፡ እያደር የተንኮል ድራቸውን እያደሩ ይገኛሉ፡፡

ለዘመናት በኢህአዴግ አስተዳደር ሲቆስል የነበረው ሰፊው ሕዝብ ለጥቂት ሳምንታት ዐቢይን በፍራቻና በተስፋ መካከል ሲያየው ቆይቶ፣ ከቦንብ ሙከራው በኋላ ግን ጥላቻውን በዐቢይ ጠላቶች ላይ በማድረግ ልቡን እየከፈተለት ይገኛል፡፡ ኢህአዴግን በሁለት ወራት ለውጥ ለማመን ይቸግራል የሚሉ አሉ፡፡ "የለም ለውጡ የሁለት ወር አይደለም፤ የሙስሊሙ የመብት ትግል እንቅስቃሴ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ የኢህአዴግን ኃይል ምልከታ ፈተና ላይ እንዲወድቅ የተደረገ በመሆኑ፣ ኢህአዴግ እየተሸረሸረ የመጣው ያኔ ነው፡፡ የውስጥ ለውስጥ ቅራኔ ተፈጥሯል" ይላሉ፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በ2006 ዓ.ም. ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ላሉ አመራሮች "ብኽርታ" ተፈጥሮባቸዋል "ማጥራት" ያስፈልጋል በሚል በኢህአዴግ ለካድሬዎቹ በተሰጠው ሥልጠና ሾልኮ በመግባት የታዘበውን በወቅቱ ትታተም በነበረችው "ዕንቊ" መጽሔት አስነብቦ ነበር፡፡ በጊዜው በኢህአዴግ የአዲስ አበባ ካድሬዎች ዘንድ በቃላት የመጎሻሸምና "መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ የመግባቱን ማስረጃ" ሲናቾፉበት ታዝቧል፡፡ በሙስሊሙ ንጠት (መናጥ) ቆሌው የተገፈፈው ኢህአዴግ ነገሩን በኃይል ለማርገብ የወሰደው እርምጃ ሌላ እሳት ጫረበት፡፡ የኦሮሚያ ጥያቄ የኢህአዴግን መሰነጣጠቅ እያሰፋው መጣ፡፡ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላም በሀገሪቱ የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ አድርጎ ዛሬ ኢህአዴግ በቀደመ ገጽታው፣በቆየ ግዝፈቱ፣ በነበረ ክብደቱ ተኮፍሶ አይታይም፡፡ እንደ ጸጉራም ውሻ ጸጉሩ ጎፍሮ፣ ውስጡ መንምኖ እየተወሸናከለ ከቶም አቅፎ ደግፎ ያሳደገውን ልጁን "ወጌን፣ ክብሬን፣ ተፈሪነቴን አስቀማኸኝ" በማለት እስከመገላመጥ እየደረሰ ነው፡፡

በሌላ ወገን ኢህአዴግ እድሜውን ማራዘሚያ አዲስ አካሄድን እየተከተለ ይገኛል፣ ይህም የመለስ ንድፍ ነው የሚሉም ጠርጣሪዎች ድምጻቸውን ያሰማሉ፡፡ ከ1997 ምርጫ ማግስት መለስ የነባር ታጋዮች በሙስና መንቀዝ፣ የብአዴንና የኦህዴድ ወደላይ መንጠራራት ፊቱን ወደ ደቡብ እንዲያዞር አድርጎት አጠገቡ ያስቀመጣቸው ደቡቦች የመለስን ዳግም ላይመለስ መሄድ ተገን አድርገው በተመቻቸው ወንበር እንዲቀመጡ፤ ኋላም ግራ የሚያጋባው ፕላን፣ ፕላነሩ ሲጠፉ በዘፈቀደ እንዲነበብ ተደርጎ ትርምስምሱ ለወጣ የኢህአዴግ (የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በክላስተር እንዲመሩ፤ በአንድ ሚኒስቴር አራት ሚኒስትር ዴኤታዎች እንዲኮለኮሉ መደረጉ) የፖለቲካ ውኽርንብር ፈጥሮ ነበር፡፡ እናም በዚህ መንገድ የተቀየሰው ፕላን ነው የኢህአዴግ ቀጣይ ጉዞ በወጣት አመራሮች ብሩህ የሆነው ይላሉ፡፡

የሆነው ሆኖ ኢህአዴግ ዛሬ የማይጎረብጥ ፓርቲ ሆኗል፡፡ ከውስጥ ጥቅማቸው የተነካባቸው ግለኞች ካልሆኑ በቀር በውጭ ኮናኞቹ በሙሉ የመደመር ፖለቲካ አቀንቃኝ በመሆን ቃሉን ሲደጋግሙ ይደመጣሉ፡፡ የወረት ፖለቲካ በሀገራችን የተለመደ በመሆኑ ብዙም ላይደንቅ ይችላል፡፡ በ1997 ዓ.ም. የሕዝብ መንፈስ ወደ ቅንጅት ተለውጦ ዛሬ ዐቢይን "ከሰማይ የተሰጠ ጸጋ ነው" እንደተባለው፤ ያኔ "ቅንጅት መንፈስ ነው" ተብሎ ተደልቆ ነበር፡፡

ይህች የመደመር ፖለቲካ በመደመር ብቻ መወሰኗ ለምን? ባይ ነኝ፡፡ መቀነሱ ይቅር መባዛቱም በሂደት ይመጣል ምነው መካፈሉ ወይም ማካፈሉ ላይ የማይበረታ? ከሰሞኑ "መደመር" የሚለው ቃል ከድግግሞሹ ብዛት የጎረበጣትን አንዲት ጉብል የቴሌቪዥን ተጠያቂ "እኔ የመጣሁት ለመቀነስ ነው" ማለቷን አንድ አድማጭ ነግሮኛል፡፡ "ጥላቻን ለመቀነስ፣ ምቀኝነትን ለመቀነስ፣ ክፋትን ለመቀነስ፣ስግብግብነትን ለመቀነስ...›› ጥሩ እይታ ነው፡፡

የመሪን ቃል እንደ በቀቀን እየደጋገሙ ማስተጋባት የመሪውም ፍላጎት አይሆንም፤ እድገትም አያመጣም፡፡ የቃሉን መሰረተ ሐሳብ ተረድቶ፣ ጽንሰ ሐሳቡን በመተርጎም ለተሻለ ተግባር መለወጡ ነው ብልህ የሚያሰኘው፡፡ ጠ/ሚ ዐቢይ "የኢህአዴግን ርዕዮት እስከተቀበለ ለምን የአራተኛ ክፍል ተማሪ አይሆንም፤ ይሾማል" የሚለውን አሮጌ፣ የጃጀና የበሰበሰ አስተሳሰብ አርቆ የጣለ ተራማጅ ሐሳብን ያነገበ፣ ብቁ መሪ እንደመሆኑ፤ ብቃት ያላቸው እንደገደል ማሚቶ ከማስተጋባት ይልቅ የራሳቸውን ክህሎት ተጠቅመው ሀገሪቷን ከእድገት ማማ ▶



ላይ የሚያስቀምጡ ልጊቃንን ማፍራት ነው የሚመኘው። ታዲያ እንዲህ ዓይነት ልጊቅ እንደ አንዳንድ ለሆዳቸው የሚያቶሰትሱ አርቲስቶች መናጆ መሆን የለበትም።

ከመደመር ባሻገር ማካፈልም ክንድ ለክንድ ተያይዞ የሚያሳድግ መርህ ነው። ከሰሞኑ ጠ/ሚ ዐቢይ "ግለኝነት አስወግደን ለኔ ለኔ ከማለት ለኛ ለኛ ማለትን ማስቀደም ነው ኢትዮጵያዊነት" የሚል መንፈስ ያለው ሐሳብ ማስደመጣቸው ይታወሳል። ይህ ማለት የማካፈል ስሌት ሊሰርጽን ይገባል ማለትም ነው። "ለራሱ የወደደውን ለወንድሙ እስካልወደደ አላመነም" እንዲል መልዕክተኛው። ካለው ላይ ማካፈልን ማሳደግ የሚገባን ጠባይ መሆን አለበት፡፡ እውቀትን በማካፈል በጋራ ማደግ፣ እህልን በማካፈል ሌላው ተመግቦ እንዲያድር ማስቻል፣ ቅንነትን በማካፈል በሌላው እንዲጋባ ማድረግ፣ ፍቅርን በማካፈል በሌላው ላይ እንዲዘራ ማድረግ የማካፈል መደብ ነውና ሊቀነቀን ይገባዋል።

ከሰዓታችን አካፍለን በመልካም ፈቃድ በሙያችን "የቮለንቲር" ሥራ ሠርቶ ወገንን መርዳት ለተጀመረው አዲስ የእድገት መንፈስ አጋዥ በሆነ ነበር። የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ በርካታ ወገንን ከችግር፣ ሀገርን ከልመና፣ ወገንን ከውድቀት የሚከላከል፣ በጽኑ የሚደገፍ ሥራ ነው።

ጽሑፌን ከማጠናቀቄ በፊት አንድ ከሰሞኑ ሰምቼው ውስጤ የቀረ ወግ ላስነብባችሁ። ወጉ በቀጥታም ባይሆን ከዐቢይ ጋር ይገናኛል።

"ሰውዬው አንዲት ርኩስ ሚስት ያገባና ነጋ ጠባ መከራውን ታሳየዋለች። እርሻ ውሎ ሲመጣ እንጀራ በሚጥሚጣ እያበላች ከጎኑ ነገር ታቀርብለታለች። የተራበ አንጀቱን ለማስታገስ ሁሌም ነገሩን ዋጥ አድርጎ እህሉን ያላምጣል። ከሷም ብሶ ተበደልኩ ባይ ሆና ለአላፊ አግዳሚው ብሶት ታወራለች። ነገሩን የሰማ እሱን እየኮነነ ስሙን ያጠፋል። ተበዳይም ተወቃሽም ሆኖ የሆዱን በሆዱ ይዞ ኑሮውን ይገፋል።

እንዲያም ሆኖ ልፍታሽ የሚል ጥያቄም አላቀረበላትም። ሚስት ለአፍታም በደሏ ሳይሰማት ባሏን በእህልም በድላ፣ በነገርም አቁስላ ኑሮዋን ትገፋለች። በዚህ ሁኔታ የተወሰኑ ዓመታት ከኖሩ በኋላ "አጉራህ ጠናኝ ካንተ ጋር መኖር ሰለቸኝ" ብላ ፍቺ ጠይቃ ቤቱን ለቅቃለት ወጣች። ባል የነገር ብልቃጧን ሸኝቶ ብዙም በብቸኝነት ሳይቀመጥ አንዲቷን ጉብል ያስገባል።

አዲሷ ሚስት፣ "እጁን ታጥቦ የሠራት" እንዲሉ፤ አመለ ሸጋ፣ ባሏን አክባሪ፣ ተንከባካቢ ሆና ታርፈዋለች። ጠዋት ሲወጣ በቅቤ የራሰ ገንፎ አገንፍታ፣ አሊያም በሶ በማር አበስብሳ፣ ሆዱን ሞልታ ትልከዋለች፤ ቀን ዶሮዋን ሠርታ፣ ቡናዋን አፍልታ፣ አብልታ አጠጥታ ወደ ሥራው ትሸኘዋለች ፣ሲመሽ እግሩን አጥባ፣ እራቱን አብልታ ታስተኛዋለች። ይህን ምቾት ካረጋገጠ በኋላ አንድ ቀን ዱላ በማንሳት ይደበድባት ጀመር፡-

"ምን አጠፋሁ ጌታዬ?" ብትለው፤

"እንዲህ ስቸገር እስከዛሬ የታባሽ ጠፍተሽ ነው" አላት ይባላል።

ለዐቢይ የተወረወረው ቦንብ አድራሻ እስካሁንም ተጣርቶ ከማን እንደሆነ ገና አልታወቀም። እንዲያው በመላ ከቀን ጅቦች፣ ጥቅማቸው ከተነካባቸው ሆዳሞች እንበል እንጂ በትክክል ማንነታቸው አልተገለጸም። እንዲያው ስንጠረጥር "እስከዛሬ የት ጠፍተህ ነው፤ አሁን ባለቀ ሰዓት የመጣኸው?" ባዮች ቢሆኑስ?

ደግ ደጉን የምንሰማበት፣ ለመልካም ሥራ የምንነሣሣበት ዐቢይ ዘመን ያድርግልን።

ቸር እንሰንብት!

# ዐቢይ ሰው!!!



ጋዜጠኛ ሚካኤል ዲኖ

"ታሪክ ሠሪው ሰፊው ህዝብ ነው" የሚለው አባባል ፍፁም ስህተት ነው፤ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በሳይንስ እና በኢኮኖሚ ረገድ አዲስ ፈር የቀደዱት፤ ያንን ተከትለው ዛሬ የምንኖርባትን ዓለም ያበጁት፤ ሥርአቱንም በበላይነት የሚዘውሩት ግለሰቦች ጥቂቶች ናቸው። ሰፊው ህዝብስ? ሰፊው ህዝብ እዚህ ውስጥ ያለው ሚና አንድም ከበረከቱ መቋደስ አንድም በእርግማኑ መደቆስ ብቻ ነው። በግለሰቦች ሲዘወር የባጀው ፖለቲካዊ ባሕላችን የሚያሳየውም የህዝብን አድራጊ ፈጣሪነት ሳይሆን በተቀደደለት ቦይ ፈሳሽነቱን ነው።

ዓለም፣ የግለሰብን ስሜት አስወግዶና ሥርዓትን ተክቶ በሳይንሳዊ መንገድ ለመተዳደር በሚጣጣርበት ዘመን እኛ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም የተቋማት ጮራ በግለሰባዊነት ጥላ በተጋረደባት አገር፣ የመከራ ኑሮን እየገፋን ነው።

እውነት ተገልብጧል! ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ አይደለም። ግለሰብ ታሪክ ሠሪ፣ ሰፊው ህዝብ ደግሞ ተባባሪ ነው።

(ይቺ መግቢያ የተወሰደችው ከፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ የመጨረሻ ዕትም 2007 ዓ.ም. ሲሆን በምናቤ ልክ የተሰፋውን ግለሰብ፣ በዋነኝነት ግን የመሪ-ተመሪን መስተጋብር ስለሚያመለክት ነው።)

የኢትዮጵያ ፓለቲካ በምትሐታዊ ለውጡ ተስፋ እና ሥጋትን አዛንቆ፣ ያረጀ ያፈጀ እሳቤን ከአዲስ ርዕይ አስተናንቆ፣ በተዋጣለት ድራማዊ ሂደቱ ያብዛኛውን ዜጋ ትኩረት ከማግኘቱም ባሻገር፤ ለመልካም ፍፃሜው የተቃዋሚዎቹን ተሳትፎ እስከማካተትም ድረስ የዘለቀ ሆኗል።

በለውጡ መንስኤነት ከቲም ለማም ሆነ ከቄሮ ባሻገር፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "እንዳርጋቸው ካልተፈታ ሥልጣኔን እለቃለሁ" የሚል መሞገቻ ማቅረባቸው፤ እሱን ተከትሎም የእንዳርጋቸው መለቀቅ፤ የአሜሪካ እና የምዕራባውያን ቡራኬም ሆነ እገዛ እንዳለው ለማሰብ ያስችላል ።

ከ2002-2007 ዓ.ም. በኢትዮጵያና የነፃውን ፕሬስ በዋነኛ ተነባቢነት ተቆጣጥረው የዘለቁት እንደቅደምተከተላቸው "ፍትሕ"፣ "አዲስ ታይምስ"፣ "ልዕልና" እና "ፋክት" መጽሔት በጋዜጠኛና ተመስገን ደሳለኝ እና ባልደረቦቹ ሲሰበክ የባጀው አብዮት እንደነበር ይታወቃል። ይህ ግልፅ አቋም ስብስቡን ከጋዜጠኝነት ማዕቀፍ ውጪ ጭምር "መንግሥት" ተደጋጋሚ የጉልበት እርምጃ እንዲወስድ ያደረገው ከመሆኑም ባሻገር በተለይ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የሦስት ዓመት አስከፊ እስርን ከፍሎበታል። በመስቀል አደባባዩ "የአብዮቱ አባት ተመስገን!!! እናመሰግናለን" የሚሉ መፈክሮችን ማየታችን ይህን እውነታ ያስረግጥልናል።

እንግዲህ የፖለቲካ እንቆቅልሻዊነት እዚህ ጋር ይገለጣል። ከአገዛዙ ድርቅና በመነሣት በህዝባዊ ማዕበል እንዲከሰት ስንወተውተው የኖርነው አብዮት፤ የምኞታችንን እሴት ተላብሶ በሥጋ ተገለጠ!!! …እናማ በግሌ በብዙ እሾኾች መካከል ታጥሮም ቢሆን ስቃትትለት የኖርኩትን ሰብእናና የኢትዮጵያዊነት ትርጓሜን የተላበሰ መሪን ለመደገፍ አይቻለኝም።

በእርግጥ ጠ/ሚ ዐቢይ በህዝብ የተመረጠ ባለመሆኑ እና የኢሕአዴግ አባል በመሆኑ በለውጡ ተስፋ፣ ዘላቂነት እና መዳረሻ ህልም በሆነው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በማስፈኑ ስኬት ረገድ የተአማኒነት ጥያቄ ደጋግሞ ይነሣል። ነገር ግን የፖለቲካን ጠመዝማዛነት ከታሪክ ለተገነዘበ ሰው ሁልጊዜም መጥፎ ዛፍ መጥፎ ፍሬ የማፍራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እዳዋ፣ በፖለቲካው አይሠራም። ለዚህም አባባል ማሳያ የሚሆነው አዶልፍ ሂትለር በህዝብ ምርጫ ወደመንበር ቢመጣም ወደፍፁም አምባገነንነት መቀየሩ ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ከላይ በጠቃቀስናቸው ገፊ ምክንያትና አካላት አማካይነት በታየው ተሐድሶ፤ ወያኔ በተጠና ሁኔታ ብልት እየለየ የወጋው ኢትዮጵያዊነት ተበሳስቶ ከወደቀበት ከቃል እስከ ተግባር በዘለቀው የጠቅላይ ሚኒስትሩ እንቅስቃሴ በተአምር ከፍ ብሎ ለመንሳፈፍ መብቃቱን ታዝበናል።

ለምሳሌ ያህል የመስቀል አደባባዩ የቦንብ ጥቃት የሚያስተላልፈው ግልፅ መልእክት ዛሬም መሬቷን ተቆጣጥረው የሚገኙት ቁልቋሎች፤ በየትኛውም ቅፅበት ከከፍታው ስበው በማውረድ ሊያፈነዱት እንደሚችሉ ከማሳየት ባሻገር ጠቅላይ ሚኒስትሩን የመግደል ዓላማ/ዒላማ ነበረው ብዬ አላምንም።


ከዚህ ጋር በተገናኘ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ከደህንነት ጋር በተያያዘ በቀጣይ መወሰድ ስለሚገቡ ተግባራት፤ "መንግሥት የሚመለከታቸው ተቋማት የሚወከሉበትና ተአማኒነት ያለው ግብረ ኃይል አቋቁሞ፣ ቢያንስ ለሁለት ቀን መሥሪያ ቤቶች ተዘግተው፣ የዝውውር እንቅስቃሴዎች ታግደው፣ የቤት ለቤት ፍተሻ አካሂዶ፣ መሣሪያዎቹን በመሰብሰብ ከተማዋን ከተደገሰላት መልከ ብዙ ጥፋት መታደግ ይኖርበታል። በአሰሳው ወቅት የመሣሪያ ፈቃድ ያላቸውንም ቢሆን የፊርማና የማእተብን እውነተኛነት ብቻ አይቶ በዋዛ ማለፉ አግባብ አይደለም። እንዴትና በምን መስፈርት ፈቃዱ እንደተሰጣቸው ከአዋጁ ጋር እያመሳከሩ በደንብ ማጣራት ያስፈልጋል።

የ1969 ዓ.ም. የደርግን እና የ1983 ዓ.ም. የወያኔን የቤት ለቤት ፍተሻ ተሞክሮን በመውሰድ፤ እንዲሁም ሰብአዊ መብት ሳይጣስ፤ ማንገላታት፣ ማዋከብ፣ ማስፈራራት ሳይፈፀም፤ አክብሮት ባልተለየው መንገድ ፍተሻውን ማካሄድ ታሳቢ ይሁን። በዚህ አጋጣሚ መሣሪያው የሚያዝባቸው ዜጎችም ትጥቁን ከፈቱ በቂ ነው። በወንጀል መክሰሱ ከተጀመረው የይቅርታ ልማድ ይቃረናልና።

በአናቱም በመከላከያ፣ በፌደራል እና በአዲስ አበባ ፖሊስ ሥር ያሉ የጦር መሣሪያ፣ የፈንጂ፣ የቦንብ፣ የጥይት ግምጃ ቤቶች ላይ ከወትሮ የተለየ ጥበቃና ቁጥጥር የማድረጉ አስፈላጊነት እንዳይዘነጋ።" በማለት ወሳኝ ነጥቦችን አንሥቷል።

በእርግጥም ጠ/ሚ ዐቢይ ሥልጣናቸውን በምልዐት ለማስረገጥና በህልማቸው መጠን ለመሮጥ መከላከያ ሠራዊቱን እና ደህንነቱን በቅጡ ከልሰው፣ ሾመውና ሽረው አዲስ ቅርፅ መስጠት ይገባቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ፍቅሩን እና ምስጋናውን በፍሬ በተግባር አስደግፎ ከመሪው ጎን በደጀንነት ሊቆም ታሪካዊ ተሳታፊነት እጁ ገብቷል!!!

ወያኔ፤ በሥልጣን ዘመኑ ያነበረውን የጎሳ ፖለቲካ እና ከምርጫ 97 ድንጋጤው ማግስት የመዘዛትን በትግራውያን ላይ ያደርሳል ያለውን የብሔር ተኮር ጥቃት በማሳያነት የደነጎለውን "ኢንተርሃምዌይ" በአልሞት ባይ ተጋዳይነት መጠቀም ያለው ቀሪ አማራጭ ይሆናል።





# ራስ ሳይጠና ጉተና!!!

በፍቃዱ አባይ

*ይህ ማስታወሻ የተጻፈው ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ “ለውጥን እንደግፍ፤ ዴሞክራሲን እናበርታ።” በሚል ዐቢይ መርህ ሥር ኢትዮጵያውያን ባካሄዱት የምስጋናና የድጋፍ ሰልፍ ላይ እንደተሳተፈ አንድ ዜጋና ጋዜጠኛ የተሰማኝን፣ የታዘብኩትን እና እርምት እንዲደረግባቸው የሚሹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው።*

## እንደ መነሻ

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደሥልጣን ከመጡ ገና ሦስት ወራትን አላስቆጠሩም:: በእነዚህ የሥልጣን ቆይታቸው ግን ያከናወኗቸው ተግባራት ገዢው ፓርቲ ለ27 ዓመታት ከሠራቸው ሁሉ ይበልጣሉ:: ከሁሉም ከሁሉም ከቁሳዊ ልማት በተሻለ በሰብአዊ ልማቱ ላይ አቅደው የሠሯቸው ሥራዎች ሰውየውን ቅቡል ለማደረግ አስችሎአቸዋል:: ይህም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለምንም ልዩነት የዘሩት የከፍታ፣ የአንድነት፣ የፍቅር፣ የይቅርታና የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሁሉንም ያስማማና ወደ አደባባይ ሆ! ብሎ እንዲወጣ መንስኤ ሆኖአል:: ገዢው ፓርቲ በ27 ዓመታት ከልባችን ማኅደር ነቅሎ የጣላቸውን የጋራ እሴቶቻችንን ዳግም ለመመለስ ከባድ ሊሆን እንደሚችል በብዙዎች ቢገመትም ልበ ብሩሁ ጠቅላይ ሚኒስትር ግን የተገመተውን ሁሉ አፍርሰው ያልተጠበቀውን መልካም ዘር በውስጣችን ዘርተዋል:: በሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በህዝብ ዘንድ የታየው መነሣሣትና መሥዋዕትነትም ዘሩ ገና ሳያሽት መልካምነት ያለው ስለመሆኑ አመላካች ነው::



## የአዲስ ዓመት ዋዜማ

ሰኔ 15 ቀን 2010 ዓ.ም. መስቀል አደባባይ በሰዎች ግርግር፣ በመድረክ ግንባታ፣ አካባቢ በማሸብረቅ እንቅስቃሴዎች ደምቆ ነበር:: የአስተባባሪው ኮሚቴ አባላት ከሰዓት በኋላ የጠሩት ጋዜጣዊ መግለጫ ደግሞ በዝናቡ እስከታወከበት ጊዜ ድረስ ለአደባባዩ ልዩ መልክ ሰጥቶት የዓውደ ዓመት ዋዜማን ዓይነት ስሜት አጋርቶን አልፏል::

ከመስቀል አደባባይ ባሻገርም፤ ሸገር በየጎዳናዋ የተለያዩ መልእክቶችንና ምስሎችን በያዙ የቲሸርት ሽያጮች ሥር መድመቋ የሸር ጉዱ አካል ስለመሆኗ ማሳያ ነው:: የኢትዮጵያ የበጎ ፈቃደኛ ጋዜጠኞች ኔትዎርክም የዚህ የዋዜማው ድምቀት ሌላኛው ግብዓት ነበር::

የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል በሚል መርህ ሥር የሚንቀሳቀሰው ኔትዎርክ የምስጋና ዝግጅቱ አካል በመሆን ቲሸርቶችን ለአባላቱና ደጋፊዎቹ በማሳተምና ዓላማውን በመደገፍ አባላቱ የተለያዩ አበርክቶችን ተወጥተዋል:: በተጨማሪም በተለያዩ አካባቢዎች በነዋሪዎች ዘንድ የታዩት መነቃቃቶችና ደስታዎችም ሰኔ 16 የዘመን መለወጫ በዓል የሚከበርበት ልዩ ቀን እንጂ በእርግጥም ለድጋፍ ሰልፍ ዝግጅት የሚደረግበት ዋዜማ ብቻ እንዳይመስል አድርጎታል:: በእርግጥም በምናብ ዕለቱ ጳጉሜ 5 ነው:: በማግስቱም መስከረም አንድ:: ከዘመነ ባርነት ወደ ዘመነ ነጻነት ሽግግር የተደረገበት የአዲስ ዘመን ማብሰሪያ ነበር የሚመስለው:: ለዚህም ይመስላል አዲስ ልብስ እንደተገዛለት ሕፃን ቲሸርታችንን ለብሰን የተኛነው፤ አልነጋ ብሎን የአዲስ ዓመትን መጥባት ያለ እንቅልፍ እንድናሳልፍ የተገደድነው:: በዚህ ረገድ ማህበራዊ ሚዲያው በተለይም ፌስ ቡክ የነበረው ሚና ከፍ ያለ ነበር::

ኢህአዴግ ፌስ ቡክን ከአረብ አብዮት ጋር አስተሳስሮ በዓይነ ቁራኛ ሲጠብቅ ቢከርምም የራሳቸውን አብዮት ማቀናበር የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ከብርቱካናማው አብዮትም ሳይደባለቁ የራሳቸውን አብዮት ሰኔ 15 ቀን 2010 ዓ.ም አውጀው ሲጨርሱ ፌስ ቡክ ትልቁ የሐሳብ ማስተላለፊያ ምንጫው እንዲሆን በአግባቡ ተጠቅመውበታል::

## ዘመን መለወጫ

ለኢትዮጵያውያን አዲሱ ዘመን መዋጀቱንና ይህንንም በክብር፣ በፍቅርና በአንድነት መቀበላቸውን ለማወጅ፤ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. ቀጠሮ ያዙ:: የቃል ኪዳኑ ማሰሪያ፣ የባተው ዘመን ማመስገኛ ስፍራ ይሆን ዘንድም መስቀል አደባባይ ላይ ተሰባሰበ:: በአራቱም አቅጣጫ ከአራት ሚሊዮን በላይ ህዝብ ወደ መስቀል አደባባይ ተመመ:: ይህ የምስጋና ማዕበልም ከጎጥ አስተሳስብ ራሱን አላቅቆ፣ ከልዩነት ይልቅ አንድነትን ታጥቆ፣ በጋራ ሆ ብሎ ከንጋት እስከ ረፋድ መስቀል አደባባይን አጥለቀለቀ:: ከዚህ በተጨማሪም እዚያው ያደሩና ትዕይንቱን ለመታደም የጓጉ ኢትዮጵያውያን በርካቶች ነበሩ::


## ከመድረክ በስተጀርባ

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መልዕክቶች ከፍ ብለው፤ በአብዛኛው በቀደመው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዎች ደምቀው፤ በተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ዜማዎች ጭፈራውን እያደሩት ነው:: ከዚህ የፊት ለፊት ትዕይንት መድረክ በስተጀርባ የድጋፍ ሰልፉ አስተባባሪዎች በሰልፍ ታድመዋል:: ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንንን ጨምሮ ሌሎች ሚኒስትሮችና የሥራ ሐላፊዎችም ከአስተባባሪው ኮሚቴ ትይዩ ተደርድረዋል:: እዚህም እዚያም ፈገግታን የተላበሱ ፊቶች ከጠዋቱ ጸሐይ እኩል ያበራሉ:: ሁሉም በየጎራው ይተቃቀፋል:: ሰላምታ ይለዋወጣል:: ሰልፊ ፎቶ ይነሣል::

በእነዚህ ውብ ፈገግታዎች እና ብሩህ ፊቶች ውስጥ ግን ጥበቃ አለ:: ሁሉም በየደቂቃው ዓይኖቻቸውን ወደ ግዮን ሆቴል የጓሮ በሮች ጣል ያደርጋሉ:: የሚጠብቁት ከመካከላቸው የጎደለ ነገር ግን የዕለቱ የኢትዮጵያውያን የክብር እንግዳ ቢዘገይ እንጂ እንደማይቀር ያውቃሉ:: የጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮቹ ጠባቂዎችም በየቦታው ደጀን ይዘው በተጠንቀቅ ቆመዋል:: በእነርሱ ዓይን ውስጥም አንድ ሰው ይጠበቃል:: ያ የሚሊዮኖች ዓይኖች በጉጉት የሚጠብቁት እንግዳም ጠባቂዎቹን አላሳፈራቸውም፤ ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ በነጫጭ ቪ 8 መኪናዎች ታጅቦ ተቀላቀላቸው:: የሁሉም ናፋቂዎች ፊቶች ከጸሐይ ልቀው አበሩ:: የፍቅር እጆች ተዘረጉ:: የመድረኩ ጀርባ በእንግዳው መምጣት ይበልጥ ተዋበ:: ከሰላምታው በኋላም ሁሉም ወደ ተዘጋጀላቸው መድረክ በጋራ አመሩ:: ቀደም ብለው በስፍራው የተገኙት አስተባባሪዎችና የሥራ አጋሮች በጠቅላይ ሚኒስትራቸው እየተመሩ ወደ ተዘጋጀላቸው መድረክ አመሩ::

## የምስጋና ስጦታ፣ ቦምብ

ቦምቡ ሲፈነዳ ከመድረኩ ከመድረኩ በስተግራ ከ100-150 ሜትር ርቀት ላይ ነበርሁ:: ሁላችንም እየሮጥን ወደ መድረኩ ጀርባ ገባን:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድንና ሌሎች የሥራ አጋሮቻቸውን ይዘው ያመጡት ቪ 8 መኪናዎች በፍጥነት አካባቢውን እንዲለቁ አደረግን:: ሁሉም በገቡበት የግዮን ሆቴል የጀርባ በር ማምለጣቸውን ▶



አረጋግጠን እንደጨረስን በርካታ ወጣቶች እያለቀሱ ወደ እኛ መጡ:: የጸጥታ ክፍሉ አባላት ምን እንደተፈጠረ አልገባቸውም:: የሁኔታዎች በፍጥነት መለዋወጥ ግራ አጋብቶአቸዋል:: አንድም የመግቢያውን በር የመጠበቅ፣ ሌላም በስሜት ያበዱትን ወጣቶች የማረጋጋት ሥራ ያሯሩጣቸዋል:: የበርካታዎቹ ወጣቶች ጥያቄ ጠ/ሚ ዐቢይን አሳዩን የሚል ነው:: በዚያ ድንጋጤ ወስጥ ለወጣቶቹ መልስ መስጠትና ለማረጋጋት መሞከር በጣም አስቸጋሪ ሆኖብን ነበር:: ወዲያውኑ ቦምብ ለማፈንዳት ሞክራለች የተባለችውና ዘባተሎ ልብስ የለበሰችው ወጣት ተያዘች ተባለ:: ሰው ሁሉ ወደዚያው ሮጠ:: እኛም ተከተልን:: ወጣቷ መሬት ላይ ተዘርራለች:: የመጣው ሁሉ የማርያም ጠላት አደረጋት:: የሰከነ አዕምሮ፣ ነገሮችን ቆም ብሎ የሚያስተውል ሰው በዚያ ሰዓት ይናፍቃል:: ከስንት ጭቅጭቅና ግብ ግብ በኂላ ወጣቷን በስሜት ካበዱት ወጣቶች እግር ፈልቅቀን አወጣናት::

ትዕይንቱ ቀጠለ:: ሌላ ተጠርጣሪ ወንድ ተያዘ ተባለ:: ተመሳሳይ ግርግር፣ ተመሳሳይ የእንገላለን አትገሉም ግብግብ ተፈጠረ:: በስንት ርብርብ ይህንንም ወጣት ለማትረፍ ቻልን:: በዚህ መልኩ አራት ተጠርጣሪዎችን መስቀል አደባባይ ጀርባ ከሚገኘውና የፌዴራልና የአድማ ብተና አባላት ከሚገኙበት ግቢ አስገባን:: ቆይቶም አንድ ተጠርጣሪ ተጨመረ:: በኂላም የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት መምጣታቸውን አረጋግጠን ተጠርጣሪዎቹ ቃላቸውን መስጠታቸውን አረጋግጠን ግቢውን ለቅቀን ወጣን:: ይህን ሁሉ አደጋና ሐላፊነት ለምን እንደተጋፈጥን በስፍራው የነበርን ታዳሚዎችን አሁን ላይ ማንም ቢጠይቀን ምላሽ ለመስጠት አንችልም:: እውነቱ ግን ሐላፊነት ተሰምቶን ማድረግ የሚገባንን በሙሉ ፈጽመናል:: ተጠርጣሪዎቹን ሰልፈኛው እንዳሰበው የከፋ ጉዳት አድርሶባቸው ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ በምርመራ የተደረሰበትን ድል ማስመዝገብ አንችልም ነበር:: ተጠርጣሪዎቹ ሕይወታቸው አልፎ ቢሆን ኖሮ፣ ለሞቱና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ምክንያት የነበሩ አጥፊዎችን ለመያዝ የተጠነሰሰውንም ሴራ ጫፍ ለማወቅ አንችልም ነበር:: ተጠርጣሪዎቹ በሚሰጡት ቃል የሴራው ዋነኛ ጠንሳሾችና የሞት ድግስ ደጋሾቹ ማንነት የመታወቅ ዕድሉ ይጠብ ነበር:: ለዚህም ነው የተጠርጣሪዎቹን ጉዳትና ሞት ተከላክለን ለጸጥታ ክፍሉ ለማስረከብ የቻልነው፤ በዚህም ተሳክቶልናል:: በእነዚህ ተጠርጣሪዎች ጥቆማ የምስጋናችንንና የደስታችንን ጠላቶች ለማወቅ እንችላለን:: ነጻነታችን ያንገበገባቸው፣ ፍቅራችን ዓይናቸውን ያቀላባቸው፣ ምስጋናና አንድነታችን ላቃራቸው ወገኖች የተጠርጣሪዎቹ በሕይወት መቆየት ከፍ ያለውን ሚና እንደሚጫወት አምናለሁ:: ህዝብ በዚያ የከፋ ስሜት ውስጥም ሆኖ ያልነውን ሰምቶ፣ ትብብራችንን አግዞ ተጠርጣሪዎቹ በሕይወት እንዲቆዩ ላሳየው ጥረት ምስጋና ይገባዋል::

## የጸጥታው ጉዳይ

ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከመድረክ ጀርባ ወደሚጠብቋቸው አስተባባሪዎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ከመምጣታቸው በፊት፤ ባቡሩ በሥራ ላይ መሆኑን አስተውዬ ከጠባቂዎቻቸው ለአንዱ ጥያቄ አቅርቤ ነበር:: ነገር ግን እሱም ጥያቄዬን መመለስ አልቻለም::

ጠቅላይ ሚኒስትራችን በመድረኩ ታድመው ንግግር በሚያደርጉ ሰዓትም ባቡሩ በአናታቸው ላይ ያልፍ ነበር:: ይህም ብቻም ሳይሆን የሲቪል ልብስ እና የፌዴራል ፖሊስ ዩኒፎርም ያደረጉ ሰዎች እንደ ልባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር እያደረጉ በአናታቸው ላይ እየተንቀሳቀሱ ነበር::

የቦምብ ፍንዳታው በተፈጸመበት ስፍራ የነበረው የአጥር ተንቀሳቃሽ ብረት ለሁለት ጊዜያት ያህል በግፊያ ፈርሶአል::

በህዝብ ጥረት የተያዘውና ኂላም ግልጽ ባልሆነ መንገድ እንዲቃጠል የተደረገው የፖሊስ መኪና ህዝብ መካከል መሣሪያ ታጥቆ እንዲገባ ተፈቅዶለታል::

ከጠቅላይ ሚኒስትራችን የግል ጠባቂዎች መካከል ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ያህል ቦምቡ ወደ ፈነዳበት አካባቢ እንዲጠጉ ሲገፏቸው ነበር:: (የተቀረጹ ፊልሞችን ማየት ይቻላል)

እነዚህና ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ህጸጾች በጸጥታ አጠባበቅ ዙሪያ የታዘብኂቸው ዝርክርክ አሠራሮች ነበሩ:: የጸጥታ ክፍሉ ከ27 ዓመታት የቆይታ ትዝብታችን በተለየ መልኩ፤ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ተዝረክርኮ ታይቶአል:: የሚመለከተው ክፍል በሚገባ ሊፈትሸው የሚገባውና እርምት ሊወሰድበት የሚገባ ችግር ነው::

## ማጠቃለያ

ከላይ በዝርዝር ለማሳየት የሞከርኩት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በድጋፉና በምስጋናው ትዕይንተ ህዝብ ላይ ከነበረኝ ተሳትፎ አንጻር መነገር ያለባቸውና አስፈላጊ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸው ነጥቦች ብቻ ነው:: ሀገራችን በ81 ቀናት ያየችው የተስፋ ጭላንጭል ዳግም እንዲጠፋ አልመኝም:: ይህ የዛሬው የድል ጅማሮ እውን እንዲሆን በርካቶች ዋጋ ከፍለውበታል:: እኛም ይህ በመሥዋዕትነት የተገኘው ብርሃን እንዳይዳፈን የዜግነት ድርሻችንን እንወጣ::



**ታምራት መርጊያ**

# “ህመም ከሌለ፥ ለውጥ አይኖርም”

ለውጥ እጅግ ከባድ፣ ውስብስብና ብርቱ ፈተናዎችን ማለፍ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ሂደቱም ቢሆን እንደዚያው የገዘፉና የተጠላለፉ ፈተናዎችንና ጥሎ ማለፎችን በጽናት ታግሎ ማሸነፍን የሚሻ ነው። አንድን ተቋም ብቻ መለወጥ እንኳን በራሱ እጅግ ከባድ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው። ሀገር ሲሆን ደግሞ፤ ተራራን የመግፋት ያክል ይሆናል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ጉልቆ መሳፍርት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስንክሳሮችን አጭቀው በያዙ ሀገሮች ውስጥ፣ ለውጥን መተግበር ቀርቶ ማሰብ እንኳን ተራራን ከመግፋት የማይተናነስ ፈተናን ስለሚደቅን፤ ይህንን ሊለውጥ የሚችል የሀገር መሪ ከፍተኛ የሆነ ጽናትን፣ ብርታትን፣ የአመራር ጥበብን እንዲሁም ቁርጠኝነትን የተላበሰና በተለየ መልኩ መሰጠት ያለው መሪ ሊሆን ይገባል።

የመጡበትን መንገድ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያመጧቸውን ለውጦችና በሕዝብ ዘንድ የተጎናጸፉትን ሞገስና ተቀባይነት ስንመለከት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንዲህ ያሉ መሪ እንደሆኑ መገመት ይቻላል። ይሁን እንጂ የተጋፈጡት ውስብስብና እጅግ ፈታኝ የሆነውን ሀገራዊ ተጨባጭ እውነታም በብቃት ለመወጣት አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸውም የሚጠበቅ ነው።


በመሆኑም እንዲህ ጅምራቸው ያማረላቸውና የሚመሩትን ሕዝብ ተቀባይነት በአጭር ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ለማግኘት የቻሉት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ለመግለጽ እጅጉን በሚያዳግቱ በርካታ ውስብስብ መንገዶች ውስጥ ማለፍ እንደሚኖርባቸው ሳይታለም የተፈታ ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥም በርከት ያሉ የርሳቸውንና የወገናቸውን ሰብአዊ ማንነት በብርቱ ሊፈታተኑ የሚችሉ ሕመሞችን ማስተናገዳቸው የማይቀር ጉዳይ ነው።

የሙስና ወንጀሎች፣ የተደራጁ ሌብነቶች፣ የፖለቲካ ሴረኝነት፣ የኢኮኖሚ ሽፍጥ፣ በየወቅቱ እዚህም እዚያም ሆን ተብለው በታቀደ መልኩ እንዲፈነዱ የሚደረጉ የብሔር ግጭቶች፣ ነባሩን ሥርዓት ለማስቀጠል የሚደረጉ የፖለቲካዊ አሻጥሮች… ወዘተ፤ ጠ/ሚ ዐቢይን ሊፈታተኑ ከሚችሉ አበይት ፈተናዎች መካከል ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦች ናቸው።

የሆነው ሆኖ፤ የእነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ድምር ውጤት የሚፈጥረው ጥልቅ ህመም መኖሩ ባይቀርም፤ ያለ ህመም የሚጠበቅ ለውጥ አይኖርም። ስለሆነም ህመሞቹን ተቋቁሞና በፈተናዎች ውስጥ እንደ ብረት ተፈትኖ በጽናት ማለፍም፣ ወደታሰበው ከፍታ ለመድረስ አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ራሳቸው፤ ሰኔ 16/2010 ወደሥልጣን በመጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ላስመዘገቧቸው ለውጦችና የማስተካከያ እርምጃዎች ምስጋና ለማቅረብና ለውጡን እንዲያስቀጥሉ ለማበረታታት እንዲሁም ከጎናቸው መቆሙን ለመግለጽ በመስቀል አደባባይ ለተሰበሰበው በሚሊዮኖች ለሚቆጠር ሕዝብ ባደረጉት ንግግር እንደገለፁት፤ “በፍቅር እና በአንድነት ጀምሮ፤ መጨረስ የተሣነው የለም”ና፤ መንገዱ የቱንም ያህል ከባድና ፈታኝ ቢሆንም፤ በጀመሩት የፍቅር፣ የይቅርታና የእርቅ መንገድ እስከመጨረሻው መጓዝ ከቻሉ፤ ያሰቡትን በጎ ሀገራዊ የመለወጥ እሳቤ ግብ መምታት እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም።



# ልዩ ዕትም

ከዚህ በተቃራኒ፤ ባለፈው ሳምንት በተካሄደው የድጋፍ ሰልፍ ላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ በተሰበሰበበት፣ ከጥቃቱ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቴሌቪዥን ቀርበው እንደገለፁት “ሞያን በታገዘ” መልኩ፤ የተፈፀመው የቦንብ ጥቃት፣ ያለምንም ጥርጥር እየታየ ያለውን ሀገራዊ ለውጥ ለማደናቀፍ የታለመና ለውጡ የግል ጥቅማቸውን እንደሚነካባቸው ባመኑ አካላት፤ በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማጥቃት የተቀነባበር ሴራ እንደነበር ግልፅ ነው:: ይሁንና ይህ የከሸፈ ሴራ በበርካታ ወገኖች ላይ ጉዳት ማድረሱና ለሁለት ሰዎች ሞት ምክንያት መሆኑ፤ የፈጠረው ሀገራዊ ህመም፥ የለውጥ ሂደቱ ሊፈጥራቸው ከሚችላቸው በርካታ ህመሞች ውስጥ እንደ አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው::

ይሁንና ይህንን እኩይ ድርጊት ልዩ የሚያደርገው፤ ፈጻሚዎቹ ሆድ እንጂ የዚህ ዓይነት ድርጊት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ሊያመዛዝን የሚችል ሕሊና የሌላቸው መሆኑ ነው:: ይልቁንም፣ ይህ ድርጊታቸው በታቀደና ሞያን በታገዘ መልኩ የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ የበርካቶችን ሕይወት ለመቅጠፍ የታለመ መሆኑን ስንመለከት፣ እ.ኤ.አ. ከ1941 እስከ 1945 በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፣ በናዚ ጀርመን ታቅዶ ከተካሄደውና የስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያንን ሕይወት ከቀጠፈው “የሆሎኮስት” ጅምላ ጭፍጨፋ ጋር የሚተካከል አረመኔያዊ ተግባር ነው::



ልዩነቱ፤ አንድም ናዚ፣ ጀርመን ድርጊቱን የፈጸመው በገዛ ወገኖቹ ላይ ሳይሆን፣ የሀገር ጠላት ናቸው ብሎ ባመናቸው ባዕዳን ላይ መሆኑ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የናዚ ጀርመን እኩይ እቅድ ተሳክቶ፣ የነዚህኞቹ አለመሳካቱ ብቻ ነው::

ያም ሆነ ይህ፣ ከዚህ የተወገዘ ሂትለራዊ ተግባር፣ የድርጊቱ ቀያሾች ለማግኘት ያቀዱት ምን ዓይነት ፖለቲካዊ ትርፍ እንደ ነበር እርግጠኛ ሆኖ መናገር ባይቻልም፤ ሁለት ዓይነት መልክ ያላቸውን መላ ምቶችን ማስቀመጥ ግን ይቻላል::

ይኸውም፣ አንደኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመግደል፤ በእጅ አዙር በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የታለመ ወይም ፈረንጆቹ “State capture” የሚሉት ዓይነት እቅድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በዝግጅቱ ላይ ሊታይ የሚችለውን፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ከፍተኛ ህዝባዊ ተቀባይነትና ድጋፍ እንዳይታይ በማድረግ፣ ይልቁንም ዝግጅቱን አሉታዊ በሆነ መልኩ ቀይሮ፣ ሀገሪቱ ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ውስጥ እንደምትገኝ ለዓለም በማሳየት፤ የጠ/ሚ ዐቢይን እና እርሳቸው የሚመሩትን መንግሥት ዓለም ዓቀፍ ገጽታ ማጠልሸት እና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፤ በተለይም በምዕራባውያኑ ዘንድ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሀገር የመምራት ብቃት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎ፤ ከውስጥም ከውጭም መፈናፈኛ በማሳጣት በእንጭጩ እንዲቀጭ ለማድረግ የታሰበ እንደሚሆን መገመትም ምክንያታዊ መላ ምት ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

ይሁንና፣ በየትኛውም መልኩ ቢታሰብ፤ በዚህ መንገድ በመንዝ ለድርጊቱ ቀያሾችና ተባባሪዎች ሊያስገኝ የሚችለው ትርፍ አለመኖሩን የዚህ ድርጊት ወጣኞች አስቀድመው አለመረዳታቸው የሚያሳየው፤ አንድም ደመ ነፍሳዊ ጭፍን ጥላቻና በቂም በቀል ስሜት አባዜ ብቻ የሚጓዙ ሰዎች ያቀዱት እቅድ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ከታየ ደግሞ፤ የዚህ ድርጊት ወጣኞችም ሆኑ ከዋኞች የሰብአዊነትና የማሰብ ደረጃ በእጅጉ ዝቅ ያለ እንስሳዊ (Subhuman) ወይም ለአውሬነት የቀረበ እንደሆነ ነው::

ምክንያቱም ማንኛውም በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚኖርና ማመዛዘን የሚችል አእምሮ ያለው ሰው፤ በዚህ መልኩ የግል ፍላጎቱንና ምኞቱን አሳክቶ ሥልጣን ለመያዝ ወይም ጥቅሙን ለማስጠበቅ ያስባል ተብሎ አይገመትም::

መቼም መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ማገናዘብ ለሚችል ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ግልፅ ሊሆን እንደሚችለው፣ በአሁኑ ሰዓት ሕዝቡ እንደ መሲሁ ተቀብሎ፤ እንደ ዐይኑ በስስት የሚጠብቃቸውንና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሳይቀር በከፍተኛ ደረጃ በአዎንታዊ መልኩ ተቀብሎ ከሀገራቸዉ አልፈው አህጉራዊ ለውጥ ሊያመጡ እንደሚችሉ ተስፋ የጣለባቸውን መሪ፤ በዚህ ዓይነት ኢ-ሰብአዊ መንገድ እንዲወገዱ አድርጎ የራስን ዓላማ ለማሳካት ማሰብ በራሱ፣ እውነታን ከመረዳት ውሱንነት የሚመነጭ ነው::

ከዚህ በተጨማሪም፣ ውጤቱ ማንንም ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደማይሆንና ሀገሪቱን ወደ እልቂትና መቋጫ ወደሌለው የርስ በርስ ግጭት ውስጥ ሊጨምር የሚችል የዜሮ ድምር ጨዋታ ነው::

ከታሪካችን እንደምንረዳው፣ ምንም እንኳን ሁኔታው ቢለያይም፤ የ1960ዎቹ ትውልዶች፣ በኢህአፓ ማእቀፍ ሥር በተደራጁና ጥቂት ሐላፊነት በጎደላቸው የፓርቲው አመራሮች ግብታዊ ውሳኔ ምክንያት፣ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለመግደልና ከሥልጣን ለማስወገድ በታቀደ ድርጊት መንስኤ፤ ያንን ተከትሎ በመጣ መዘዝ የበርካታ ውድ ዜጎቻችን ሕይወት እጅግ አስከፊ በሆነ መንገድ በከንቱ እንዲቀጠፍ አድርጎ ያለፈበት ጥቁር የታሪክ ጠባሳችን፣ ከዚህ ዓይነት ድርጊት ማንም አትራፊ ሊሆን እንደማይችል ካለፈዉ መማር ለሚችል ሰው፣ ህያው ማሳያ ነው::

በርግጥ አሁን ያለው ሁኔታ ከዚያ አስከፊ ሁኔታ ጋር ለንጽጽር የሚቀርብ ባይሆንም፤ ጠ/ሚ ዐቢይም ከኮሎኔል መንግሥቱ አንጻር የተለዩ መሪ ቢሆኑም፣ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት ግን ተመሳሳይ ውጤት ወይም ሌላ አይነት መልክ ሊኖረውና በሕዝቦች መካከል ሊፈጠር የሚችል የከፋ የርስ በርስ መተላለቅ በማስከተል አዲስ የመቃብር ታሪክ ከፋች ሊሆን ይችል እንደነበር ግልጽ ጉዳይ ነው::

የሆነው ሆኖ፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ አዲስ ነገርን ከሥር ከመሰረቱ ጤናማ በሆነ መንገድ ከመገንባት ይልቅ፤ የነበረን አሠራር መቀየር የሚፈጥረው ምስቅልቅና ውጣ ውረድ፣ እዳው ገብስ እንደሚሆን ለማንም ግልጽ ነው::

በመሆኑም ጠቅላይነት ሚኒስትር ዐቢይም ሆኑ፣ አጠቃላይ ሕብረተሰቡ ይህንን እውነታ በመረዳት እንዲህ ያሉ ኹነቶች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ህመሞች አስቀድሞ በመገንዘብና ህመሞቹን እንደየአመጣጣቸው በመቋቋም፣ ፈተናዎችንም ወደ መልካም አጋጣሚዎች በመቀየር፤ የተጀመረውን ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ ሥር ነቀል የለውጥ እርምጃዎችና እመርታዎች ማስቀጠል ይጠበቅባቸዋል::

በመጨረሻም “ፍትሕ ገዳዮቿን ትገድላለች” እንደሚባለው፤ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የዜጎቻችንን ሕይወት የቀጠፉ፣ አካል ያጎደሉና ፍትሕን የገደሉ ሁሉ፣ በሕግ ፊት ቀርበው በአፋጣኝ ፍትሕ እንዲያገኙ ማድረጉ የሚጠበቅ ነው::

ድል ለፍትሕ እና ለዴሞክራሲ!
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!!

## ልዩ ዕትም



# የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ምን አሉ?

*የዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ስለሰልፉ ትዕይንት ያቀረቡትን ዘገባና ከመላው ዓለም ጥቃቱን በማውገዝ የተሰነዘሩ መግለጫዎችን በማሰባሰብ የግዮን ዘጋቢዎች እንደሚከተለው አጠናቅረውታል፡፡*

### ኒዮርክ ታይምስ በጁን 23 ቀን 2018

ራሳቸውን የመጻሕፍት ክበብ አባላት አድርገው በየወሩ በአንደኛው ቅዳሜ ተሰብስበው በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ላይ የሚወያዩ ሠላሣ አባላት ያሉት ክበብ አባላት ውስጥ ሃያዎቹ ሴቶች ናቸው፡፡

በዛሬው ውሏቸው ስለ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራቸው የ41 ዓመቱ ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ሥልጣን ከያዙ ቀን ጀምሮ ስለፈፀሙት ሥራ፣ ስለአደረጉት ይቅርታ እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ፍቅር እና አንድነት ይመጣ ዘንድ ስለወሰዱት እርምጃ ለመነጋገር ወስነዋል፡፡

የክበቡ አባል የሆነውና በአንድ ዩኒቨርስቲ በሌክቸረርነት የሚሠራው የ33 ዓመቱ መኮንን መንገሻ ስለ ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ ሲናገር “ከቀድሞዎቹ የሀገሪቱ መሪዎች ጋር ትልቅ የሆነ የትውልድ ክፍተት ነበር፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ግን የእኛ ትውልድ አባል ነው፤ ሕመማችንን፣ ስሜታችንን ይጋራልናል፤ ይሰማዋል” ብሏል፡፡

ሌላዋ የ31 ዓመቷ የፐብሊክ ፖሊሲ ኤክስፐርት የሆነችው ማክዳ ጌታቸው፣ “ሁሉንም ነገር እንደአዲስ እየጀው ነው፤ ስለዚህ እናደንቀዋለን” ብላለች፡፡

ይህንን ለውጥና የአዲስ ነገር ጅማሮ ሁሉም ወገን አልተቀበለውም፤ በቅዳሜው የሰልፍ ትዕይንት ላይ በተወረወረ ቦንብ የሰልፉ ተሳታፊ የነበሩ ሁለት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩም ለከባድና ለቀላል መቁሰል አደጋ ተዳርገዋል፡፡

የመጽሐፍ ንባብ ክበቡ አባላት፣ “እንደቀድሞ ባለሥልጣኖቻችን ማለቂያ የሌላቸው ርዕዮተ ዓለማትንና ፓርቲው የሚጠቀምባቸውን ቃላት አይጠቀምም፡፡ እያንዳንዱን ችግራችንን በሚገባ ይረዳል፤ ሕዝቡ ምን እንደሚሰማውም ያውቃል፡፡ የፓርቲውን ውድቀት፣ በመንግስት ፖሊሲ ችግር ሳቢያ የተፈጠረውን ስቃይና ችግር ያውቃል፡፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ትኩረቱ በኢትዮጵያውያን እድገት ላይ ነው፤ ይህ ደግሞ ለእኛ አዲስ ነው” ይላሉ፡፡

ማክዳ ጌታቸው “ከእርሱ ብዙ እንድንጠብቅ አድርጎናል፤ ግን አሁንም ቢሆን ሀገሪቱን የሚመራው በቆየ አሮጌ የፓርቲ መዋቅር፣ በአሮጌ የመንግሥት መዋቅር፣ በአሮጌ ሕግ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች ነው፡፡

አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ወደፊት ያሰበውን ለማድረግ፣ የምንመኘውን ለማከናወን ከፈለገ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ብሔራዊ ውይይት ማካሄድ ለቀጣዩ ምርጫ የሚሆኑ የፖለቲካ ማሻሻያዎችና የምርጫ መርሐ ግብር ሊያዘጋጅ ይገባዋል” ብላለች፡፡

የመጽሐፍ ክበቡ አባላት ያን እለት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ብቻ ሳይሆን “ዘ ፕሪንስ” በተሰኘው በማካቬሊ መጽሐፍ ላይ ጭምር ነው ሲወያዩ የነበረው ብሏል፤ የኒዮርክ ታይምሱ ዘጋቢ፡፡

### ዋሽንግተን ፖስት

ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚኖሩ ሕዝቦች ወደ አደባባይ በመምጣት ለአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለዶክተር ዐቢይ አሕመድ ድጋፋቸውንና ምስጋናቸውን በመግለጽ ታላቅ ትዕይንተ ሕዝብ አድርገው ነበር፡፡

በትዕይንተ ሕዝቡ ላይ በእንግድነት የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኔልሰን ማንዴላ ምስል ያለበትን የአፍሪካ ካርታ የታተመበት አረንጓዴ ቲሸርት ለብሰው ንግግር ካደረጉ በኋላ ወደ ተለያዩ የአደባባዩ አቅጣጫዎች በመዞር ጎንበስ እያሉ ሲያመሰግኑ ቆይተው፤ ቦንብ ወደተወረወረበት ስፍራ ዞር ብለው ሲያዩ በጠባቂዎቻቸው ተከልለው ተወስደዋል፡፡

ጥቃቱ ከደረሰ በኋላ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ጥቂት ሰዎች በደረሰው ጥቃት ላይ መሞታቸውን ተናግረዋል፡፡ ይህንን የተቀነባበረና በባለሙያ የተዘጋጀ ጥቃት “የማይጠቅም ርካሽ ተግባር ነው” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አውግዘውታል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር አሚር አማን ዘግይተው በቲዊተር ገፃቸው እንዳሳወቁት “ሁለት ሰዎች በአደጋው ሲሞቱ 155 ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል” ብለዋል፡፡

ዶክተር ዐቢይ “ፍቅር ያሸንፋል፤ ይቅርታ ያሸንፋል፤ መግደል የሽንፈት ምልክት ነው፡፡ ዛሬ ተሸንፈዋል ነገም ይሸነፋሉ” ብለዋል በመግለጫቸው፡፡

የትዕይንተ ሕዝቡ አዘጋጅ፣ ስዩም ተሾመ ለዋሽንግተን ፖስት እንደተናገረው “አንድ ሰው ወደ መድረኩ ቦንብ ሊወረውር ሲል አጠገቡ ያለው ሰው የወርዋሪውን እጅ በመንካት የቦንቡን አቅጣጫ ወደሆነ ቦታ በመቀየር የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሕይወት ከአደጋ አትርፏል፡፡”

በሀገሪቱ ቴሌቪዥን በቀጥታ ሲተላለፍ የነበረው ትዕይንተ ሕዝብ የቦንቡ ጥቃት ከደረሰ በኋላ ተቋርጧል፡፡ በሀገር ውስጥ ያሉ ሚዲያዎች የቦንብ ጥቃቱን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የተቃጣ እንደነበር ዘግበዋል፡፡

የቦንብ ጥቃቱን ሊያደርሱ የሞከሩት ሰዎች የፖሊስ ልብስ ለብሰው እንደነበር የዐይን ምስክሮች ይገልፃሉ፡፡ በአደጋው የተፈጠረውን አሳዛኝ ሁኔታ ተከትሎ የዐቢይ አሕመድን ቲሸርት የለበሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ትዕይንተ ሕዝብ አድራጊዎች በተለያዩ የከተማይቱ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላቸውን ድጋፍ ሲገልጹ ተስተውሏል፡፡

### ቢቢሲ

በአዲስ አበባ ከተማ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. ማለዳ ላይ በተካሄደው “ዲሞክራሲን፣ ለውጥን እንደግፋለን” በሚል መሪ ቃል አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ለመደገፍ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር የአዲስ አበባና አካባቢዋ ነዋሪ በመስቀል አደባባይ ባደረገው ደማቅ ትዕይንተ ሕዝብ ላይ በተፈፀመ የቦንብ ጥቃት ሁለት ሰዋች ሲሞቱ፣ ከአንድ መቶ ሃምሣ በሚበልጡ ሰዎች ላይ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደርሷል፡፡

ከአደጋው ጋር በተያያዘ የከተማዋ ፖሊስ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር እና ሌሎች ስምንት የፖሊስ አባላት በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከአደጋው በኋላ በቴሌቪዥን በመቅረብ “አደጋው ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ማየት ከማይሹ ኃይሎች የተፈፀመ ያልተሳካ ሙከራ ነው” ሲሉ ድርጊቱን አውግዘዋል፡፡

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከተሾሙ ወዲህ በሀገሪቱ በርካታ የለውጥ እርምጃዎችን የወሰዱ ሲሆን፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድረ ገፆች ላይ የነበረው እገዳ እንዲነሣ፣ ሀገር ውስጥ እንዳይተላለፉ ታግደው የነበሩ የቴሌቪዥን ቻናሎችም ሥርጭታቸው እንዲተላለፍ ፈቅደዋል፡፡

### ሮይተር

የዩናይትድ ስቴት መንግሥት በቅዳሜው የመስቀል አደባባይ የደረሰውን የቦንብ ጥቃት በማውገዝ የኤፍ ቢ አይ የምርመራ ባለሙያዎችን ወደ ኢትዮጵያ መዲና እንደላከች አስታወቀች፡፡


እንድሮይተር ዘገባ የለውጥ አራማጁን አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ሥልጣን ከወጡ ጀምሮ ለወሰዷቸው ሥር ነቀል የፖለቲካና የኢኮኖሚ እርምጃዎች፤ እንዲሁም በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት ለወሰዱት በጎ ጅምር ምስጋና ለማቅረብ በተጠራው ሕዝባዊ ትዕይንተ ሕዝብ ላይ በደረሰው የቦንብ ጥቃት ጋራ በተያያዘ እስከ አሁን 30 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውም ታውቋል፡፡

### አልሐድ ኒውስ

ለለውጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈቱ ናቸው የተባሉትን አዲሱን ጠ/ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ለመደገፍ በብዙ መቶ ሺህ የሚገመት ሕዝብ ባለፈው ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን፣ ማለዳ በአዲስ አበባ፣ መስቀል አደባባይ ትዕይንተ ሕዝብ ተካሄዷል፡፡

በትዕይንተ ሕዝቡ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ “ለውጥ መጥቷል፤ ካሁን ወዲያ ወደ ኋላ አንመለስም፡፡ ለአንድ መቶ ዓመት የነገሠብን ጥላቻ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶብናል” ሲሉ ንግግራቸውን አጠቃለው ሕዝቡን ዝቅ ብለው ካመሰገኑ በኋላ ነበር የቦንብ አደጋው የደረሰው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጠባቂዎቻቸው ይዘዋቸው ሲሸሹ የሚያሳይ ምስል በመንግሥት ቴሌቪዥን ጣቢያ ስርጭት ላይም ታይቷል፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያውያን በዚህ በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የለውጥ ጅማሮ ላይ ደስተኛ አይደሉም፡፡ ለ27 ዓመታት በኢትዮጵያ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆነው የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ፓርቲ በመንግሥታቸው አቋም ላይ ለመነጋገር አስቸኳይ የማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል፡፡







ተረፈ ወርቁ




# ጠ/ሚ ዐቢይ በኔልሰን ማንዴላ የፍቅር እና የዕርቀ-ሰላም መንገድ ላይ...!!

## 1.እንደ መንደርደሪያ

የደቡብ አፍሪካው የነጻት ታጋይ፣ አርበኛና የዓለም ሰላም የኖቤል ተሸላሚው፣ ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ፣ ከ27 ዓመታት የወኅኒ ግዞት ወጥተው፤ እርሳቸውንና ሕዝባቸውን እጅግ አሰቃቂ ለሆነ ግፍና መከራ ለዳረጋቸው ለአፓርታይድ ዘረኛ መንግሥትና የሥርዓቱ ቀንደኛ አቀንቃኝ ለሆኑ መሪዎችና ደጋፊዎች ከልብ የሆነ ይቅርታ ማድረጋቸውን ባወጁበት፣ ለሕዝባቸው ባደረጉት ታሪካዊ ንግግራቸውም፤ "ለነገዪቱ ደቡብ አፍሪካ ብሩሕ ተስፋ ያለን ብቸኛው መንገድ ወይም አማራጭ "የፍቅር፣ 'የመደመር' የዕርቀ ሰላም መንገድ" ብቻ መሆኑን ባወጁ ማግሥት የለንደኑ ታይም መጽሔት በፊት ሽፋን ገጹ ላይ የኔልሰን ማንዴላን ትልቅ ምስል ያካተተ አንድ ወቅታዊ ዘገባ ይዞ ወጥቶ ነበር::


"ታይም" የኔልሰን ማንዴላን የካርቱን ምስል ይዞ የወጣበት መንገድ በወቅቱ ብዙዎችን ያስገረመና ያነጋገረ ጉዳይ ሆኖ ነበር:: መጽሔቱ የማንዴላን የራስ ቅል በጣም አግዝፎ የቀረውን አካላቸውን ደግሞ ትንሽ አድርጎ ነበር በካርቱን ምስሉ ያወጣቸው:: የዚህ የማንዴላ የካርቱን ምስል አንድምታም፤ "በኃይላቸው፣ በሠራዊታቸው ብዛትና በጠብመንጃ ኃይል ሳይሆን በአእምሮአቸው ታላቅነትና ብስለት፤ በፍቅር፣ በቅን ልቦና እና በማስተዋል ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን የሚመሩ፤ ብልህና ታላቅ የሆነ መሪን አፍሪካ አሁን ገና አገኘች፤" የሚል መልእክትን ለማስተላለፍ ነበር ይህን ምስል የተጠቀመበት::

በእርግጥም ሥልጣን የፈጣሪና የሕዝብ አደራ መሆኑን የዘነጉ፤ ሥልጣን ርስት፣ ጉልት በሆነባት አፍሪካችንና ኢትዮጵያችን፤ ለሥልጣናቸው ሲሉ በገዛ ሕዝባቸው ላይ ጦር ለማዝመት ወደኋላ የማይሉ፤ አፍሪካችን በደም አበላ እንድትዋኝ፣ ምድራችን የደም ምድር (አኬልዳማ) እንድትሆን ያደረጉ፤ ከአውሬ ያልተለዩ አምባገነን መሪዎችን ባየንባት አህጉራችን/ኢትዮጵያችን፣ የምርጫ ኮሮጆ ገልብጠውና የሕዝብን ድምፅ ወዲያ ብለው "ሥልጣን ወይም ሞት!" በሚል መፈክር ሕዝባቸው ላይ የጥይት ውርጅብኝ የሚያዘንቡ ብኩኖችን፤ በሙስናና በሌብነት ላይ የነገሡ አልጠግብ ባይ "የቀን ጅቦችን"፣ ግብዞችንና አስመሳዮችን፤ የእውነትና የፍትሕ ጠላቶች ነፍስ ሥጋችንን ባስጨነቁባት ኢትዮጵያችን፤ የአፍሪካዊውን፣ ታላቅ ጀግና የማንዴላን፤ "የእውነት፣ የፍቅር፣ የዕርቀ ሰላም መንገድ የሚከተል በፍቅር ልብ፣ በአእምሮ ብስለትና በማስተዋል ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን የሚመሩ መሪዎችን ማግኘት እንደ ታላቅ የምሥራች የሚቆጠር ነው::

ምዕራባውያኑ ታላላቅ ሚዲያዎች ለዚህም ይመስላል "የሰላም፣ የዕርቅ ሰው" የሆኑትን ኔልሰን ማንዴላን እንዳሞጋገሷቸውና ከፍ እንዳደረጓቸው ሁሉ፤ በተመሳሳይም ሰሞኑን እንደ ዋሽንተግተን ፖስት፣ ዘጋርዲያን ያሉ ጋዜጦችና ታላላቅ የመገናኛ ብዙኃን፤ የሀገራችንን የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር የዶ/ር ዐቢይ አሕመድን "የፍቅር፣ የዕርቀ ሰላም ጉዞ" ከግምት ውስጥ በማስገባት "ዳግመኛው አፍሪካዊው ማንዴላ" ሲሉ ለመጥራት የተገደዱት::

## 2.ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በማንዴላ የፍቅርና የዕርቅ መንገድ...!!

"Ethiopia always has a special place in my imagination and the prospect of visiting Ethiopia attracted me more strongly than a trip to France, England, and America combined. I felt I would be visiting my own genesis, unearthing the roots of what made me an African. ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤ በእኔና



በሕዝቤ ልብና ማንነት ውስጥ ያለው ሥፍራ እጅጉን ክቡርና የተለየ ነው፤ በዓለማችን ከሚገኙ ታላላቅ ሀገራት መካከል ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ሀገራት ጉብኝቴ ይልቅ፤ የመላው ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ፣ ሥልጣኔ፣ ቅርስና የአፍሪካዊ ማንነቴ ሥርና መሠረት የሆነችውን ሀገረ ኢትዮጵያን መጎብኘት በእኔና በሕዝቤ ልብ ውስጥ ልዩ ትርጉም፣ ልዩ ስፍራ አለው::" (ኔልሰን ማንዴላ)

በውድ ሀገራቸው በኢትዮጵያ፣ በሕዝባቸውና በአፍሪካ ምድር ፍቅር፣ ዕርቀ ሰላም፣ ብልጽግና ይሰፍን ዘንድ ምኞታቸው የሆነው የሀገራችን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ፤ ቅዳሜ ዕለት በተጠራው ታሪካዊና ታላቅ የድጋፍ ሰልፍ በለበሱት ካኔተራ/ቲሸርት ላይ የደቡብ አፍሪካውያን፣ የፀረ-አፓርታይድ ታጋይና የነጻነት አርበኛ፣ ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ ምስል እንዲሆን መፍቀዳቸው፣ የእኚህን ታላቅ አፍሪካዊ አድናቂያቸው ብቻ ሣይሆኑ በተግባርም የእርሳቸውን የዕርቀ ሰላም መንገድ ለመከተል መወሰናቸውን የሚያሳብቅ ነው::

ደቡብ አፍሪካውያን "ታታ ማዲባ (ታላቁ አባታችን)" በሚል የሚጠሯቸውና የሚያሞካሿቸው ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ የሀገራቸውን፣ የሕዝባቸውንና የእርሳቸውን እንደ መርግ የከበደ የመከራ፣ የግፍና የጭቆና ታሪክ፣ የአፍሪካንና ሕዝቦቿን የዘመናት የባርነትና የቅኝ ግዛት አሰቃቂ፣ የመከራ ዘመናት በፍቅር፣ በይቅርታ ዘግተው፤ ለ27 ዓመታት ከቀዝቃዛው የአትላንቲክ ውቅያኖስ ማዶ፤ በሮቢን ደሴት ወኅኒ ቤት ተግዘው፤ በዘረኛው የአፓርታይድ መንግሥት በውድ እናታቸውና በበኩር ወንድ ልጃቸውን እረፍተ ሞት ላይ እንኳን እንዳይገኙ ማእቀብ ተጥሎባቸው፤ እንደ መርግ የከበደ የእናታቸውን ህልፈት ለብቻቸው ሆነው በኀዘንና በቁጭት በትር እንዲገረፉ የፈረደባቸውን፤ ከትግል አጋራቸውና ከውድ ሚስታቸው ጋር እንኳን በስድስት ወር አንድ ጊዜ ለሠላሳ ደቂቃ ብቻ እንዲገናኙ የወሰነባቸውን፤ ያን በእርሳቸውና በሕዝባቸው ላይ አስከፊ የሆነውን የዘረኝነት ቀንበር የጫነባቸውን፤ መራራና አስከፊ፣ የሰቆቃ ሥርዓት ይቅር ብለው በአፍሪካና በዓለም ፊት አዲስ ታሪክ የጻፉት፤ የአፍሪካ ጥቁር አፈር ውድ ልጅ የሆኑት ማንዴላ፤ የጠ/ሚ ዐቢይ ሕያውና ታላቅ ተምሳሌት ሆነው በቅዳሜው የድጋፍ ሰልፍ ላይ ደምቀው ታይተዋል::

እኚህ የሀገራችን ጠ/ሚ የዶ/ር ዐቢይ ታላቅና ሕያው ተምሳሌት የሆኑ፣ የዕርቅና የሰላም ሰው፣ ደቡብ አፍሪካዊው የነጻነት ታጋይና አርበኛ፣ ኔልሰን ማንዴላ ከ27 ዓመታት ግዞት ነጻ በተለቀቁበት እ.ኤ.አ. የካቲት 11 ቀን 1990 ደስታቸውን ለመግለጽ ለተሰበሰቡ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ደቡብ አፍሪካውያን ሕዝባቸው፤ በኬፕታውን ከተማ ባደረጉት ንግግራቸው እንዲህ ነበር ያሉት፤

"I stand here before you not as a prophet but as a humble servant of you, the people. Your tireless and heroic sacrifices have made it possible for me to be here today. I therefore place the remaining years of my life in your hands. ደቡብ አፍሪካውያን ሕዝቦቼ ሆይ! በፊታችሁ የቆምሁት እንደ ነቢይ ሳይሆን እንደ ትሑት አገልጋያችሁና ታዛዣችሁ ሆኜ ነው፤ የእናንተ ድካም የለሽ ጀግንነታችሁና መሥዋዕትነታችሁ የዛሬ የነጻነት ቀን ዕውን እንዲሆን አድርጓል፤ ስለሆነም እናንተን በታማኝነትና በቅንነት ለማገልገል ቀሪ የሕይወት ዘመኔን በእጃችሁ አደራ እተዋለሁ::"

እንደ አፍሪካዊው ጀግና ኔልሰን ማንዴላ ሁሉ ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድም በሄዱባቸውና በተገኙባቸው የተለያዩ መድረኮች ሁሉ በሚያደርጓቸው ንግግሮቻቸውና ተግባሮቻቸው የሕዝብ አገልጋይነታቸውን ለማስመስከር፤ በፍቅር፣ በቅን ልቦና እና ትሕትና ተግተው በመሥራት ላይ ናቸው:: አይሁዳዊው፣ ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን፣ "ትጋት ለሰው የከበረ ሀብት ነው፤" እንዲል ጠ/ሚ ዐቢይ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ፤ ሀገራቸው ኢትዮጵያን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በመኳዝ የፍቅርን፣ የሰላምንና የዕርቅን ዘር ለመዝራት እየደከሙ፣ እየተጉ ነው:: "ፍቅር ያሸንፋል!" በሚል መርሕም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላለፉት ረጅም ዓመታት ጥላቻና መከፋፋት፣ መበላላትና መለያየት በነገሠበት የሀገራችን ጨለማው የፖለቲካ መንገድ ላይ የፍቅር ብርሃን ይበራበት፣ የይቅርታ ጎሕ ይደምቅበት ዘንድ እየተጉ፤ ሕዝባቸውን፣ የሥራ ባልደረቦቻቸውንና ፓርቲያቸውን ኢሕአዴግን ጭምር እያተጉ ነው::

## 3. ፍቅር ያሸንፋል!

ደቡብ አፍሪካዊው የነጻት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ፤ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እርሳቸው፣ የሕዝባቸውና የመላው ጥቁር ሕዝቦችና በአጠቃላይ የሰው ልጆች ሁሉ ግዙፍ ታሪክና ገናና ሥልጣኔ መነሻ፤ የሰው ልጆች የነጻነት፣ የተጋድሎ ክቡር ተምሳሌት… ወዘተ መሆኑን ባወጁበትና "Long Walk to Freedom" በሚል ረጅሙን የትግል ሕይወታቸውን በተረኩበት መጽሐፋቸው፤ "ፍቅር በማንኛውም ልብ ውስጥ በተፈጥሮ አለ፤ በተቃራኒው ጥላቻ ግን በትምህርት እንጂ በተፈጥሮ አይገኝም::" እንዳሉት ሁሉ ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ ይህን የፍቅር፣ የዕርቀ ሰላም መንገድ ለመኳዝ ረጅሙን ጉዞ ተያይዘውታል::

ጠ/ሚ ዐቢይ ባሳለፍነው ቅዳሜ በመስቀል አደባባይ በተጠራው ታሪካዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ የማንዴላ ምስል ያረፈበትን ካነቴራ ለብሰው መምጣታቸው፤ እኔም ለውድ ሀገሬ፣ ለዚህ ባለ ታሪክና ታላቅ ሕዝብ "የማንዴላን/የማዲባን የፍቅር፣ የሰላም፣ የእርቅ መንገድ እከተላለሁ!" በሚል መርሕ፤ የኢትዮጵያዊነትን የፍቅርና የአንድነት ቃል ኪዳን ከሕዝባቸው ጋር አብረው ለማደስ ቃል የገቡበት፤ ለውድ ሀገራቸውና ለውድ ሕዝባቸው፣ ምኞታቸውና ሕልማቸው "ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነት፣ መደመር" መሆኑን ዳግመኛ ያረጋገጡበት ታሪካዊ ዕለት ነው ማለት ይቻላል::

ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ማግሥት ጀምሮ ፍቅርን፣ ይቅርታን፣ ሰላምንና ዕርቅን በማወጅ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በቀደመ ታሪኳ ወደነበራት ገናና የሥልጣኔ፣ የታላቅነትና የክብር ሰገነት ትመለስ ዘንድ መወጣጫ መሰላሉ እና እንደ ሀገር ለመቀጠል ያለን ብቸኛ አማራጭ፤ "አንድነት፣ ሕብረት፣ መደመር ነው፤ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ፍቅር፣ ሰላም እንዲናኝ ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽኦ እናድርግ!" በማለት ደጋግመው ጥሪያቸውን ለሕዝባቸው አስተላልፈዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ ፍቅርን፣ ሰላምንና ዕርቅን ባስቀደሙበት ጉዞአቸው ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ውጪም ከምሥራቅ አፍሪካ እስከ ሰሜን አፍሪካ፤ እንዲሁም እስከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ድረስ ተጉዘው ለሕዝባቸው ያላቸውን ፍቅርና ክብር በተግባር ጭምር አሳይተውናል::

## ቅዳሜ ሰኔ 16ን በጨረፍታ፡-


የቅዳሜው የድጋፍ ሰልፍ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የፍቅር፣ የዕርቀ ሰላም ጥሪ፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት ድንበር ሳይለያቸውና ሳይከፋፍላቸው በአንድነት ሆነው፤ "እኛም ከጎንህ ነን፤ ኢትዮጵያና ሕዝቧን ታላቅ የማድረግ ክቡር ራእይህም ተካፋዮች ነን:: ጠቅላይ ሚኒስትራችን፤ "ሕልምህ ሕልማችን፣ ቁጭትህ ቁጭታችን፣ ተስፋህ ተስፋችን ነው!" በሚል ናፍቆት፣ ታላቅ ስሜትና ጉጉት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በፍቅር የታደሙበት ነበር፤ የቅዳሜው ዕለት የመስቀል አደባባዩ ታሪካዊ ሰልፍ:: በተቃራኒው ደግሞ የእውነት፣ የፍትሕ፣ የፍቅር፣ የሰላም ጠላቶችን ያስደነገጠ፣ ያስበረገገና የክፋት ምክራቸው የተናደበት፣ ታሪክ በቀለመ ወርቁ የከተበው ደማቅና ታሪካዊ ሰልፍ ሆኖ ነው ያለፈው::

ዕለቱ ይቅርታ ከፍ ያለበት፣ ፍቅር የነገሠበት ነበር:: ምንም እንኳን የቦንብ ፍንዳታው የሰልፉን ድባብ በኀዘን ቢያዳምነውም የሰልፉ ትዕይንት ግን ቃላት ከሚገልጸው በላይ እጅግ ልዩ ነበር:: ያልተሰማ የመፈክር ዓይነትና ያልተሰማ ዜማ አልነበረም:: ላለፉት ሃያ ዓመታት የታሰሩ መፈክሮችና ዜማዎች በነጻነት የአዲስ አበባን ጎዳናዎች አድምቀውት ነበር የዋሉት:: ሕፃን፣ ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ አርበኞች፣ አረጋውያን፣ ካህናት፣ መነኮሳት… ብቻ ምንም የቀረ የኅብረተሰብ ክፍል አልነበረም ማለት ይቻላል:: ደማቅና እጅግ የተዋበ ሰልፍ ነበር!!

በኢትዮጵያ ፍቅር ነፍሳቸው የተማረከ፣ በእናት ምድራቸው የአንድነት የተጋድሎ ታሪክ ብሔራዊ ኩራት፤ መንፈሳቸው ከፍ ያለ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በፍቅር ሸማ ጥበብ ደምቀው፤ በደስታ እንባ የታጠቡበት ቀን ሰኔ 16 ዕለት ቅዳሜ!! በዚህ የድጋፍ ሰልፍ ላይ የእናት ሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ በክብር ከፍ አድርገው የተሸከሙና የሚያውለበልቡ አረጋውያን አባቶችና እናቶች በዕንባ እየታጠቡ የኢትዮጵያን አምላክ በደስታ ሲቃ ተውጠው ሲያመሰግኑ ማየት ልዩ የሆነ ስሜትን የሚያጭር ነበር:: ይህ ፍቅር፣ ሰላም እና የይቅርታ መንፈስ በሀገራችንና በሕዝባችን መካከል ጸንቶ ይቀጥል ዘንድ የሁላችንም ጸሎትና ምኞት ነው::

*"Let Unity, Discipline and Peaceful Action become the Hallmark of Everything We Do! Viva Peace! Viva Democracy! አንድነት፣ ጨዋነትና ሰላምን መርሕ ያደረገ የለውጥ እንቅስቃሴ፤ በምናደርጋቸው በማንኛውም ድርጊታችን ዋና ቁልፍ ጉዳይ ይሁን! ቪቫ ለሰላም! ቪቫ ለዲሞክራሲ!" (ኔልሰን ማንዴላ)*

ሰላም ለኢትዮጵያ! ሰላም ለሀገራችን!







# “ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ገናናነቷ እንደምትመለስ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አይኑራችሁ”

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ

*ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሰኔ 16/2010 ዓ. ም. በመስቀል አደባባይ ለሕዝብ የተናሩት ሙሉ ንግግር*

የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ! ከሁሉም በፊት ኢትዮጵያን እንዲህ ለፍቅር፣ ለይቅርታ፣ ለአንድነት፣ ለመደመር ተሰባስበው ማየት ምን ያህል ተስፋ እንዳጫረብኝ ስነግራችሁ ታላቅ ክብርና ከፍተኛ ደስታ እየተሰማኝ ነው:: እናም ለወትሮው የንግግሬን ማሳረጊያ ለዛሬ የንግግሬ መጀመሪያ እንዳደርግ ይፈቀድልኝና ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ:: ገና ኃላፊነት ከተረከብን መንፈቅ ሳይሞላን፤ ፊት ለፊታችን እንደ ተራራ የተቆለለውን ግርዶሽ ሳንገፍ፤ ፊት ለፊታችሁ ቆመን ምስጋናን ለመቀበል የሚያስችለን አቅም አላደራጀንም:: ነገር ግን ጥላቻ አክስሮናል፣ አጉድሎናል፤ ፍቅር ግን ያጠግባል:: ያሻግራል ብላችሁ በተስፋ ተሞልታችሁ በምስጋና ጀምራችኋልና በፍቅርና በአንድነት ጀምሮ መጨረስ የተሳነው ስለሌለ የዛሬው የፍቅርና የምስጋና ቀን መድረስ ከሚገባን ማማ የሚያደርሰን የመጀመሪያው ጡብ መቀመጡን ያሳየናል::

የዛሬዋን ቀን እንድናይ፤ የዛሬዋን ቀን ያላዩ፤ እንድንኖር ሲሉ የሞቱ፤ እንድንከብር ሲሉ የተዋረዱ፤ እንድንፈታ ሲሉ የታሰሩ፤ ለሕይወታችን ሕይወታቸውን የገበሩ ሰማዕታትን በዚህ በተከበረ ቦታ ቆመን ልናመሰግናቸው ይገባናል:: ያለ እኛ ሊኖሩ ይችሉ ነበር:: ያለእነርሱ ግን እኛ መኖር አይቻለንም:: ይህቺ የፈጣሪ ጥበብ መጀመሪያ አገር ኢትዮጵያ፤ ይህቺ የሰማንያ ውብ ውብ ጌጦች ኢትዮጵያ፤ ይህቺ የሰው ልጅ እስትንፋስ መጀመሪያ አገር ኢትዮጵያ፤ ይህቺ የጥቁር ህዝቦች የነፃነትና ያልበገር ባይነት ተምሳሌት አገር ኢትዮጵያ፤ ሁለት ወር ሠርቶ ለምስጋና የሚታበይ መሪ ሳይሆን ችግሯን ሰምቶ ከሥሯ የሚነቃቀልላት መሪ ያስፈልጋታል::

መሪ ግን ያለህዝብ ፍቅር ባዳ ነው፤ መሪ ግን ያለህዝብ አንድነት ባዶ ነው:: አዎ መሪ ያለህዝብ አለኝታነት ከንቱ ነው:: እናም ዛሬ የመጣሁት እስከዛሬ ለሰጣችሁን ፍቅር ላመሰግናችሁ ነው:: አዎ የመጣሁት ይህንን ከባድ ኃላፊነት ከተረከብንባት የመጀመሪያዋ ቀን ጀምሮ ላሳያችሁን አለኝታነት ላከብራችሁ ነው::

ዛሬ የመጣሁት፤ የተረከብናት ሀገር ለበርካቶች የሚተርፍ ሀብት ያላት፤ ግን ፍቅር የተራበች ሀገር መሆኗን ፊት ለፊት ልነግራችሁ ነው:: ያለንን እየጣልን፣ የሌለንን ለመፈለግ ስንባዝን እንደከረምንና እንዳንራመድ ጠፍሮ የያዘንን ጥላቻና ቂም በፍቅር ከበጣጠስን ወደሚገባን የእድገት ማማ መውጣት እንደማይሳነን ላበስራችሁ ጭምር ነው:: በመሆኑም እርስ በእርስ ያለመመዘኛ የተዋደዳችሁ እለት ያኔ እኔንና ከእኔ ጋር ሲለፉ የቆዩትን ባልደረቦቼን እንዳመሰገናችኋቸው ይቆጠራል:: ሌብነትን እምቢ አሻፈረኝ ያላችሁ እለት እኔን እንዳመሰገናችሁ ይቆጠራል:: ይህ ክልል የኔ ነው፤ ይህ ወሰን የኔ ነው፤ ውጡልን መባባል አቁመን በፍቅር ተግተን ለሀገራችን መሥራት የጀመርን ዕለት ያኔ ምስጋናችሁን በሌላችሁበት እንደደረሰን ቁጠሩት::


ከምሥራቅ ጫፍ እስከ ምዕራብ ጫፍ፤ ከደቡብ ጫፍ እስከ ሰሜን ጫፍ የምንዋደድበት፣ የምንደመርበት፤ ቤተ መንግሥቱም፣ ፓርላማውም ለህዝቦቹ ክፍት የሚሆንበት ዘመን እንዲመጣ፤ ልጆቻችሁን ከፊደል እኩል የሀገር ፍቅር አስተምራችሁ ኢትዮጵያዊነትን ያላበሳችኋቸው ዕለት፤ ያኔ ምስጋናችሁ በፍሬ ይደርሰናል:: እናቶች፣ እህቶች በአጠቃላይ ሴቶችን በአክብሮት የተቀበላችሁ ዕለት ያኔ ምስጋናችሁን ዓለም ያስተውለዋል:: ያለ ሌላ ተደራቢ ምክንያት ስለሀገር ፍቅር ብላችሁ ለአካባቢያችሁ ዕድገት መቆርቆርና መቆጨት ስትጀምሩ፣ በተግባርም ስትተጉ፤ ያኔ ምስጋናችሁ ከልብ ይሆናል::

ዓላማችን ሩቅ ነው፤ ግባችን እጅግ ሰፊ ነው:: ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ገናናነቷ እንደምትመለስ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አይኑራችሁ:: ወደ ብልጽግና መሻገሪያው አቅጣጫ ግን ይቅርታ ፍቅር መደመር መሆናቸውን ደግሜ ላበስራችሁ እወዳለሁ:: ሆኖም ግን ለውጥ ጥቂት ተጨዋቾችንና ብዙ ተመልካቾችን አይፈልግም፤ ለውጥ የሁላችንንም ሜዳ ውስጥ ገብቶ መጫወት የሚፈልግ ሂደት ነው:: ተመልካቾች ውጤት ሲመጣ ሊያጨበጭቡ፤ ውጤት ሲጠፋ ሊወቅሱ በዙሪያው የሚመለከቱት ጨዋታ አይደለም:: ልዩነቱ የምንጫወትበት ሥልጣን፣ ኃላፊነት፣ አቅም፣ ቦታና ድርሻ ብቻ ነው::

ምሁራን የበሰለ ሐሳብ አምጡ፣ ባለሙያዎች አዲስ አሠራሮችን አመላክቱ፣ የእምነት አባቶች ዘረኝነትንና ሙስናን አጥፍታችሁ፤ ድሃ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ በሉ:: በውጭ ዓለም የምትኖሩ ወገኖች ዞሮ መግቢያ ሀገራችሁ የሆነችውን ኢትዮጵያን በሀብትም በዕውቀትም በነገር ሁሉ ዕለት በዕለት እንድታስቡ:: ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የትናንትናውን እርሱ፤ ለመደመር በይቅርታና በቅን ልቦና ትጉ:: ወጣቶች ወገባችሁን አስራችሁ ለሥራና ለዕድገት ተሰለፉ:: አባቶች ምከሩ፤ እናቶች ዝከሩ፤ ጎልማሶች ምሩ፤ መምህራን እውቀት ዝሩ፤ ተማሪዎች በርትታችሁ አጥኑ:: በትጋትና በተስፋ ወደፊት ተራመዱ::

ሀገራችንን ከወደድን ግዴታችንን እንወጣ፤ መብታችንንም እንጠይቅ:: ሀገራችንን ከወደድን ሥልጣን ኃላፊነት እንጂ ገዥነት አይሁን:: ሹመት ማገልገያ እንጂ መገልገያ አይሁን:: ሌብነት ጥዩፍ እንጂ ኩራት አይሁን:: ሀገራችንን ከወደድን የሚፈናቀል ሰውና የሚንገላታው እያንዳንዱ ዜጋ ኢትዮጵያዊ ነው ብለን እንቁምለት:: ሀገራችንን ከወደድን የምትባክነው እያንዳንዷ ሳንቲም የኢትዮጵያ ናት ብለን እንሳሳላት:: ሀገራችንን ከወደድን የምትጠፋ እያንዳንዷ የሥራ ሰዓት የኢትዮጵያ ናት ብለን እንቆርቆርላት:: ሀገራችንን ከወደድን የሚበላሸው እያንዳንዱ ንብረት የእናቴ ኢትዮጵያ ነው ብለን እንጨህለት:: ሀገራችንን ከወደድን በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል አንድ ኢትዮጵያዊ መብቱ ሲጣስ ብሔሩን ወይም ሃይማኖቱን ወይም ሌላ ማንነቱን ሳንመለከት ወገኔ ተነካ ብለን እንቁምለት::

ኢትዮጵያ ተነካች፤ ኢትዮጵያ ተነካ ብለን እንቁምለት:: ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ:: ሁላችንም ለኢትዮጵያ እናስፈልጋታለን፤ ኢትዮጵያም ለሁላችንም ታስፈልገናለች:: ኢትዮጵያችንን ሊተካ የሚችል አንዳች ነገር አልተሰጠንምና:: ኢትዮጵያ የድህነት ክንብንቧን አውልቃ እንድትጥል ቢተባበሩ ተራራ ሊንዱ የሚችሉ የልጆቿ ክንዶች ከተሸበቡበት የስንፍና ►



ግርዶሽ ተላቀው ቀን ከሌሊት ሊተጉ ይገባል:: ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሰላም ማማ እንድትሆን፣ ከጎረቤቶቿ ጋር ያላትን ግኑኝነት በፍቅር እና በመተሳሰብ እንዲሁም አብሮ በማደግ መርህ ላይ የተመሰረተ ልታደርግ ይገባል::

ኢትዮጵያ ሀገራችን ታላቅ እና ገናና ሀገር ናት:: ከድንጋይ እስከ ወረቀት ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ የዘለቀ የስነ ጽሑፍ ታሪክ ያላት፤ በራሷ ዜማ የምታዜም፤ በራሷ ምት የምትንቀሳቀስ፤ በራሷ ኮርታ የኖረች በራሷ ራሷን ጠብቃ የዘለቀች ሀገር ናት:: ይህ ሁሉ ሀብታችን፣ ታሪካችን እና ኩራታችን ግን ነፃነትን ፍትሕን ዴሞክራሲን በኢኮኖሚ መበልፀግን ማምጣት ካልቻለ ኩራት እንጂ እራት ሊሆነን አይችልም::

ነፃ የሆነች አገር መገንባት እና ነፃ የሆነ ሕዝብ መገንባት ይለያያል:: በነፃ አገር ነፃ ህዝብ ከሌለ፣ ነፃነት ቦታው የቱ ጋር ነው? የክልል ወሰኖች ድንበሮች ከሆኑ፣ የሚያስተሳስሩንን ድልድዮች ትተን የሚለያዩንን ግንቦች ከገነባን፣ የሺህ ዓመታት ነፃነት ትርጉሙ እና ጥቅሙ የቱ ላይ ነው? ለመናገር፣ ለመጻፍ ከፈራን፣ ከሰጋን፤ ለመደራጀት እና ለመንቀሳቀስ ከተጨነቅን እና ከተደበቅን፤ የሺ ዓመታት ነፃነት ትርጉሙ እና ጥቅሙ የቱ ላይ ነው?

አንዱ ብሔር ሌላውን መጣብኝ ካለ፤ ውጣልኝ፣ ሂድልኝ ካለ፤ ይሄኛው የኢትዮጵያ ክፍል የእኔ እንጂ የአንተ አይደለም ካለ፤ ታዲያ ቅኝ ገገርዎች ከዚህ የባሰ ምን ያደርጉ ነበር? በመጨረሻም አንድ ልብ እንድትሉ የምፈልገው ጉዳይ፤ ግለሰቦችን ከህዝቦች እንለይ:: እሾኹን ከጽጌሬዳው እንነጥል:: አይጥ በበላ ዳዋ አይመታ:: በአንድ ጠማማ ዛፍ ምክንያት ደኑ አይለቅ:: ከይቅርታ የተሻለ ማሸነፊያ መንገድ አለመኖሩን በየዕለቱ አንዘንጋ::

በዚህ አጋጣሚ፣ ይህ ዛሬ ከህዝባችን የተሰጠን ወሰን የሌለው ፍቅር፤ ቀን ከሌሊት ያለ እረፍት ለሚተጉ የህዝብ አገልጋይ ለሆኑ ባልደረቦቼ ጭምር መሆኑን እየገለፅሁ፣ ዛሬ እዚህ ያሳያችሁን ወደር የሌለው ፍቅር ህዝብ ተቀብሎናል ብለን የሚያኩራራን ሳይሆን፤ ለበለጠ ትጋት ለበለጠ ታታሪነት የሚያነሣሣን መሆኑን ከልብ በመነጨ ጥልቅ ስሜት ልገልፅላችሁ እወዳለሁ:: እያንዳንዷን ደቂቃ፣ እያንዳንዷን ሰዓት፤ በታማኝነት እና በፍቅር ከሌብነት ፀድተን፤ ከዘር ፀድተን፤ ፍትሕ እና ዴሞክራሲን በሚያመጣ አቅጣጫ በፍፁም ትሁት ልብ እንደምናገለግላችሁ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ::

ማሳረጊያውን ዐረፍተ ነገር ከመናገሬ በፊት፣ ውድ እህቶቼንና ወንድሞቼን የምለምናችሁ፣ ላለፈው አንድ መቶ ዓመት ጥላቻ ቀልዶብናል፤ ጥላቻ ሸብቦናል፤ ለእኔ ብቻ ሆዳምነት፣ ግለኝነት ጎድቶናል:: የተወደዳችሁ ወገኖቼ ሆይ! ይህንን ሁሉ በደል፤ ይህንን ሁሉ ችግር፤ ይህንን ሁሉ ታሪክ፤ አሸንፈን እንድንሻገር የሚያደርገን ግን ይቅርታና ፍቅር ብቻ ነው:: በቀል የደካሞች ነው ኢትዮጵያውያን ደካሞች ስላልሆንን አንበቀልም፤ በፍቅር እናሸንፋለን:: እያንዳንዱ ወንድምና እህት ከጎኑ ያለውን ሰው በማቀፍ እንደሚወደውና ይቅርታ እንዳደረገለት ይህ የዛሬ ቀን የፍቅር ቀን እንደሆነ ከጎኑ ያለውን በማቀፍ በፍቅር እንዲያረጋግጥ እጠይቃለሁ:: ኢትዮጵያ በልጆቿ ታቅፋና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ! አመሰግናለሁ::!

# "የዛሬው መሥዋዕትነት ከኢትዮጵያውያን ፍቅር ሰላም እና አንድነት የተከፈለ ነው"

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ**

"የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ጥላቻን፣ ገዳይነትን ክፋትን በተባበረ ክንድ ማሸነፍ ስለቻላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ:: ይህ ቀን ኢትዮጵያውያን ተደምረው በፍቅርና በይቅርታ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ፍቅር እንዲዘንብ ያደረጉበት ዕለት ቢሆንም ይህን የማይፈልጉ ኃይላት በተጠና፣ በታቀደ መልኩ እና ሙያን ታግዘው፤ ይህን ደማቅ ሥነ ሥርዓት ለማደፍረስ፣ ለማበላሸት፣ የሰው ሕይወት ለመቅጠፍ፣ ደም ለማፍሰስ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: አጠቃላይ ዓላማቸው የጨነገፈ፣ ያልተሳካ፣ የከሰረና የወደቀ ቢሆንም ጥቂት ኢትዮጵያውያን እንዲጎዱ ሆኗል::

በመጀመሪያ ለዚህ ክቡር ዓላማ፣ ለኢትዮጵያ ፍቅር እና ይቅርታ ሲሉ ሕይወታቸውን ላጡ ወንድምና እህቶቼ፤ ለቆሰሉ ወገኖች ቤተሰብ ሁሉ መጽናናትን እየተመኘሁ፤ የዛሬው መሥዋዕትነት ለኢትዮጵያውያን ፍቅር ሰላም እና አንድነት የተከፈለ እና ሁሌም የምናስታውሰው ነው:: ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ይህቺንም ቀን ያመጣነው በመሥዋዕትነት እና ብዙዎችን አጥተንበት ያመጣነው ቀን ስለሆነ ከመሥዋዕት ውጪ ያላገኘነው፤ ከመሥዋዕት ውጪ የማንጠብቀው ነገር መኖሩን የተማርንበት ዕለት ነው::

የሆነው ሆኖ ዛሬም ለኢትዮጵያውያን ወንድሞቼ ላበስር የምፈልገው ፍቅርና ይቅርታ ያሸንፋል:: መግደል መሸነፍና መዋረድ ነው:: በደስታ አንድ ሆኖ አገሬን የሚል ሕዝብ በራሱ ዜጋ ሰዎች አቅዶ አስቦ እንዲጨነግፍ መሥራት ትንሽነት ነው:: ኢትዮጵያውያን ግን ትንሽ አይደለንም:: ኢትዮጵያውያን ትልቅ ህዝቦች ነን:: ከትንንሽ ሰዎች ጋር ወርደን ትንሽ አንሆንም:: ይህንን ደስታና ፍቅራችንን ለማጨለም፤ አንድነታችንን ለማደፍረስ ያሰባችሁ ኃይሎች አልተሳካላችሁም::

ኢትዮጵያ አሁንም ለፍቅር፣ ለይቅርታ፣ ለአንድነት የዘረጋችው እጇ አይታጠፍም:: በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የሚዘንበው ሰላም እና ፍቅር አይቀየርም:: ይህ እንዲሆን የምትተጉ ሰዎች ትናንት አልተሳካላችሁም፤ ዛሬም አልተሳካላችሁም፤ ነገም አይሳካላችሁም:: አሁንም ልመክራችሁ የምፈልገው ከዚህ እኩይ ተግባር በመመለስ መንግሥት እና ሕዝብ ወደአልተገባ አቅጣጫ እንዳይሄዱ ጥንቃቄ ማድረግ ቢቻልና መታረም ቢቻል መልካም ነው ብዬ አስባለሁ::

የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረው ልበ ሰፊነት፤ ጠንካራነት እና የመደመር እሳቤ በትናንሽ ክስተቶች ወደኋላ መመለስ ስለሌለበት ይህንን ነገር ላደረጉ እኩይ ሰዎች ያዘንን ሲሆን የተሰው ሰዎች ነፍሳቸው በገነት እንዲያርፍ፤ የቆሰሉ ሰዎች እንዲታከሙ እና ቤተሰቦቻቸውም እንዲጽናኑ እመኛለሁ:: ዛሬ የተሰው ሰዎች ቤተሰቦቻቸው መላው ኢትዮጵያዊ ነው:: የእኔም ወንድሞች እና የሁላችን ወንድሞች ናችሁ:: ለሁላችን እህትና ወንድም፣ ወገን እና ቤተሰብ ናቸው:: ይህን እያሰብን ሁሌም የምንዘክራቸው ሲሆን በአጠቃላይ ለፍቅር እና የነበረውን መሥዋዕትነት ማሳረጊያ ይሆናል ብዬ አስባለሁ::

ጉዳዩ እንዴት እንደተፈጸመ ዝርዝር ጥናት ፖሊሶች እያካሄዱ ሲሆን፣ ጥናቱ ሲጠናቀቅ ለሕዝብ ይፋ ይሆናል:: እስከዚያ ድረስ በአካባቢው የነበራችሁ ሰዎች ያያችሁትንና የሰማችሁትን ማንኛውም ምልክት ለፖሊስ እንድታሳውቁ አደራ እያልኩ ተባብረን በመሥራት ጥላቻና ክፋትን እናሸንፋለን:: ኢትዮጵያ ከጀመረችው የፍቅርና የይቅርታ መንገድ ሊገታት የሚችል ኃይል የለም:: የተሸነፈ የወደቀ ሃሳብ ነው:: በተሸነፈ እና በወደቀ ሃሳብ እንደማንቆም ዳግም ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ:: አመሰግናለሁ::" ***ጠ/ሚ ዐቢይ ከቦንቡ ጥቃት በኋላ የሰጡት መግለጫ***

# "የይቅርታ ጉዞአችን ከተደናቀፈ፣ ተሸንፈናል ማለት ነው"

***ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ***

ወንድምና እህቶቻችን ደማቸው ፈስሷል፤ ለነርሱ ደም መለገስ ያስፈልጋል:: የዕለቱ አስፈላጊነት የነበረው ኢትዮጵያ የተራበችው ፍቅር ነው፤ ፍቅር የተራበውን ህዝባችንን ፍቅር ለመመገብና እኛም ፍቅር ለመቀበል የነበረን ጥረት ፍቅር በማይወዱ ኃይሎች፤ በከንቱ ወንድምና እህቶቻችን ደማቸው ፈሷል:: ያንን የፈሰሰ ደም ለመተካት ጤነኞች፣ በዕለቱ ደግሞ ምንም ጉዳት ያልደረሰብን ሰዎች ደም በመለገስ ፍቅራችንን ልናረጋግጥ ነው:: ፍቅር በመስጠት፣ ፍቅር በመቀበል፣ በይቅርታ የኢትዮጵያን መፃኢ ጉዞ ማሳመር ስለሚቻል:: ከፍቅር ውጪ ያለው ሁሉም መንገድ ከንቱ ነው::


የማስተላልፈው መልዕክት ሰው ሆኖ የማይሞት የለም:: ለሀገር መሞት ግን ክብር ነው:: መሞትን ማስቀረት አይቻልም:: ጊዜውን ማርዘም ወይ ማሳጠር ነው የሚቻለው እና ይጠርም ይርዘምም ለኢትዮጵያ የሚከፈል ዋጋ ክብር ነው:: ለሞት የሚሣሣ በተለይ ሕይወታችንን ለሀገር ለመስጠት የምንሣሣ እንዳልሆንና በማንኛውም ሰዓት ለኢትዮጵያ ደማችንን ሰጥተን፤ ግን ለፍቅር፣ ለይቅርታና ለእድገት ሲሆን የማንሣሣ መሆኑንና እንደማያቆሙን በዚህ አጋጣሚ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ:: ኢትዮጵያውያን ወገኖች ደግሞ የጀመርነውን የፍቅርና የይቅርታ ጉዞ እንቀጥል:: የይቅርታ ጉዞአችን ከተደናቀፈ፣ ተሸንፈናል ማለት ነው:: ፍቅርና ይቅርታ መቀጠል የለበትም፤ አንድ መሆን የለባችሁም ብለው ሰዎች ሲረብሹን የኛን ዓላማ ጥለን የነርሱን ከተከተልን ተሸንፈናል:: እኛ አንሸነፍም፤ ደማችንን፣ ጊዜያችንን፣ ሕይወታችንን፣ ዕውቀታችንን ሠውተን፤ ፍቅርና ይቅርታን ኢትዮጵያ ውስጥ እናመጣለን:: አንድ ሆነን እንበለጽጋለን:: ህዝባችን ከዓላማው ዝንፍ ሳይል፤ በትንኮሳ ሳይሸነፍ፤ ወደ ፍቅር የጀመርነውን ጉዞ እንዲያቀጣጥል፣ እንዲያፈጥን የአደራ ጥሪ አቀርባለሁ:: ለተጎዱ ወገኖቻችን በሕይወታቸው ለመድረስ ሁላችንም ደም መለገስ አለብን፤ ይሄም ፍቅር ስለሆነ:: አመሰግናለሁ::

***ጠ/ሚ ዐቢይ ደም ሲለግሱ ያስተላለፉት***



# የፖለቲካ ሰዎች ስለ ሰላማዊ ሰልፉ

## ፕ/ር መስፍን ወልደ ማርያም



እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይና መከራ አይቶ ዓቢይ አህመድን ፈጠረውና ወደኢትዮጵያ ላከው፤ ስለዚህም እንደአንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ኑሮውን አደላድሎ በመኖር ፋንታ ከተሰየመበት ቀን ጀምሮ ሳያርፍ በየቦታው እየዞረ ፍቅርን ሲሰብክና እስረኞችን ሲያስፈታ ቆየ፤ ከዚያም በላይ ከጎረቤት አገሮች ጋርም በመወዳጀት እስረኞች ሁሉ እንዲፈቱ አደረገ፤ በቴሌቪዥንና በራድዮ ሕዝብ ነጻ አስተያየቱን እንዲገልጽ አደረገ፤ ከኤርትራ ጋር የእርቅ በር ከፈተ፤ ለግንቦት 7 እንዲሁ የእርቅ በር ከፈተ፤ የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻል ውጥኖችን ነግሮናል፤ በየቀበሌውና በየፖሊስ ጣቢያው ንጹሓን የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሰሩ ማሰቃየቱ እንዲቆም አድርጓል፤ በሦስት ወር ያህል ጊዜ ከዚህ በላይ እንዲሠራ ለመጠበቅ አንችልም።

የፊታችን ቅዳሜ ጠቅላይ ሚኒስትርን ለመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ ይደረጋል፤ በሰልፉ የሚሳተፍ እያንዳንዱ ሰው በጎኑ ያለው የሚያደርገውን ማየትና መቆጣጠር የሰልፉ ጤንነት ይሆናል፤ በሚያዝያ 30፣ 1997 ቅንጅት የተጠቀመበት ዘዴ ነው።

## ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም

በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የነበሩ የጥላቻን፣ ህዝብ የመከፋፈልንና የመሳሰለውን ፖለቲካ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት ጠ/ሚኒስትሩ በሚያደርጉት ጥረት ከጎናቸው እንደምቆምና እንደማበረታታቸው፤ ሁለተኛ ደግሞ ኔልሰን ማንዴላ መልካምና ዕርቅ ብለው በሰየሙልን መንገድ በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር አብሬ እንደምጓዝ፤ በሦስተኛ ደረጃ በኢትዮጵያዊነት መንፈስና በበጎ አድራጎት፤ የዘር፣ የጎሳ ጥላቻንና ህዝብን የሚያራርቁ ነገሮችን አጥፍተን ሰላምና ፍቅር ለመመሥረት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብሬ እንደምቆም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ከማናቸውም ከመንደር አንሥቶ እስከ ትልልቅ ከተማና መዲና ድረስ ሁላችንም ተባብረን የሰላምና የእርቅ ዘመቻ ከማካሄድ በተጨማሪ፤ ሁሉንም በማካተት ወደፊት መጓዝ የሚያስችለን መንገድ የሚያስፈልገን መሆኑን መረዳት እንደሚገባን::



በዚህም ላይ ደግሞ በግሌም ሆነ ከኔ ጋር ያሉትን ባለሙያዎች በማደራጀት አብረው ከሕዝቡ ጋር እንዲሰለፉ ለማድረግ ዲያስፖራዎችን ለማንቀሳቀስ ጥረት እንደማደርግ:: በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስኋቸውን በሙሉ የአዲስ አበባ ሕዝብ እኔን ወክሎ ለጠ/ሚኒስትሩ እንዲስያተላልፍልኝ በጽሑፍ በትኛለሁ::



## ግርማ ሰይፉ

ቅዳሜ ሰኔ 16/2010 የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ስሙ የሚመጥነው ነው:: በእውነትም ሰላማዊ ነው:: ሕዝቡም በከፍተኛ ጥንቃቄ ደህንነቱን አስከብሮ፣ እንደ ወርቅ ተፈትኖ ሰላማዊነቱን አረጋግጧል:: ይህ ሰልፍ በሕዝብ ገንዘብ መዋጮ የተደረገ መሆኑም አስደማሚ ነው:: ሌብነት ያልፈቀደ ሰላማዊ ሰልፍ:: በምንም መለኪያ በፍላጎት የተደረገ ስለሆነ እጅግ አስደሳች መሆኑን መደበቅ አይቻልም:: ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ በሚደረጉ ሰልፎች በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ዜጎችን፣ በኑሮ ደካማ የሆኑ እናቶችን፣ በተለያየ ሁኔታ ኑሮአቸው ከመንግሥት ጋር የተያያዙ ሰዎችን በማስገደድ ከተደረጉት ሰልፎች ጋር ፈፅሞ ተመሳሳይነት የለውም::

ለማሸበር የተደረገ ድርጊትን ያደበዘዘ፤ ሽብሩ አንድነትን የበለጠ ያጠበቀበት መሆኑ ደግሞ አስደማሚ ነው:: አሁንም እንደመር እንላለን:: እኛ ኢትዮጵያውያን ነን፤ በጋራ የሚያገናኘን ይህ ነው:: ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጋሞ፣ ጉራጌ፣ ሲዳማ፣ ደራሼ፣ ኮንሶ፣ አማራ፣ ...ወዘተ መሆናችንን የማይነጥቀን ኢትዮጵያዊነት ለዘላለም ይኑር::

## ዶ/ር አረጋዊ በርሄ



ለኢትዮጵያ የመጣውን ለውጥ ለማደናቀፍ የሚያስቡና ለውጡን የሚነቅፉ ወገኖች እንዳሉ ሁላችን እናውቃለን:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ የዱሮ ተጠቃሚዎች ናቸው:: በቻሉት መንገድ አዲስ አበባም ይሁን ሌላ አካባቢ ሁከት መፍጠር ይፈልጋሉ፤ ለምሳሌ፡- መቐሌ አካባቢ የሠማዕታት ቀን ብለው ‘ህወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ነው፤ የሚለያያቸው የለም’ እያሉ በኦሮምኛ ሳይቀር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያስተላልፉት መልዕክት፤ በኢትዮጵያ በአንድነት ለውጥ ለማምጣት እየተካሄደ ያለውን ጉዞ ለማደናቀፍ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ወደተሻለ የአንድነት፣ የእኩልነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት በምታደርገው ግስጋሴ ቀኝ እጃቸውን ሰጥተው ማበረታታት ሲገባቸው፤ በጎን እየመጡ ሊያደናቅፉ መሆኑን ህዝቡ ልብ እንዲለው፤ የሚያስተላልፉት መልዕክትም ዋጋ ቢስ መሆኑን እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ነው:: በተለይ አሁን ያለው የትግራይ ወጣትም ይህንን እኩይ የሆነ አካሄድ ተገንዝቦ ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲና ለብልፅግና በሚደረገው ትግል ደጋፊ እንዲሆን በጥብቅ አሳስባለሁ::

## ሀብታሙ አያሌው



የለውጥ ሂደት ቀልባሾቹ የቀን ጅቦች ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ለመግደል አዘጋጅተው የነበረው ሦስት F1 በመባል የሚታወቁ የእጅ ቦምቦችን ነበር። ቦምቦቹ በፈነዱበት ቦታ የተጠመዱ አልነበሩም:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ከሚያደርጉበት መድረክ በስተግራ በቀላሉ ወርውሮ ጉዳት ለማድረስ በሚያስችል ሁኔታ ዝግጅት የተደረገበት ነበር። ጠቅላዩ ንግግራቸውን ጨርሰው እንደተቀመጡ ወርዋሪው ፊውዙን ነቅሎ ቦምቡን ሲወረውር አንድ የሰልፍ ታዳሚ ስላየው እጁን መትቶ አስጣለው፤ ቦንቡም ያለቦታው ፈነዳ። የፈነዳው አንዱ ሲሆን ሁለቱ ሳይፈነዳ ለመያዝ በቃ። ይህ ባይሆን ኖሮ ሁኔታዎች ከዚህ በላይ ይከፉ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍንዳታው በኋላ በሰጡት መግለጫ “ሆን ብለው አቅደው፣ በሙያ ታግዘው፣ የራስን ዜጋ ለመግደል” እንዳሉ ልብ ስንል፤ ከፍንዳታው በስተጀርባ የቀን ጅቦቹ መቆማቸውን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ለሞቱት ነፍስ ይማር፤ ለቤተሰብም ሆነ ለሁላችን ፈጣሪ መፅናናቱን ይስጠን። ታጋይ ይሞታል፤ ትግሉ ይቀጥላል:: ድል የህዝብ መሆኑ የማይቀር ነው።

ያንን ሁሉ ጥብቅ ፍተሻ ቦምቡ እንዴት አለፈ? ከፍንዳታው በኋላስ የፖሊስ መኪናው ለምን እንዲቃጠል ተደረገ? ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

















# የሰኔ 16ቱ ትዕይንተ ሕዝብ















